3ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች ዘመዶቻቸውን ወይም ከራሳቸው ጐሳ ለይተው ለአመራር ሲመርጡ ስላየህበት ሁኔታ አብራራ:: ለ) እንዲህ ያለው ድርጊት በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያመጣው ውጤት ምን ነበር? ሐ) የመሪዎችን ምርጫ እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠር ማመን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ሐ) <u>መሪ ለመሆን ግፊት ልናደርግ ወይም በሥልጣናችን ላይ ለመቆየት መታገል የለብንም</u>:: ሰዎች እኛን እንዲመርጡ ልንነግራቸው ወይም መሪነታችንን የሚያበረታቱ ነገሮችን ማድረግ የለብንም:: ያንን ካደረግን፣ እግዚአብሔር ማን የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን እለበት የሚለውን ነገር መወሰን እለበት ብለን እንደማናምን ተናገርን ማለት ነው:: የዳዊትና የሳኦልን ታሪክ ታስታውሳለህ:: እግዚአብሔር ዳዊት መሪ እንዲሆን ከመረጠው በኋላ፣ እግዚአብሔር በንግሥና ላይ እስኪያስቀምጠው ድረስ ዳዊት 13 ዓመታት መቆየት ነበረበት:: ሁለት ጊዜ ዳዊት ሳኦልን ገድሎ በፍጥነት መሪ መሆን የሚችልበት ዕድል አጋጥሞት ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በቀባው መሪ ላይ እጄን አላነሣም አለ:: ዳዊት መሪዎችን የሚያስቀምጠው እግዚአብሔር እንደ ሆነ በማወቅ፣ መሪ የነበረውን ሰው በማስወገድ ውስጥ እጁን ማስገባት አልፈለገም:: ያ የእግዚአብሔር ሥራ ነበር (1ኛ ሳሙ. 24:3-13፣26:7-11):: ራሳችንን አመራር ላይ ለማውጣት ወይም ሌሎችን ከሥልጣን ለማውረድ ስንታገል ቤተ ክርስቲያን ከፋኛ ትጐዳለች:: ይህ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ዝቅተኝነት የሚያሳይ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም::

ከልባችን በእግዚአብሔር ካመንን፣ በሌላ ሰው እንዲተካን ልንፈቅድለት ይገባል:: በ2ኛ ሳሙኤል 15:25 ላይ የዳዊት ልጅ ስለሆነው አቤሴሎም ዐመፅ እናነብባለን:: ዳዊት ሁኔታውን በሥልጣን ለመቆየት አልተጠቀመበትም:: ይልቁንም፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ብቻ በአመራር ላይ እንዲያቆየው በእግዚአብሔር እንዴት እንደ ታመነ እናነብባለን:: ዳዊት



እንዳለው፣ «. . . በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፣ እርሱ እኔንም መልሶ ታቦቱንና ማደሪያውን እንደገና ለማየት ያበቃኛል፤ ነገር ግን እርሱ፣ 'ባንተ አልተደሰትሁም' የሚል ከሆነ፣ መልካም መስሎ የታየውን ነገር ያድርግብኝ፣ እኔም ለመቀበል ዝግጁ ነኝ::» (2ኛ ሳሙ. 15:25 እና 26)::

መ) ሰዎች ስለ እኛ <u>ስለሚያወሩት ነገር ልንፈራ አይገባም፣ ደግመው ቢመርጡንም ባይመርጡንም ልንፈራ አይገባም:: ሊያሳስበን የሚገባው እግዚአብሔር ስለ እኛ አመራር የሚለው ነገር ነው</u> (ገላ. 1:10፤ 1ኛ ቆሮ. 4:1-5):: እግዚአብሔር ለመሪነት ከጠራን በኋላ፣ ስለ አመራራችን በኃላፊነት ይጠይቀናል:: እግዚአብሔር ስለሚያስበው ነገር ከመጨነቅ ይልቅ ሕዝቡ ስለሚያስበው ነገር አብልጠን የምንጨነቅ ከሆነ፣ ወይም ሰዎች ደግመው አይመርጡንም በሚል ፍርሃት ሰዎች ከእግዚአብሔር መንገድ እንዲያርቁን የምንፈቅድ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆናችን ቀርቶ የሰው ባሪያ ሆንን ማለት ነው:: ሰዎችን ለማስደሰት ስንል አመራራችንን ከቀየርን፣ እግዚአብሔርን እያገለገልን አይደለም ማለት ነው:: እርግጥ ነው፣ ሰዎችን መስማት አለብን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጥር ሳንወጣ፣ መልካምን ልናደርግላቸው ይገባል:: ነገር ግን ሁልጊዜ በመጀመሪያ የሚያሳስበን ነገር እግዚአብሔርንና ቃሉን መታዘዝ መሆን አለበት:: መሪዎች «በመሆን ላይ ያለው ነገር እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ነገር ግን በዚህ መንገድ ካላደረግነው፣ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን ይለቅቃሉ» ሲሉ ሰምቻለሁ:: እንዲህ ስንል ወይም ስናስብ፣ ዋናውና አስፈላጊው ነገር የሕዝቡ አስተያየት እንጂ የእግዚአብሔር አይደለም ማለታችን ነው::

መሪነት የእግዚአብሔር ሥራ እንጂ የእኛ አለመሆኑን ስንረዳ መሪዎች ከፍተኛ ነጻነት ይሰማቸዋል! በአመራር ላይ ባሉ ሌሎች ሰዎች ያለው ቅናት ይጠፋል:: የበቴ ክርስቲያን መሪ ለመሆን ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ለመቆየት የሚደረገው ትግል

ይጠፋል። የሕዝቡን አስተያየት መፍራት ይጠፋል። ይህ ነጻነት አላችሁን?

> 4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህን ሁኔታዎች አብራራ። 1) አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ለመመረጥ ሲሞክር ያለውን ሁኔታ፤ 2) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዳግም ሳይመረጥ ቀርቶ ከመሪነቱ እንዳይነሣ የሚያደርገውን ጥረት፤ 3) የቤተ ክርስቲያን መሪ በአመራሩ፣ በጸሎቱና በስብከቱ ላይ የሕዝቡ ፍላጐት ተጽዕኖ እንዲያመጣ ሲፈቅድ፤ 4) ሽማግሌዎች ሰዎች የሚሉትን በመፍራት ትክክል ነው ብለው የሚያምኑትንና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሲቀይሩ፤ ለ) በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ መሪው የሚሰጠው ምላሽ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመራና እንደሚያገለግል ስለ ማመን አለማመኑ ምን ይነግረናል?

መሪ ለመሆን ግፊት ማድረግ እንዳለብን ወይም በቤተ ክርስቲያን ያለንን የአመራር ቦታ ላለማስነካት መታገል እንዳለብን የምናስብ ከሆነ፣ ስለ አመራር ያለን ግንዛቤ ልክ እንደ ዓለማውያን ነው ማለት ነው። እየመራን ያለነው ስራሳችን ክብርና ጥቅም ነው። ወይም እያልን ያለነው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ጥሩ መሪ ይመርጣል ብለን እናምንም። እኛ ያንን ልናደርግለት ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሪ ለመሆን የሚይዙትን የራሳቸውን መንገድ ንስሐ ሊገቡበት ያስፈልጋል። ራሳችንን በጥንቃቄ ልንመረምርና ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ልንሰጥ፣ እርሱ ከፈለገ ለአመራር እንዲያስነሣን ልንጸልይ፣ ወይም እርሱ ከፈለገ ከመሪነት እንዲያነሣን ልንጠይቅ ይገባል። እናም በአመራር ላይ እስካለን ድረስ፣ እግዚአብሔር ራሱ ለመሪነት እንደ መረጠንና ለበጎቹ ስለምንወስደው ጥንቃቄም በኃላፊነት እንደሚጠይቀን በመረዳት ልናገለግለው ይገባል። በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ አለህን? እግዚአብሔር በዚያ እንዳስቀመጥህ ትረዳለህ? «የተመረጥከው» በእርሱ ሲሆን፣ በአገልግሎት ውስጥ የተቀመጥከው ለዓላማ ነው።

## 2. ጥሪ እግዚአብሔር እንድናገለግለው የሚሰጠው ትእዛዝ



ነው። ስለ እግዚአብሔር የሚመጣው ትእዛዝ መጋቢ፣ አስተማሪ፣ ወንጌላዊ ወይም ሽማግሌ በመሆን ማገልገል ነው። በልባችን ይታወቀናል፣ በዚያ መንገድ ካላገለገልን፣ እግዚአብሔርን እንዳልታዘዝን እንረዳለን። ጳውሎስ ስለ ጥሪው ሲገልጥ፣ «ወንጌልን ባልሰብክ ግን ወዮልኝ» (1ኛ ቆሮ. 9:16) ብሎ ነው። ስለዚህ ጓደኞቻችንና ቤተሰቦቻችን የተሻለ ሥራ እንድናገኝ ቢፈልጉም እንኳ፣ ወይም የተሻሉ ሥራዎችን የማግኘት ዕድል ቢመጣልንም፣ እግዚአብሔር እናገለግለው ዘንድ ከባድ ሸክም በልባችን ስላስቀመጠ እግዚአብሔር በተለየ መንገድ እንድናገለግለው እንደሚፈልግ እናውቃለን። ስለዚህ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና የሚፈልገውን ለመሥራት ለሥጋችን መልካም የሆኑ ነገሮችን እምቢ እንላለን። አገልግሎት ምናልባትም የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ወይም ሚስዮናዊ ሆኖ ማገልገል፣ ወይም ስለ ኢየሱስ ሰምተው ለማያውቁ ሰዎች ወንጌልን ማድረስ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም በሽምግልና ወይም በቤተ ክርስቲያን መጋቢነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት ማገልገል ሊሆን ይችላል፤ ያንን ስናደርግ የምንፈልገውን ያህል ከቤተሰባችን ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ላይኖረን ወይም ለራሳችን ሕይወት ባወጣነው ዕቅድ መሄድ ያቅተን ይሆናል።

እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ዕቅድ እስኪቀየር ድረስ፣ እንድናገለግለው የሰጠንን ትእዛዝ በእርሱ ቦታ ሆነን ልንፈጽም ይገባል። እግዚአብሔር በግልጽ ሌላ ሥራ እንድንሠራ ካልተናገረን በስተቀር በሌሎች ምክንያቶች አገልግሎቱን ከተውን፣ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ መንገድ መርጠናል ማለት ነው። ወይም የምናገለግለው ከእግዚአብሔር በመጣ ጥሪ ሳይሆን፣ ያንን አገልግሎት የመረጥነው ለራሳችን ምቾት እንደ ነበርና አሁን ደግሞ ሌላ ነገር ማድረግ እንደ ፈለግን ነው የሚያሳየው።

> 5ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች ከእግዚአብሔር «ጥሪ» ስላላቸው ያንን ጥሪ ለመፈጸም ሲሉ የሆነ አገልግሎትን ሲመርጡ እንዴት እንዳየህ ግለጥ። ለ) የተሻለ የሥራ ዕድል ሲመጣ አገልግሎቱን የተወ ሰው እንዴት እንዳየህ

ግለጥ። ያንን ሰው እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ እንዲሆን ስለ መጥራቱ ሁኔታ ይህ ምን ያሳየናል? ሐ) የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በእርሱ ቦታ ሆነው እንዲሠሩለት «ስለ መጠራታቸው» ማወቃቸው በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

3. <u>ከእግዚአብሔር የሚመጣ ጥሪ ለተለየ አገልግሎት እንጂ በጥቅሉ ለማገልገል አይደለም</u>። እግዚአብሔር ማናቸውንም ዓይነት አገልግሎቶች እንዲያገለግል ሰውን አይጠራም። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር አንድን ሰው የሚጠራው በተለየ መንገድ እንዲያገለግለው ነው። እግዚአብሔር አንድን ሰው ለተለየ አገልግሎት ለማዘጋጀት የሰውየውን ልምድ ይጠቀማል። እግዚአብሔር የሰውየውን ቤተሰባዊ መሠረት፣ የትምህርት ደረጃውንና የሥራ ልምዱን ይጠቀማል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ሊረዳው የሚችለውን የተለየ የጸጋ ስጦታ ይሰጠዋል። እናም እግዚአብሔር ሰውየው ሊያገለግልበት የሚገባውን የአገልግሎት ደረጃ ይወስናል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይሁን፣ በአውራጃ ደረጃ ይሁን፣ በዞን ደረጃ ይሁን፣ ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወስነው እርሱ ነው።

በሕይወቱ ዘመን ሁሉ፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በማድረግ ላይ ያለው እግዚአብሔር እንዲያደርገው የሚፈልገውን መሆን አለመሆኑን መመርመር አለበት። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ አገልግሎት እንዲንቀሳቀስ ብትጠይቀው፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን በጸሎት መጠየቅ አለበት። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከተናገረው ነገር ወደ ተለየ ሌላ አገልግሎት እንዲቀየር ከተጠየቀ፣ እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንጂ የግል ጥቅም ፍለጋ ለመሄድ አለመፈለጉን ለማረጋገጥ ሲል የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ አለበት። የእግዚአብሔር ጥሪና ሹመት በሰውየው የሕይወት ዘመን ሊለዋወጥ ይችላል። ነገር ግን በእያንዳንዱ እርምጃ ላይ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ እግዚአብሔርን ለመስማት



መወሰን አለበት። ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መታዘዝ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በቀዳሚ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሚሾምበት መንገድ ያ ከሆነና፣ ለዚያ አገልግሎት የእግዚአብሔር ጥሪ እንደሌለው ከተሰማው፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አያገለግልም። ከ«ተጠራ» አገልጋይነት ይልቅ (ከየትኛውም የቢሮ ሠራተኛ የማይበልጥ ወይም የሚያንስ) «ቅጥር» ሠራተኛ ይሆናል።

4. <u>ጥሪው ከእግዚአብሔር ስለሚመጣ፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጥሪ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት</u>። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ልክ እንደ መንግሥት ሠራተኞች «ተቀጣሪ» አይደሉም። መንግሥት ደመወዝ ስለሚከፍልና የሰውየው ተጠሪነት ለመንግሥት በመሆኑ እንደ ፈለገ ሊያደርጋቸው ይችላል። የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ግን ጥሪውን ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ይታመናል። ያንን ጥሪ ለማሳካት ከሽማግሌዎች ጋር ይሠራል። ነገር ግን የትኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ ሰው ከጥሪው ውጪ የሆነ ነገር እንዲያደርግ የማስገደድ መብት የለውም። ለተለየ አገልግሎት እንደ ተጠራ ሰው እንጂ እንደ ተቀጣሪ መታየት የለበትም።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ስለሚይዙበት መንገድ መጠንቀቅ አለባቸው። እያንዳንዱ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተለየ ጥሪ ካለው፣ ቤተ ክርስቲያን ያንን ጥሪ የመረዳትና ሰውየውን በዚያ ስፍራ እንዲያገለግል የማድረግ ኃላፊነት አለባት። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከተጠሩበት ዓላማ ውጪ እንዲያገለግሉ ማድረግ ጥሪውንና የተለየ ጸጋ ከሰጣቸው እግዚአብሔር ጋር መጋፋት ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ልክ እንደ «ቅጥር» ሠራተኞች ተመልክተው ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚነግሯቸው ከሆነና ለጥሪአቸው ግድ ከሌላቸው፣ እግዚአብሔርን እየታዘዙ አይደለም

ማለት ነው፣ ብዙም ሳይቆይ መንፈሳዊ ሕይወታቸውና እግዚአብሔርን ለማገልገል ያላቸው ፍላጐት ይደርቃል:: የሚያገለግሉትም ሥራቸውን እንዳያጡ በመሥጋት ይሆናል:: ስለዚህ በተቻላቸው መጠን ትንሽ ሥራ ብቻ ለመሥራት ይሞክራሉ:: ቤተ ክርስቲያንም ትጐዳለች:: የወንጌል ስጦታ ያለውን ሰው አስተዳዳሪ ስናደርገው ምን እንደሚፈጠር ሁላችንም ተመልክተናል:: ሰውየው ስኬታማ ወንጌላዊ ነው ማለት እግዚአብሔር ስኬታማ አስተዳዳሪ እንዲሆን ጠርቶታል ማለት አይደለም:: በወንጌላዊነት የተቀባው ሰው በሚችለው ሁሉ ለማስተዳደር ቢጥርም፣ ስጦታው ስለሌለው ቤተ ክርስቲያን እንደ ልቧ አትሠራም::

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ:- ሀ) በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው እግዚአብሔር እንዲያደርግ ያልጠራውን ነገር እንዲሠራ በመጠየቁ ምን ያክል ሲሠቃይ እንዳየህ ግለጥ:: ለ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እግዚአብሔር እንዲያገለግል ከጠራው ውጪ እንዲያገለግል በመደረጉ ምን ያክል ቤተ ክርስቲያን እንደ ተሠቃየች ግለጥ:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አገልጋዮችን የሚመለከቷቸው እንደ ቤተ ክርስቲያን ተቀጣሪ ሳይሆን እግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት እንደ ጠራው ቢሆን ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚኖራቸው አመለካከት እንዴት ይቀየራል? |

5) <u>የእግዚአብሔር ጥሪ ዓለም ስኬትን በሚረዳበት መንገድ ስኬትን አያመጣም::</u> ወዲያውኑ ፍሬ ባናይም፣ እግዚአብሔር እድርጉ ላለን ነገር ታማኝ መሆን አለብን:: ከላይ ባሉት ጥቅሶች ላይ እንዳየነው፣ እግዚአብሔር ኢሳይያስን፣ ሕዝቅኤልንና ጳውሎስን ለራሳቸው አገልግሎት ጠራቸው:: ነገር ግን ዓለም ስኬትን በሚረዳበት መንገድ ስኬታማ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ተስፋ አልሰጣቸውም:: ለኢሳይያስና ለሕዝቅኤል ማንም እንደማይሰማቸው ነግሯቸዋል:: ለጳውሎስ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ብዙ ሥቃይ እንደሚደርስበት ተናግሮታል:: እነዚህ መሪዎች በጣም አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ሲያልፍ እንዴት ማገልገል ቻሉ? የእግዚአብሔር ጥሪ ስላላቸው ነው:: ሰዎች ሰምተው ምላሽ ቢሰጡ



ባይሰጡ ወይም ስኬታማ ባይመስሉና ማንም ሳይድን ቢቀር፣ እግዚአብሔር ለሰጣቸው ተግባር ታማኝ መሆን ነበረባቸው::

6) <u>የእግዚአብሔር ጥሪ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ማገልገላቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችላቸው ዋነኛ ነገር ነው</u>:: የቤተ ክርስቲያን መሪነት ሰዎች ሁሉ በአመራራችኘ ደስ ቢሰኙም እንኳን ሁልጊዜ የስኬት ዘመንን አያመጣም:: እኛ የምንታገልበትና ሰዎችም በአገልግሎታችን ደስተኞች የማይሆኑበት ጊዜ ይኖራል:: ግን በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንድንቀጥል የሚያደርገን ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለሥራው እንደ መረጠን መረዳታችን መሆን አለበት:: ለዚያ ነው በሐዋ. ሥራ 20:28 ላይ ጳውሎስ ለሽማግሌዎች ሽማግሌዎች እንዲሆኑ የመረጣቸው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ የተናገረው:: የሾመቻቸው ቤተ ክርስቲያን አይደለችም:: መንፈስ ቅዱስ ሽማግሌዎች እንዲሆኑ ከጠራቸው፣ በመከራ ቀናትም ይረዳቸዋል:: ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ጥሪ በመከራ ጊዜ እንድንጠነክር ያደርገናል:: በሕይወታችን የሚመጣ የመከራ ነፋስ እንዳያሸንፈን የሚያደርግ እንደ ጠንካራ ካስማ ያለ ነው::

7. <u>ከእግዚአብሔር የሆነ ጥሪ ለመረዳት በሕዝቡ ከመመረጥ ጋር ወይም ሥልጠና ስላገኘን ከማገልገል ጋር ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ተካፋይ ከመሆን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም</u>:: በዘመናችን፣ ብዙዎች ለአገልግሎት ካላቸው ጥሪ የተነሣ እግዚአብሔርን የማገልገል ጥሪአቸው የጠፋ ነው የሚመስለው:: ሰዎች ወንጌላዊ የሚሆኑት ለእነርሱ ሥራ ስለሆነ ነው:: ደመወዙ ጥሩ እስከ ሆነ ድረስ፣ ያገለግላሉ:: ነገር ግን ደመወዙ ጥሩ ሳይሆን ሲቀር፣ ወይም ደመወዝ ሲቋረጥ አገልግሎቱን አቁመው ወደ ቤት ይመለሳሉ:: ነገር ግን ጳውሎስ «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ» (1ኛ ቆሮ. 9:16) እንዳለው ዓይነት ጥሪ ቢኖርባቸው እንዲህ አያደርጉም:: ብዙዎች ከእግዚአብሔር ጥሪ እንዳላቸው ይናገራሉ:: ነገር ግን የተሻለ የትምህርት ዕድል

ሲመጣ፣ ወይም ወደ አሜሪካ እንዲሄዱ የዲቪ ሎተሪ ሲደርሳቸው፣ ወይም የተሻለ ክፍያ የሚከፍል መንግሥታዊ ያልሆነ (መያድ) ድርጅት ሲያጋጥማቸው፣ አገልግሎታቸውን ይተውዋሉ። ምናልባትም በጣም ጥቂት የሚባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ባለፉት ትውልዶች ውስጥ የነበሩ ያልተማሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የነበራቸውን ኃይልና ሥልጣን መለማመድ የቻሉበት ምክንያት የእግዚአብሔር ጥሪ ወይም ሸክም ኖሮን ስለማናገለግል ነው።

የአገልግሎት ጥሪ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚገልጸውን በዘመናችን ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ፊት የተጋረጠውን ችግር የሚገልጡትን ቀጣይ ምሳሌዎች መርምር፡-

1. በቤተ ክርስቲያን ተቀምጠሃል እንበል፣ ድንገት አንድ ሰው እጁን አውጥቶ የአንተን ስም ለምርጫ ይጠቁማል። በጣም ጥሩ የትምህርት ደረጃና ጥሩ የመንግሥት ሥራ ስላለህ ለመሪነት ተመረጥክ። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትህ የእግዚእብሔርን ሕዝብ ለመንከባከብ የሚያስፈልገው «የእረኛ ልብ» እንዳለህ አላሳየህም። ሽማግሌ ለመሆን አልጸለይክም፣ መሪ ለመሆንም ምንም ዓይነት ሸክም የለህም። ማንም አንተ መሪ ለመሆን የሚያበቃህን መስፈርት ማሟላት አለማሟላትህን አልጠየቀም። ነገር ግን ለመሪነት ተመረጥክ። ይህ መሪ ለመሆን ከእግዚእብሔር የመጣ ጥሪ አይደለም። የእግዚአብሔርን ድምፅ ሳትሰማ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ መምራት ትችላለህ? የማይመስል ነው።

2. በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሠራተኛ እንፈልጋለን። አንድ ጥሩ ተሰጥኦ ያለውና ትምህርቱን መቀጠል ያልቻለ ወጣት አገኘን፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ላክነው። ከተመረቀ በኋላ፣ ወደ እኛ ሲመለስ በቤተ ክርስቲያናችን እንዲያገለግል ጠየቅነው። ይህ የመሪነት ጥሪ አይደለም። ትምህርት የእግዚአብሔርን ጥሪ በሕይወታችን ላይ አያመጣም። ጥሪ የሌላቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ከመሥራታቸው በፊት የሚያነሡት ጥያቄ አለ። ዛሬ



ዛሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በከፍተኛ ደረጃ የተመረቁ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉ ሲጠየቁ፣ «ስንት ነው የምትከፍሉኝ?» የሚል ምላሽ እንደሚሰጡ እየተነገረ ነው። ወይም «ክፍያው በቂ ካልሆነ ማንም ሰው ወንጌላዊ አይሆንም» ሲባል እንሰማለን፤ «ደመወዙን ከጨመርን ሰዎች ወንጌላዊ ሆነው ይሠራሉ። ከዚያ የተነሣ፣ የምናገኛቸው ወንጌላውያን ጥሩ ክፍያ ስላለ የሚያገለግሉትን ይሆናል። የእግዚአብሔር ጥሪ ከሰውየው ደመወዝ አይመነጭም። እንደዚያ ያለ አመለካከት ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 2:17 ላይ እንዳስጠነቀቀው ዓይነት ወንጌልን በገንዘብ የምንሸቃቅጥ ሰዎች ያደርገናል። ጥቅማችን እንዲጨምር የምናደርገው ነገር ሁሉ ወንጌልን የመሸቃቀጥ መንገድ ነው። አንድ ሰው አንድ ጊዜ፣ «ለምንድን ነው ሁልጊዜ መጋቢዎች ወደ ትልልቅ ቤተ ክርስቲያናት እንዲያገለግሉ ጥሪ የሚመጣባቸው?» ብሎ ጠየቀ። እግዚአብሔር አንዳንዴ ሰዎችን ራቅ ወዳለ ቦታዎች አይጠራም እንዴ? ያ የሆነው ከእግዚአብሔር ጥሪ በመነሣት ስለማናገለግልና እግዚአብሔርን የምናገለግለው እስከተጠቀምን ድረስ ይሆን? በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ማገልገል ልክ እንደ ሥራ ሆነ እንዴ እናም በመንግሥት መሥሪያ ቤት እንዳለው ዓይነት የሥራ ደረጃ እድገት እንድናገኝ እንጠብቃለን እንዴ?

3. የአውራጃዋ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንደ መሆናችን፣ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በእግር በመጓዝ ወይም አውቶብስ በመያዝ ይሆናል ወደ ወርሐዊ ስብሰባ የምንሄደው። ከዚያ፣ «ወደ ሽማግሌዎች ስብሰባ የማደርገው ረጅም ጉዞ ነው። የሆነ የማገኘው ጥቅም ከሌለ፣ ለምንድን ነው ያንን ሁሉ መንገድ የምጓዘው? እዚያ ለመድረስ ዋጋ ስለ ከፈልኩኝና አስፈላጊ መሪም ስለ ሆንኩኝ፣ ቢያንስ ጥሩ ምግብ (ማለትም፣ ሥጋ) ሊያቀርቡልኝ ይገባል። የትራንስፖርት ወጪዎቼን እስካልሸፈኑልኝ ድረስ ለምንድን ነው ከግል ገንዘቤ የምከፍለው? ቤተ ክርስቲያን መክፈል ይኖርባታል።» ብለን ማሰብ እንጀምራለን። ስለዚህ ለምናገኛቸው ጥቂት ጥቅማ

ጥቅሞች «ጥሩ ምግብ»፣ ወይም በኢኮኖሚ እስካልተጐዳን ድረስ ብቻ ማገልገል እንጀምራለን:: ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት አብዛኛውን የመባ ገንዘብ የሚያውሉት በሽማግሌዎች ላይ፣ ማለትም በሰብሰባቸው ላይ ስለሚሆን፣ ገንዘቡ ወንጌልን ለማስፋፋት ሳይውል ያቀራል:: ጥሪው የት ደረሰ? 'ይህ እግዚአብሔር ከእኔ የሚፈልገው ነው:: ጥቅም ባገኝበትም ባላገኝበትም፣ ከራሴ ገንዘብ መክፈል ቢኖርብኝም ባይኖርብኝም አገለግለዋለሁ' የሚለው ስሜት የት ደረሰ? ይልቁንም አመለካከታችን፣ «እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት ከጠራኝ፣ ለእርሱ ካለኝ ፍቅር የተነሣ አደርገዋለሁ:: ምግቡ ጥሩ ቢሆንም ባይሆንም፣ ወይም ምግብ ቢኖርም ባይኖርም፣ ወጪዎቼን ቢመልሱልኝም ባይመልሱልኝም እንኳ፣ ችግር የለም:: እንዲያውም፣ እነዚህን ጥቅሞች ማግኘቴ ሰዎች እኔን እና ለአገልግሎት ያለኝን ተነሣሽነት እንዲጠራጠሩ የሚያደርጋቸው ከሆነ፣ ወይም የወንጌልን መስፋፋት የሚገድብ ከሆነ፣ ጥቅሙ ይቅርብኝ» ማለት መቻል አለብን::

ጳውሎስ እግዚአብሔር ስለ ሰጠው «ጥሪ» የሚናገረውን በዚህ ዘመን እኛ ስለ አመራር ካለን አስተሳሰብ ጋር እነጻጽር:: በ1ኛ ቆሮ. 9:15-18 ላይ ጳውሎስ ወንጌልን የሚሰብከው በምርጫው ሳይሆን በመታዘዙ እንደ ሆነ ይናገራል:: በአገልግሎቱ የሚገኝ ጥቅምን እምቢ ብሏል:: ሰው ጳውሎስ የሚያገለግለው ጥሩ ገንዘብ ለማግኘ ትና ከማንም የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው ብሎ እንዲያስብ ጨርሶ አይፈልግም:: ይህ ነገር በጣም ስለሚያሳስበው ደመወዝ እንኳን አይቀበልም ነበር::

በሚገርም ሁኔታ፣ በአሁኑ ወቅት፣ በዓለማችን ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተሰይም የሚከፈላቸው ወንጌላውያንና መጋቢዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ሀብታም» ሆነዋል:: ከአብዛኛ ዎቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የተሻለ ደመወዝ አላቸው:: እነዚህ አባላት ወደ መሪያቸው ሲመለከቱ የሚያታቸው የተሻሉ ቤቶች፣



ጥሩ ጥሩ ልብሶች፣ ወዘተ. . . ናቸው:: «የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን እንዴት ጥሩ ነገር ነው:: ከእኛ ገንዘብ ምን እንዳገኙ ተመልከቱ!» ብለው ያስባሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪውም፣ «ታማኝ በመሆኔ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ባረከኝ ተመልከቱ» ይላል:: ነገር ግን ይህ የኢኮኖሚ አለመመጣጠን ቅናትን እየፈጠረ ሰዎች ስአገልግሎት ያለንን ተነሣሽነት እንዲጠራጠሩ ያደርጋል:: ምናልባት «በረከቱ» ከሰይጣን፣ ወይም አገልግሎትን በተሳሳተ መንገድ ከመረዳት፣ እና እግዚአብሔርን በ«ጥሪ» የማገልገልን ንጽሕና የሚደመስስ ይሆናል!

ለአገልግሎት ወይም ለመሪነት ከእግዚአብሔር የሚመጣ ጥሪ በእግዚአብሔር መንገድ የመምራት መሠረት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታላላቅ መሪዎች ሁሉ መምራት የቻሉት እግዚአብሔር ስአገልግሎት እንደ ጠራቸው በማወቃቸው ነው:: እንዲያውም፣ የመሪነትን ቦታ ስመያዝ በጣም የሚያንገራግሩ ነበሩ:: ሙሴ እግዚአብሔር ሌላ ሰውን እንዲልክ ለምኗል (ዘጸአ. 4:13):: ኤርምያስም ለእግዚአብሔር ገና ልጅ እንደ ሆነ ተናግሯል:: አንድ ቀንም የነቢይነት ሥራውን ለማቆም ሲሞክር የእግዚአብሔር ቃል በልቡ ሲነድበት መናገር ጀመረ (ኤር. 20:7-9):: ስተጠሩት ለእነዚህ አገልጋዮች ደመወዝ ጉዳያቸው አልነበረም:: ይልቁንም፣ ለእነርሱና ለሕዝቡ አስፈላጊው ነገር በእግዚአብሔር ለመሥራታቸው ማረጋገጫ ማግኘት ነበር:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል ርቀናል!

ማጠቃለያ:- መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ መሪ እንዲሆን ሰውን የሚመርጠው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራል:: ሰውየው ሥራውን ስለ ፈለገ ወይም ቤተ ክርስቲያን ሰውየው በሽምግልና ወይም በመጋቢነት እንዲያገለግል ስለ ጠራቸው አይደለም ሽማግሌ ወይም መጋቢ የሆነው:: መሪነት በቀዳሚነት በሰውየው ወይም ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያን ምርጫ የሚታይ መሆን የለበትም:: እግዚአብሔር በሰውየው ሕይወት ያለውን ጥሪ ለማረጋገጥ ቤተ

ክርስቲያንን ሊጠቀም ይችላል። ነገር ግን ጥሪው የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው። ምንም ዓይነት የትምህርት ደረጃ ወይም ደመወዝ የእግዚአብሔርን «ጥሪ» አያመጣም። በእርግጥ ትምህርትና ገንዘብ ላይ ካተኮረን፣ አብዛኛውን ጊዜ ጥሪ እንደሌለን፣ ወይም ቢያንስ ጥሪያችንን እንደ ረሳን ይገልጣል።

እግዚአብሔር መሪ እንድንሆን ካልጠራን፣ መሪ ለመሆን ማንገራገር ይኖርብናል። መሪ መሆን የማይፈልግ ሰው መሪ ሲሆን ጥሩ መሪ አይወጣውም። ያልተጠራ መሪ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። በጣም ትንሽ በመሥራት ወይም በዓለማውያን ኃይልና መንገድ ይመራል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ልክ እንደ ኤርምያስ በቀጥታ ነው ለመሪነት የሚጠራን። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ጥሪው በተዘዋዋሪ ነው የሚደርሰን። የሚጠራን በልባችን ለሰዎች ሸክም በመስጠት ነው። ለእነርሱ መዳንና ማደግ ካለን ሸክም ውጪ፣ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ማገልገል አንችልም።

መሪ መሆን የሚፈልገን ሰው ተጠንቀቅ። ብዙ ጊዜ ሰዎች መሪ መሆን የሚፈልጉት በመሪነት ውስጥ የሆነ ነገር ስላለ ነው። ያም መንፈሳዊነት አይደለም። አንድ መሪ ሲናገር፣ «እውነተኛና ጥሩ መሪ የመምራት ፍላጐት የሌለው፣ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ግፊትና በውጫዊ ሁኔታዎች ተገፋፍቶ የመሪነትን ቦታ የሚይዝ ሰው ነው» ብሏል። መሪ እንዲሆን ከመመረጡ በፊት በንቃት ያላገለገለ ሰውን ይጠራጠሩ። ሽማግሌና መጋቢ የሚለው የማዕረግ ስም የምናገለግልበትን መንገድ ሲሰውጠው አይገባም። ይልቁንም፣ በአመራር ውስጥ ከመሳተፋችን በፊት ሰዎች እንዲያድጉ ራሳችንን ልንሰጥ ይገባል። መሪ ሆኖ መመረጥ አንድን ሰው መንፈሳዊ መሪ አያደርገውም። ይልቁንም፣ ለመሪነት መመረጣችን እግዚአብሔርና ሕዝቡን ሰዎች እረኛቸው እንደ ሆንንና መንፈሳዊ ፍላጐታቸውን እንደምናሟላ በማወቅ ለእኛ ክብርና እውቅና የሚሰጡበት መሆን አለበት።



7ኛ ጥያቄ፡- 1) ሀ) እግዚአብሔር እንዴት ወደ አገልግሎት እንደ ጠራህ ግለጥ። ለ) ምን ዓይነት አገልግሎት ነው በልብህ ያስቀመጠው? ሐ) ራስህን ለዚያ አገልግሎት እንዴት ነው የምታዘጋጀው? መ) እንዴት ነው በአሁኑ ወቅት በዚያ አገልግሎት ውስጥ የምትሳተፈው? 2) ሀ) በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ስላየሃቸው መሪዎች ወይም ያለ እግዚአብሔር ጥሪ ስለሚያገለግሉ ሰዎች ግለጥ። ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ችግር ያስከትላል? ሐ) በአንድ ሰው አገልግሎት ውስጥ የአገልግሎት ወይም የመሪነት ጥሪ ምን ዓይነት ልዩነት ያመጣል?

## 2. ፍጹም የሆነ ታዛዥነት፡- የሚያስከፍለው ዋጋ ምንም ይሁን ምን የመሪነትን መስቀል መሸከም።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዘፍጥ. 12:1 እና 4ን አንብብ። 1) እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነበር? 2) ለአብራም ይህንን ትእዛዝ መቀበል አስቸጋሪ የሆነው ለምንድን ነበር? 3) ከመታዘዙ የተነሣ አብራምና ዓለም የሚያገኟቸውን አንዳንድ በረከቶች ዘርዝር። ለ) ሕዝ. 24:15-18ን አንብብ። 1) እግዚአብሔር ሕዝቅኤል እንዲያደርግ ያዘዘው ምንድን ነበር? 2) ለምን ነበር ይህ ለመታዘዝ አስቸጋሪ የሆነው? ሐ) ኤር. 16:1-2ን አንብብ። 1) እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነበር? 2) ለምንድን ነበር ይህ ትእዛዝ ለመፈጸም አስቸጋሪ የሆነው?

አብዛኛዎቻችን ብዙ ዋጋ ካላስከፈለን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ነን። እግዚአብሔር እንድናደርግ ባዘዘን ነገር ውስጥ በቂ ጥቅም ካየን፣ ለመታዘዝ ፈቃደኞች ነን። ነገር ግን ጥቅም የሌለው ከሆነ፣ አብዛኛውን ጊዜ አንታዘዝም። ለምሳሌ፣ አንዳንዱ «ለሰዎች ጥሩ ክፍያ ካልከፈልን በስተቀር፣ ሰዎች ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ሆነው የቤተ ክርስቲያን ሥራ አይሠሩልንም። ሰዎች ወደ አገልግሎት ይሳቡ ዘንድ ጥሩ ክፍያ መክፈል አለብን።» ሲባል እንሰማለን። ያ ማለት እግዚአብሔርን በማገልገል የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ከቀነስን፣ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ካልገቡ የሚከፈለው ዋጋ ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔር ሥራ ይበለጽጋል ማለት ነው። ይህ ፈጽሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አሳብ ነው። እንዲህ ዓይነት አባባሎች

እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሳይሆን በግላቸው ከሚያገኙት ጥቅም የተነሣ የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እሉን ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፣ ወንጌልን መሸቃቀጥ ወይም ወንጌልን ለግል ጥቅም ማዋል ማለት ነው (2ኛ ቆሮ. 2:17)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት ሁልጊዜ ታላቅ ዋጋን ያስከፍላል። አብርሃም ከመባረኩ በፊት ቤተሰቡን ጥሎ መውጣት ነበረበት። ሕዝቅኤል ሚስቱ በትሞት ማልቀስ እንኳን አልተፈቀደለትም ነበር። ኤርምያስ ማግባት አልተፈቀደለትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ብዙ መከራን በግላቸው ተቀብለዋል። በዚህ ዘመን ላሉ መሪዎችም ልክ እንዲሁ ነው። ራሳችንን ለሌሎች ሰዎች ስለምንሰጥ፣ የምንፈልገውን አብዛኛውን ነገር አናገኝም። አንድ ጸሐፊ ሲናገር፣ «የክርስቶስ መስቀል በእኛ እንዲሠራ በፈቀድነው መጠን (ለክርስቶስ በመታዘዝ ሕይወታችንን ለሌሎች ስንሰጥ ነው የክርስቶስ ትንሣኤ በእኛ የሚገለጠው። መስቀሉን መሸሽ መንፈሳዊ መሪነትን መተው ነው።» ብሏል። በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ያሉት ሰዎች በቂ የግል ጊዜ፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ፣ ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር የሚዝናኑበት ጊዜ የላቸውም። በአንድ ወቅት ጓደኞቻችን የነበሩ ሰዎች እንደ ቀድሞው ወዳጅነታቸው አይሆኑልንም፣ ከዚያ የተነሣ ብቸኞች እንሆናለን፣ ወይም ከእኛ ሕዝቡ የማያውቀውን ውለታ ይጠብቃሉ፣ እኛ ግን እግዚአብሔር እንድንሠራ የጠየቀንን ነገር እንሠራለን። ሰዎች እውነት ባልሆኑ ነገሮች ሲከሱን በሕይወታችን «ጠባሳ» ትቶ ያልፋል፣ ወይም ያሙናል፣ ወይም አመራራችንን ይቋቋማሉ (2ኛ ቆሮ. 4:7-12)። በቀጣይነት ራሳችንን ለሌሎች በመስጠታችን አካላችንና ስሜታችን ይደክማል። ነገሮችን ሞክረን እንዳሰብነው ሳይሆንልን ሲቀር ተስፋ እንቆርጣለን። እኛ ለሌሎች ሰዎች አንድ ነገር ማድረግ እንፈልጋለን፣ ነገር ግን ሰዎቹ በእኛ ላይ ይነሣሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንድናገለግል ስለ



ጠራን፣ ዋጋ መቀበልን ልንማር ይገባል።

ለእኛ ባይመችንም እንኳን እግዚአብሔርን መታዘዝን ካልተማርን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስንሆን በቀዳሚነት እግዚአብሔርኝ የሚያስከብርና ለእርሱ የምንታዘዝበትን ሥራ አንሠራም። ይልቁንም፣ ሁልጊዜ እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቃለን።

ሀ. «ከዚህ አገልግሎት ምን እጠቀማለሁ?» ስለዚህ ጥቅም የማያስገኝ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን እንታዘዝም። የምናስበው ስለ ደመወዛችን፣ የጉዞ ወጪአችንን ማን እንደሚሸፍን፣ ማን መጽሐፍ እንደሚገዛልን፣ በመሪነት ደረጃችን ወደ ላይ ከፍ የምንልበትን መንገድ፣ መቼ ቀጣይ ትምህርታችንን እንደምንቀጥል፣ ወዘተ. . . ይሆናል።

ለ. «በመሪነቴ ሕዝቡን እንዴት ነው የማስደስተው?» ውሳኔያችን ሕዝቡን ከማሳዘን ይልቅ አብዛኛው ሕዝብ የሚቀበለው እንዲሆን እንጥራለን። የምንመራው በቅድሚያ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሳይሆን ሕዝቡን ለማስደሰት ይሆናል።

> 9ኛ ጥያቄ:- ገላ. 1:10ን አንብብ። ጳውሎስ ምን ምርጫ ነበረው? የዘረዘራቸውን እያንዳንዳቸውን ምርጫዎች ወስዶ ቢሆን ምን ይፈጠር ነበር?

የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን አብዛኛውን ጊዜ በአንዳንድ ሰዎች የማይወደዱ ውሳኔዎችን ማስተላለፍን ያካትታል። በእንደዚህ ያሉ ጊዜያት፣ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መሪ አንድ ምርጫ አለው። ምርጫውም ውሳኔው ምንም ያህል አስቸጋሪና ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም፣ እግዚአብሔርን ለመከተልና ለመታዘዝ መቁረጥ፣ ወይም ደግሞ በመጀመሪያ ሰዎችን ለማስደሰት መፈለግ ይሆናል። ለግላችን ባይመቸንም ወይም ውሳኔያችን በብዙ ሰው ተቀባይነት ባያገኝም፣ እግዚአብሔርን መከተልና መታዘዝን ከመረጥን፣ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነን ማለት ነው። ነገር ግን በቅድሚያ ለእኛ የሚመቸንንና ጥሩ የሆነውን ነገር በማድረግ የምንመራ ወይም ጥሩ እንዳልሆነ

እያወቅን ሕዝቡ እንደሚፈልገው ብንመራ፣ እኛ የሰው ባሪያዎች ነን ማለት ነው።

እኛ ወይ የግል ደስታችን ባሪያዎች አለያም የሌሎች ሰዎችና የምኞቶቻቸው ባሪያዎች ነን። የራሳችን ደስታና ምቾት ባሪያዎች መሆን፣ ወይም የሌሎች ሰዎች አመለካከቶችና ፍላጐቶች ባሪያዎች መሆን ቀላሉ መንገድ ሊሆንልን ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንገድ፣ ሰዎች በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ የምንረዳበትን ብቸኛ መንገድ መከተል ከፈለግን፣ በመጀመሪያ ኢየሱስን መታዘዝ መልመድና የእርሱ ባሪያ መሆን አለብን። ከእግዚአብሔር ዘንድ ሽልማትን የምንቀበለው ለእኛ ባይመችም እርሱን ስመታዘዝ ስንወስን ነው።

ሐ. «ኃላፊነቴን ስመወጣት እንዴት አድርጌ ነው በትንሹ ለእኔ በሚመች መንገድ የምሠራው?» ንግዳችን እስካልተጐዳ ድረስ የሽማግሌዎችን ስብሰባ መካፈል እንፈልጋለን፣ ወይም ከሥራችን የዓመት እረፍት ብሰን እንዳንወጣ፣ ወዘተ. . . እንጥራለን። ነገር ግን የሽማግሌዎች ስብሰባና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ካልተመቹን፣ እንቀራለን። እናም እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችንና ኃይላችን ከማገልገል ይልቅ በግማሽ ልብ እናገለግላለን።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሙላት እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ሸሽተው በከፊል ወደ መታዘዝና በከፊል ወደ መሠዋት የሚሄዱባቸውን መንገዶች ግለጥ። ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደዚህ ካለው አመራር ምን ውጤት ይገኛል? ሐ) ሌሎችን ባያስደስትም እንኳን እግዚአብሔርን በሙላት መታዘዝን የመረጥክበትን መንገድ ዘርዝር። መ) የእግዚአብሔር ፍላጐት እንዳልሆነ እያወቅህ ሕይወትህን ቀላል ለማድረግ ወይም የሰዎችን ፍላጐት ስመፈጸም ስትል ውሳኔ የወሰድክባቸውን ጊዜያት ግለጥ። |

በጣም አስገራሚው ነገር ሁኔታው ባይመችም መሪዎች ፍጹም መታዘዝን ለእግዚአብሔር ካሳዩ፣ ሌሎች አባላትም ያንን ማስተዋልና እግዚአብሔርን በሙላት መታዘዝ መጀመራቸው ነው።



እግዚአብሔርን መታዘዝ ከመሪዎች ሕይወት «የምንቀስመው» እንጂ፣ ከምስባክ ላይ «የምንማረው» አይደለም። ኃጢአት ስንሠራ እንኳን፣ መሪዎች ኃጢአታችንን በግልጽ ንስሐ ካስገቡን፣ ሕዝቡ የኃጢአት ስርየትን ይማራል። ከሕዝቡ ያለንን ክብር ከማጣትና ከአገልግሎት ከመባረር ይልቅ፣ ሰዎች እውነተኛ መንፈሳዊ ብስለት በማሳየታችን ይበልጥ ያከብሩናል። ከሁሉ በላይ ግን፣ እግዚአብሔር ደስ ይለኛል፣ ይከብራልም።

## ሁለተኛ ቀን:- ለመንፈሳዊ መሪነት የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 4)

### ስኬታማ ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት:- መሪው ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ግንኙነት የሚመነጩ ባሕሪዎች (ክፍል 2)

እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል እንዲጠቀምብን ካስፈለገ፣ እግዚአብሔር የሚጠቀምብን ዓይነት ሰው መሆን አለብን። አመራራችን በተለያየ የሕይወታችን ክፍል ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት እንደሚነሣ ማረጋገጥ አለብን። በትላንትናው ዕለት እያንዳንዱ አገልጋይና መሪ እግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት እንደ ጠራው ማረጋገጥ እንዳለበት አይተናል። የተጠራንበት አገልግሎት ባይመቸንና ታዋቂነትን ባያመጣልንም፣ በዚያ አገልግሎት እግዚአብሔርን መታዘዝ አለብን። የሚከተሉት ባሕርያት መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የግንኙነት ደረጃ ይገልጣሉ።

### 3. ታማኝነት:- ሰዎች ባያዩንም እንኳን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ሥራ በመሥራት ታማኝ መሆን።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዘፍጥ. 39:1-6ን አንብብ። 1) ዮሴፍ የት ነበረ? እንዴት ነው እዚያ ሊገባ የቻለው? 2) እግዚአብሔር ለዮሴፍ ምን አደረገለት? 3) እግዚአብሔር ዮሴፍን ሊባርክበት የቻለው የዮሴፍ ባሕሪ ምንድን ነበር? ለ) ማቴ. 25:14-28ን አንብብ። 1) ጌታው ለአገልጋዮቹ ሁሉ የሰጣቸው |

ምንድን ነበር? 2) እያንዳንዱ ባሪያ በተሰጠው ነገር ምን አደረገ? 3) ታማኝ የሆኑትን ጌታቸው እንዴት ሸለመ? 4) ጌታው በሰጠው ገንዘብ ታማኝ ያልሆነውን ባሪያ ጌታው ምን አደረገው? 5) ይሄ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ምን ያስተምረናል?

በመሪነት ውስጥ ጥቂት ባሕርያት ከታማኝነት ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው:: ታማኝነት እምነት የሚጣልበት ሰው የመሆን ባሕሪ ነው:: ያ ማለት ሰዎች ምንም ይሁን ምን ለመሥራት የተስማማነውን ነገር እንደምንሠራ ያምናሉ ማለት ነው:: በአንድ በተወሰነ ቦታ በአንድ በተወሰነ ሰዓት እንገኛለን፣ ብለን ከተናገርን፣ ታማኞች ከሆንን ባልነው ቦታና ጊዜ እንገኛለን:: ታማኝነት ማለት አንድን ነገር እናደርጋለን ብለን በተናገርንበት ጊዜ ማድረግ ነው:: ሰዎች ቃላቸውን ይጠብቃሉ ብለው የማያምኑን ከሆነ፣ ሰዎች በአመራራችን ላይ እምነት አይኖራቸውም::

ሀ) <u>ጠቀሜታቸው ያልጐላ አገልግሎቶችን በማገልገል ታማኝ መሆን::</u> የቤተ ክርስቲያን አመራር መሠረት ያደረገው መመሪያ ለትልልቅ ኃላፊነቶች ከመታመናችን በፊት በትንንሽ አገልግሎቶች ላይ ታማኝነትን ማሳየት ነው:: እግዚአብሔር በትንንሽ ነገሮች ላይ ስንታመን የሚሸልመን በታላላቅ የአገልግሎት ዕድሎች ነው:: ይህንን በዮሴፍ ሕይወት ማየት እንችላለን:: እግዚአብሔር ዮሴፍ በባርነት ተሽጦ ጲጥፋራ ቤት እንዲገባ ፈቀደ:: ዮሴፍ ባሪያ በመሆኑ በእግዚአብሔር፣ በቤተሰቡና በሌሎች ላይ ሊማረር ይችል ነበር:: ነገር ግን አልተማረረም:: ልክ እንደ ሌሎቹ ባሪያዎች ሲገደድ ብቻ መሥራት ይችል ነበር:: አለቃው ሲያየው ሲያየው ብቻ ትንሽ ትንሽ ሊሠራ ይችል ነበር:: ነገር ግን አዲስና ትንሹ ባሪያ ሆኖ እያለም እንኳ፣ ጠንክሮ ይሠራ ነበር:: ሆኖም ዮሴፍ እግዚአብሔር እርሱን ለማክበር ታማኝነቱን እንደሚጠቀም አያውቅም ነበር:: «ጠንክሬ ክሠራሁ በሌሎች ባሪያዎች ላይ እሾምና ከባድ ሥራ መሥራቱ ይቀርልኛል» ብሎ አላሰበም:: እርሱ ያሰብ የነበረው ጠንክሮ በመሥራት እግዚአብሔርን ማክበር ነበር::



እግዚአብሔር የዮሴፍን አመለካከትና ታማኝ አገልግሎቱን ባርኮ በጲጥፋራ ቤት ላይ መሪ አድርጎ ሾመው:: ዮሴፍ በአንድ ሰው ቤት ላይ ታማኝ ነበር፣ ነገር ግን በፈጠራ ክስ እስር ቤት ገባ:: በድጋሚ በእግዚአብሔርና በሌሎች ሰዎች ላይ ማማረር ይችል ነበር:: ወይም ልክ እንደ እስረኛ ትንሽ ትንሽ ለመሥራት መወሰን ይችል ነበር:: ነገር ግን ዮሴፍ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ጠብቆ በታማኝነት እስር ቤት ውስጥ አገለገለ፣ ያንን ሲያደርግ እግዚአብሔር ለታላቅ የመሪነት ቦታ ያስነሣኛል ብሎ አልነበረም:: ዳግም፣ እግዚአብሔር ዮሴፍ ታማኝ እንደ ሆነ አይቶ በእስር ቤቱ ላይ በሁለተኛ የአመራር ደረጃ ላይ አስቀመጠው:: ዮሴፍም በእስር ቤት ውስጥ ብዙ ሰዎች አመራሩ ታማኝ ነበረ:: በእነዚህ ሁለት የአመራር ደረጃዎች ላይ የተሰጠውን ኃላፊነት በታማኝነት ስለ ተወጣ እግዚአብሔር በወቅቱ በዓለም ላይ ኃያል በነበረችው አገር ግብጽ ላይ መሪ እንዲሆን አስነሣው:: በፈርዖን ሥር ሆኖ በጠቅላይ ሚኒስትርነት አገለገለ:: እግዚአብሔርን፣ ቤተሰቡንና ግብጽ የምትባለውን አገር በታማኝነት አገለገለ:: የዚያ ምክንያት ከዚያ በፊት በትንንሽ ነገሮች ላይ ታማኝ ስለ ነበረ ነው::

የታማኝነት ባሕሪን የምናሳድገው በመሪነት ከተመረጥን በኋላ አይደለም:: ባሕሪያችን ሊያድግ የሚገባው በመሪነት ከመመረጣችን በፊት ነው:: ያ የሚጀምረው ቤተሰቦቻችን ከብቶችን እንደ መጠበቅ ያሉ ነገሮችን እንድንፈጽም ሲያዝዙን ነው:: የተሰጠንን ሥራ ጥሩ አድርገን ካልሠራን፣ ማንም ባያየንና ቤተሰባችንም ወደ ሜዳ ወጥተን ስላደረግነው ነገር ባያውቁም፣ እግዚአብሔር ግን ወደ ተሻለ የአገልግሎት ደረጃ አያመጣንም:: እግዚአብሔር ሌሎች አማኞች በእምነት እንዲያድጉ እንድንረዳቸው ሲጠይቀን፣ በምንችለው ኃይል አማኙን ደቀ መዝሙር ካላደረግን፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆንን ባሕሪ ሳናሳድግ እንቀራለን:: ወይም ቤተ ክርስቲያንን እንድናጸዳ ስንጠይቅ በፈቃደኝት ጥሩ አድርገን ካጸዳን፣ የታማኝነት ባሕርያችን አድጓል ማለት ነው:: እኛ

ለክርስቶስ ነው። በምንችለው ኃይል ሁሉ በታማኝነት ካልሠራን፣ ኢየሱስን በምንችለው አቅም አላገለገልንም ማለት ነው።

| |
|---|
| 12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሕይወትህ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ በትንንሽ ነገሮች ላይ የመታመን መመሪያ ታላላቅ ኃላፊነቶችን ሲያመጣ እንዴት እንዳየህ ግለጥ። ለ) ሰዎች እንድትሠራቸው የጠየቁህን የተለመዱና አስፈላጊ ነገሮችን ዘርዝር። እነዚህን ነገሮች እንዴት በታማኝነት እንደፈጸምካቸው ግለጥ። ሐ) እግዚአብሔር አሁን እንድታደርጋቸው የጠየቀህ አንዳንድ ነገሮች ምን ምን ናቸው? የተጠየቅኸውን በመፈጸም ረገድ ታማኝነትን እንዴት እያሳየህ እንደ ሆነ ግለጥ። መ) ኢየሱስንና ሌሎችን በምትችለው አቅም ሁሉ በማገልገል ላይ ካልሆንክ፣ ጊዜ ወስደህ ጸልይ። በእነዚያ አገልግሎቶች ላይ በታማኝነት ለማገልገል ራስህን ስጥ። |

አንደ ቤተ ክርስቲያን፣ እግዚአብሔር መሪን ከሚያሳድግበት መንገድ ውጪ አንዳንዴ መጠንቀቅ አለብን። አንድ ወጣት፣ «መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስገቡኝ፣ ስመረቅ፣ የዚህች ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እሆናለሁ» አለ። አንዳንድ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተማሩት እውቀትና የሚሰጣቸው ወረቀት በሕዝብ ፊት ለማገልገል የሚያበቃቸው ይመስላቸዋል። ከትምህርት ቤት ሲመረቁ፣ ከፍተኛ የአመራር ቦታ እንደሚገባቸው ያስባሉ። ካልተቀጠሩ የተሰደቡ፣ ያልተከበሩ፣ ወይም ከፍተኛ የመሪነት ቦታ ያልተሰጣቸው ይመስላቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር፣ «በመጀመሪያ ወንጌላዊነት ሹመትን ከማግኘትህ በፊት በታማኝነት ስለ እኔ መስክረህ አሳየኝ።» ወይም «በመጋቢነት አንተን ከመሾሜ በፊት ሽማግሌዎች በሰማያውቋቸው አማኞች ያለህን መቆርቆር በታማኝነት እነርሱን በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲበስሉ በማድረግ አሳየኝ።» ነው የሚላቸው። የመጋቢ ልብ የሚያድገው በዚያ ነው። ወይም «ማንም ሳይጠይቅህ ቤተ ክርስቲያን አጽዳ፣ መታጠቢያ ቤቶችን አጽዳ፣ ወንበሮችንም አስተካክል። ስለ ቤቴ ግድ ይበልህ። እነዚህ ነገሮች ታላላቅ የመሪነት ኃላፊነቶችን እንደምትወጣ ያሳዩኛል።»



ነው የሚለን።

እግዚአብሔር መሪዎችን የሚያሳድግበትን መንገድ፣ ማለትም ከትልልቅ ኃላፊነት በፊት በትንንሽ አገልግሎት መታመንን ካላከበርን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ጉዳት እናመጣለን። ውጤቱም ሰው ካላያቸው በስተቀር በታማኝነት ማገልገል ምን እንደ ሆነ የማያውቁ ወንጌላውያንና መጋቢዎችን ማፍራት ነው። ስለዚህ፣ ሽማግሌዎች እስካልተገኙና እንዲሠሩ እስካልተነገሯቸው ድረስ በሚችሉት ኃይል ሁሉ አይሠሩም። ለአገልግሎታቸው ታማኝ አይደሉም፣ ነገር ግን ሥራቸውን ላለማጣት ብቻ ትንሽ ትንሽ ይሠራሉ። ወይም የትምህርት ደረጃቸውን ብቻውን የታላቅነትና የስኬት ቁልፍ አድርገው በማሰብ ይኮራሉ። እነርሱ ከደረሱበት የትምህርት ደረጃ ያነሰ የትምህርት ደረጃ ያለውን ሰው ሁሉ በንቀት ነው የሚመለከቱት። ሽማግሌዎች እነርሱ የሚፈልጉትን ነገር ካላደረጉ፣ በኩራት ተነሥተው ቤተ ክርስቲያንን በመክፈል በወጣቶችና በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መካከል መለያየትን ይፈጥራሉ። መሪነት የሚገኘው በትምህርት ነው የሚለውን ባሕላዊ አስተሳሰባችንን ጥሰን ማለፍ አለብን። በትንንሽ ነገሮች ላይ ከመታመን ተነሥቶ ወደ ትልልቅ ሹመት ወደሚያደርሰው የእግዚአብሔር አሠራር ልንመለስ ይገባል።

## 4. ምሪት ለመቀበልና የመምራት ችሎታን ለማሳደግ በእግዚአብሔር መታመን።

ተሰጥኦ ላላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትልቁ አደጋ ነገሮችን በራሳቸው ጥንካሬ መሥራት ነው። አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች ብዙ የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ አስፈላጊው ነገር በራሳችን ጥንካሬ የምንሠራው ነገር ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእኛ አልፎ በራሱ ጥንካሬ የሚሠራው ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎታቸውን በተመለከተ በእርሱ መታመንን መማር

አለባቸው:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ አገልግሎት ሲያሠማራ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ብሏቸዋል (ዮሐ. 15:5):: ጳውሎስ ሁሉን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ጥንካሬን ስለ ሰጠውና ስላስቻለው እንደ ሆነ ተናግሯል (ፊልጵ. 4:13)::

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ:: 2ኛ ቆሮ. 4:7-12፤ 12:7-10፤ 2:17፣ 4:1-2:: ስመሪነት በእግዚአብሔር ስለ መታመን ምን እንማራለን? |

የ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክት በዚህ እውነት ላይ ያተኩራል:: የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ክብር የማገልገል ችሎታና ጥንካሬ የሚመጣው እኛ ስንደክም እንደ ሆነ ሊያስታውሱ ይገባል:: በ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክት ውስጥ ያሉትን የሚከተሉትን እውነቶች አስተውል::

ሀ. 2ኛ ቆሮ. 4:7-12:- እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን እድገትና ልማት የእርሱ ኃያል ሥራ እንጂ የመሪው ችሎታ እንዲሆን አይፈልግም:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ኃይለኛና የከበረውን ወንጌል «በሸክላ ዕቃ» ውስጥ አስቀመጠ:: ደካማው ሥጋችንና ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን እግዚአብሔር ኃይለኛውን ወንጌል ለሰዎች ያሳይ ዘንድ ዕድሉን ይሰጠዋል:: በሕይወታችን ሊያሸንፉን የደረሱ አስቸጋሪ ነገሮችን እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን በማሳየት ደካማ በሆኑ ሰዎች አልፎ መንግሥቱን ይገነባል::

ለ. 2ኛ ቆሮ. 12:7-10:- ጳውሎስ የተፈጥሮ ተሰጥኦ ያለው ሰው ነው:: እግዚአብሔርም አስገራሚ ችሎታንና መንፈሳዊ ስጦታን በመስጠት አከበረው:: እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በራእይ እንዲያይ ፈቅዶለታል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ይህ ልዩ ራእይ ለሰው ልጆች አደገኛ እንደ ሆነ ያውቃል:: ስለዚህ ለጳውሎስ የግል ድካሙን ለመግለጥ ችግር ሰጠው:: ጳውሎስ እግዚአብሔር እንዲያስወግድለት ሲጸልይ እንኳን፣ እግዚአብሔር ለጳውሎስ አስፈላጊ እንደ ሆነ በመግለጥ እምቢ አለው:: ጠንካራ



አካል ባለው ጳውሎስ ከመጠቀም ይልቅ ደካማ በሆነው ጳውሎስ ታላቅነቱን ገለጠ:: ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 3:4-5 ላይ እንደ ተናገረው፣ ስኬቱ የመጣው እግዚአብሔር በእርሱ ለመጠቀም ስለ መረጠው ነው:: በውስጡ ካለው ኃይል የተነሣ አልነበረም::

ሐ. 2ኛ ቆሮ. 2:17፣ 4:1-2:- ጳውሎስ ሰዎች እንዲያምኑት ለማድረግ ወይም ራሱን ስኬታማ ለማድረግ «ማታለያም» ሆነ ሥጋዊ መሣሪያ አልተጠቀመም:: የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ በግልጽ ለመስበክና በሰዎች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተአምራትና ደኅንነትን እንዲሠራ በመፍቀድ ወሰነ::

ጳውሎስ በአገልግሎቱና በነገር ሁሉ በእግዚአብሔር መደገፍን ስለ ተማረ፣ እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲሆን በሚፈቅደው ነገር ሁሉ «በቃኝን» ተምሯል:: (ፊልጵ. 4:11-13ን ተመልከት):: ጳውሎስ ከእግዚአብሔር መገኘት ሌላ በሕይወቱ የሚፈልገው ነገር አልነበረም:: ጳውሎስ ሞት ቢሆንም እንኳን ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ክብር ለማፍሰስ ፈቃደኛ ነበረ (2ኛ ቆሮ. 2:15-16፤ 2ኛ ጢሞ. 4:6) ጳውሎስ የእርሱ ሕይወትና የግል ምቾቱ አስፈላጊ እንዳልሆነ አውቋል:: አስፈላጊው ነገር ቶሎ ይሙትም ይቆይ፣ ሕይወቱ ለእግዚአብሔር ክብር መዋሉ ነው:: ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ክብር ሊያደርግ ስለሚፈልገው ነገር በእግዚአብሔር ላይ ይደገፍ ስለ ነበር፣ ራሱን ከሞት ለመጠበቅ መጣርም ሆነ አካላዊ ጥቅምን ማግኘት ለእርሱ ቦታ አልነበራቸውም::

እንደ መሪነታችን፣ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ልንደገፍ ይገባል:: በእግዚአብሔር ላይ የምንደገፈው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ እንዲነግረን ነው:: ሥራውን መሥራት የሚችሉ ትክክለኛ ሰዎችን እንዲሰጠን በእርሱ ላይ እንታመናለን:: እግዚአብሔር ለሥራው የሚሆን ገንዘብ እንዲሰጠን በእግዚአብሔር ላይ እንታመናለን:: በአመራራችን ላይ የሥጋ ፍላጐታችን እንዳያሸንፈን ለየዕለት ጥንካሬአችን በእግዚአብሔር ልንታመን ይገባል:: ራሳችንን ዝቅ በማድረግ መምራት እንድንችል

በእግዚአብሔር እንታመናለን። በእግዚአብሔር ላይ በሙሉ መታመን መኖርን ተምረሃል?

14ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በራሳቸው ጥበብ፣ ትምህርት፣ ከታላላቅ ሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ በሃብታቸው፣ ባላቸው የመከራከሪያ ነጥብ ወይም የእግዚአብሔርን ሥራ በማስፈጸም ኃይላቸው የሚታመኑበትን መንገዶች ግለጥ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የራሳቸውን ድካም እንዲረዱ እንደሚፈልግ ቢገባቸውና በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ታምነው የእግዚአብሔርን ቃል ለሰኬታቸው ቢሰብኩ ኖሮ ምን ያህል የተለየ አገልግሎት ይኖራቸው ነበር። ሐ) «ደካማ» የሆንክባቸውን ጥቂት ነገሮች ዘርዝር። እግዚአብሔር በሕይወትህ ኃይሉን እንዲያሳይ እነዚህ ድክመቶች በምን መልኩ ይጠቅሙታል?

15ኛ ጥያቄ:- መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያሳዩትን ከላይ ያየናቸውን ለስኬታማ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉትን አራት ባሕሪዎች ቃኝ። ሀ) እነዚህ አራት ባሕሪዎች የሕይወትህ ክፍሎች ናቸው? መልስህን አብራራ። ለ) እግዚአብሔር ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ይጠቀምብህ ዘንድ በእነዚህ አራት ባሕሪዎች ለማደግ ምን ማድረግ ይገባሃል?

## ስኬታማ ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት:- ከመሪው ውስጣዊ ሕይወቱ የሚመጡ ባሕርያት (ክፍል 1)

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች ለእግዚአብሔር ክብር በሚያመጣ መንገድ ማገልገል ካለባቸው፣ መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ሊያሳድጓቸው የሚገቡ ጥቂት ባሕርያትን አጥንተናል። ሁለተኛው የባሕሪ ምድብ የሚመለከተው መሪዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ ይመሩ ዘንድ የትኞቹን የግል ባሕርያት ማሳደግ እንዳለባቸው በማሳየት ላይ ይሆናል።

16ኛ ጥያቄ:- መሳፍንት 6 እና 7ን አንብብ። ሀ) ጌዴዎን ድፍረት ያሳየባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መሪነት



ድፍረትን የሚጠይቁባቸውን ምሳሌዎች ዘርዝር። ሐ) ለቤተ ክርስቲያን መሪ ድፍረት ለምን ያስፈልጋል ብለህ ታስባለህ?

1. ድፍረት:- ሁሉንም ሁኔታዎች የመቋቋም ችሎታና ለእውነትና ለወንጌል እስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ከሰዎች ሁሉ የተለየ አቋም መያዝ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጣም ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል። መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲደረግ የኖረውን ነገር ከመቀጠል ይልቅ አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ድፍረት ያስፈልጋቸዋል። ድፍረት ሌሎች በማይስማሙበት ጊዜም እንኳ ለእምነታችን ብቻችንን እንዳንቆም ያስችለናል። ድፍረት የሐሰት ወይም ሚዛናዊ ያልሆነ ትምህርት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች በሌሎች ዘንድ ዝነኛ ቢሆኑም እንኳን፣ እንድንቋቋማቸው ያደርገናል። ሌሎች ሽማግሌዎች ቢያደርጉትም እንኳን፣ በድፍረት በእግዚአብሔር ዓይን ትክክል ያልሆነውን ነገር መቋቋም እንችላለን። ድፍረት የሌለው ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚገባ መምራት አይችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ መንፈሳዊ ድፍረትን እናያለን። በኢያሱ 1:6-9 እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ለአዲሱ መሪ ኢያሱ፣ በርታ ጠንክር ሲለው እናያለን። የጌዴዎን ድፍረት 300 ሰዎችን ብቻ ይዞ ታላቅ ሠራዊት እንዲገጥም አድርጎታል። ዳዊትም ታላላቅ ወታደሮች እንኳን ፈርተው ባለበት ሰዓት በድፍረት ጎልያድን ገጥሟል። የጳውሎስ ድፍረት እስርና ሞትን ያስ እንዳች ፍርሃትና ሽሽት እንዲቀበል አድርገውታል። ድፍረቱ ጴጥሮስ የወንጌልን ቅንነት የሚጎዳ ነገር ሲያደርግ ሲያየው ፊት ለፊት እንዲቃወመው አድርጎታል (ገላ. 2:11-14)።

እንዲህ ያለው ድፍረት ከየት ይመጣል? ይሄ ወደ መሪነት ከመግባታችን በፊት ልናሳድገው የሚገባ ነገር ነው። ድፍረት የሚመጣው እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነ ከመረዳትና በምንም

ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በእርሱ ከመተማመን ነው:: ያ የሚጀምረው ገና በትምህርት ቤት እያለን ጓደኞቻችን እያሾፉብን ለእግዚአብሔር ጽኑ አቋም ይዘን ከቆምንበት ዘመን ነው:: ድፍረታችን የሚያድገው በመዘምራን ቡድናችን ውስጥ ሌሎች ሰዎች ትክክል ያልሆነ ነገር ሲሠሩ እነርሱን በመቃወም ለመናገር ስንገደድ ነው:: እርሱንና ቃሉን በማመን ብቻችንን ከእግዚአብሔር ጋር መቆም ስንማር ነው የቤተ ክርስቲያን መሪ ስንሆን የሚያስፈልገንን ድፍረት የምናሳድገው:: መሪነት በጣም ብቸኛ የምንሆንበት ቦታ ነው:: ይህም ማለት ያለምንም ማዳላት በክርስቶስ ወንድምና እኅቶቻችን ከሆኑት ጋር መሥራት ሲገባቸው፣ እንደ ባሕላቸው መምራት የሚፈልጉ ሽማግሌዎችን፣ ለራሳቸው ዘመዶችና ጐሣዎች የሚያዳሉ ሽማግሌዎችን ተቃውመን የምንቆምበት ነው:: ድፍረት ማጣት ማለት ዝምተኛ መሆንና ስሕተት ሲሠሩም አብሮ መሥራት ነው:: ድፍረት ሁሉም ሽማግሌዎች ሲቃወሙንና ከመሪነት ሲያስነሡን እንኳን ለእውነት መቆም ነው::

የሚያስገርመው፣ ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ላይ ካለን ፍጹም እምነት የተነሣ ከሌሎች ጋር ጊዜያዊ ግጭት ቢፈጥርብንም፣ የኋላ ኋላ ግን ሌሎች ምንም ቢሉ በሚያምነው ነገር የሚጸናን የቤተ ክርስቲያን መሪ ሰዎች ማክበራቸው ነው:: ያንን በትሕትና በእግዚአብሔር በመታመን ካደረገው፣ ሰዎች ያ ሰው መሪያቸው እንዲሆን ወደ እርሱ ይመጣሉ:: ሁልጊዜ ትክክል የሆነውን ነገር እንደሚናገርና እንደሚሠራ ያምናሉ:: እግዚአብሔርም ለእርሱ ካለው ፍቅር የተነሣ ልጁ ይስሐቅን እንደ ሠዋው አብርሃም መልካም ዝናና ታዋቂነታቸውን ለእግዚአብሔር ፍቅር የሚሠዉትን መሪዎች ያከብራቸዋል::

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ድፍረት እንዲኖረው ስለሚያስፈልግበት ሁኔታ ዘርዝር:: ለ) ድፍረት ማጣት በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ላይ ስለሚያስከትለው ተጽዕኖ ግለጥ:: ሐ) በምን ዓይነት መንገድ ነው የአንድ ሰው ድፍረት በሌሎች ዘንድ ክብርን የሚያመጣለት? |



2. ትሕትና:- ራሳችንን ከሌሎች የተሻልን አድርገን አለማየትና ሌሎች ክብርን እንዲቀበሉ መፍቀድ::

| |
|---|
| 18ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 11:28-30፤ ሉቃ. 18:14፤ ፊልጵ. 2:8-9፤ 1ኛ ጴጥ. 5:5-6ን እንብብ:: ሀ) ትሑት ስለ መሆን እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል? ለ) ከኢየሱስ ሕይወት ስለ ትሕትና ምን እንማራለን? ሐ) ትሕትና በጣም አስፈላጊ የቤተ ክርስቲያን መሪ ባሕሪ የሆነው ለምንድን ነው? |

ግሪኮች የትሕትናን ባሕሪ አያከብሩም ነበር:: ቃሉ ያገለግል የነበረው ሌሎችን በመፍራት የሚንቀጠቀጥና፣ ሰዎች በጣም የሚናቅ ነው ብለው የሚገልጡት ሰው ነው:: ነገር ግን ይህ ቃል በክርስትና ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት የመንፈሳዊ ሰዎች ባሕሪ ውስጥ አንዱን ነው የሚገልጠው:: መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እግዚአብሔር ኩራትን ሁሉ እንደሚጠላና ትሕትናን እንደሚያከብር ይናገራል:: ሙሴ ታላቅ የተባለው በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ትሑት በመሆኑ ነበር (ዘኁል. 12:3):: ኢየሱስ ራሱን የሚገልጠው ትሑት አድርጐ ነበር:: ራሱን ዝቅ በማድረግ ለማያዊ ክብሩን ሁሉ ትቶ ሰው ሆነ:: ጴጥሮስ ሲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ትሑታንን ግን ያከብራል ብሏል::

ስለዚህ ትሕትና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስፈላጊ ባሕሪ ውስጥ አንዱ ነው:: ግን ትሕትና ምንድን ነው? በምንራመድበት ስፍራ ሁሉ ራሳችንን ዝቅ አድርገን እኛ አንጠቀምም፣ ሌሎች ሲረማመዱብን የሚገባ ችሎታና የማንጠቅም ቆሻሻዎች ነን ማለት ነው? ያ ማለት ስለ ራሳችን ዝቅተኛ ግምት አለን፣ ስለዚህም ሌሎች የሚፈልጉትን እናደርጋለን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትሕትና የሚከተሉትን አሳቦች ያጠቃልላል:-

ሀ. በተለምዶ ስለ ራሳችን ስናስብ ራሳችንን በጥሩ መልኩ ነው የምንመለከተው:: እኛ ከሌሎች የተሻለን እንደ ሆንን እናስባለን:: እኛ ከተሻለ ቤተሰብ የመጠን፣ ቀላ ያለ የቆዳ ቀለም ያለን፣ ጥበበኛና ትክክለኛ ምላሽ ያለን ሰዎች አድርገን ራሳችንን እንመለከታለን::

ይህ ደግሞ የትሕትና ተቃራኒ ወደ ሆነው «ትዕቢት» ይመራል:: ትዕቢት ራሳችንን ከእኛ እንደሚሻሉ ከምናውቃቸው ሰዎች ጋር እንድናነጻጽር ያስገድደናል:: ትሕትና ግን ራሳችንን ልክ እግዚአብሔር እንደሚያየን እንድናይ ይረዳናል:: በእዎንታዊ ጎኑ፤ እግዚአብሔር የሰጠንን ጸጋና ችሎታ እንመለከታለን (ሮሜ 12:3):: ነገር ግን በአሉታዊ ጎኑ፣ ድካማችንን፣ ራስ ወዳድነታችንንና ለእግዚአብሔር በምንሰጠው አገልግሎትና ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት የወደቅንባቸውን በርካታ ጊዜአት እናያለን:: ስለዚህ እኛ የተለየን እንዳልሆንን እናውቃለን:: ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ባይሆን ኖሮ፤ ለአገልግሎትም ሆነ ለመሪነት የማንገባ ነበርን::

ለ. ሁላችንም በራሳችን ብቃት የመርካት አዝማሚያ አለን:: አካባቢያችን እንመልከትና ራሳችንን ከሌሎች ጋር እናነጻጽራለን:: እንደ ሌላ ሰው ከፍተኛ ስጦታ አይኖረን ይሆናል፣ ነገር ግን ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በማነጻጸር፣ ደህና እንደ ሆንን እናስባለን:: መንፈሳዊ ሕይወታችንን (ጸሎታችንንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን) በማነጻጸር «እኔ ከነእገሌ የተሻልኩ ነኝ፣ ስለዚህ ጥሩ ነኝ» ብለን እናስባለን:: ነገር ግን ክርስቲያናዊ ትሕትና የሚመጣው ራሳችንን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስናነጻጽር ነው:: ከዚያም ጉራ የምንነዛበት ምንም ነገር እንደ ሌለን እንገነዘባለን:: ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሄደን የእግዚአብሔርን ቃል ተምረን ይሆናል:: ነገር ግን ያንን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው እውነት ሁሉ ጋር ስናነጻጽር እውቀታችን በጣም አነስተኛ እንደ ሆነ እንገነዘባለን:: ወይም ጥሩ ሙዚቀኞች ልንሆን እንችላለን፣ ነገር ግን ከታላላቅ ሙዚቀኞች ጋር ሲነጻጸር የእኛ ክህሎት ምንም ማለት አይደለም:: ተሰጥኦ ያለን አስተዳዳሪዎች ልንሆን እንችላለን፤ ነገር ግን ከእኛ በጣም የሚበልጡ እንዳሉና እነርሱ ላይ ለመድረስ ገና ማደግ እንዳለብን እናውቃለን:: ታዋቂ ሰባኪ ልንሆን እንችላለን፣ ነገር ግን ጥሩ ያልሆንባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ እንረዳለን:: ክርስቲያናዊ ትሕትና ሁል ጊዜ መሪው በጣም ጥሩ እንዳልሆነና



ማሻሻል የሚገባው በርካታ ነገሮች እንዳሉ እንዲሰማው ያደርጋል:: እርሱ እንደ ግብ የሚያየው ባይደርስበትም ፍጹምነትን ነው:: የእርሱ መስፈርት ከሌሎች ጋር በማነጻጸር የሚያየው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ነው::

ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትሕትና የሚያተኩረው ሰውየው በእግዚአብሔር ፊት ባለው ዋጋ እንጂ በዓለም እይታ ሲታይ ባለው አይደለም:: በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠራችን በእግዚአብሔር እንደምንከበር እናውቃለን:: እርሱ ስለ መረጠንና ልጆቹ ስላደረገን እንዳከበረን እናውቃለን:: እግዚአብሔርን የምናገለግልበት ልዩ ጸጋ ስለ ሰጠን በእግዚአብሔር እንደምንከበር እናውቃለን:: ከዚህ የተነሣ፣ ምንም የምናፍርበት ነገር የለም:: ግን ይህ ለሁሉም አማኝ ስለሚሠራ ከሌሎች የተሻልን እንዳልሆንን እናውቃለን:: የእኛ የሆነ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ እናውቃለን:: ራሳችን ያመጣነው አይደለም:: (1ኛ ቆሮ. 4:5-7ን ተመልከት::) ትሑት ሰው ጠቃሚነቱ ከእግዚአብሔር እንጂ ሰብአዊ ከሆነ ነገር እንዳልሆነ ይረዳል:: እውነተኛ ዋጋችን የሚገኘው ወንድ በመሆናችን፣ ከተወሰነ ጐሣ በመውጣታችን፣ ወይም የተወሰነ የትምህርት ደረጃ ስላለን፣ ወይም የመሪነት ቦታ ስላለን አይደለም:: በእግዚአብሔር ዓይን፣ ዓለም አስፈላጊ የሚላቸው እንደ ሀብት፣ ትምህርት፣ ብሔርና ውበት ምንም እንዳይደሉ እናውቃለን:: ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ዓለም እንደሚገልጠው ታዋቂ ባለመሆናቸው ራሳችንን ልናሳፍርም ሆነ ከዓለም መስፈርት ተሽለን በመገኘታችን ልንኩራ አያገባም::

መ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትሕትና አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ መሪ የሚሆንበት ምክንያት እንደሌለ ይረዳል:: ወይም ሌሎች ሰዎች የሌላውን ሰው አሳብ ትተው የእኛን አሳብ ብቻ የሚሰሙበት ምክንያት እንደሌለ ይረዳል:: ወይም ከሌሎች የበለጠ ሀብታም የምንሆንበት ምክንያት እንደሌለ ይረዳል:: ስለዚህ፣ አንድ ሰው መሪ እንዲሆን ሲመርጥ፣ ወይም የሌሎች ሰዎች አሳብ ሲደመጥ፣

ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች ከእኛ ይልቅ ሲባረኩ ደስ ይለናል፡፡

ሠ. ትሕትና ማለት በእግዚአብሔር ፊት ማን እንደ ሆንን ስለምናውቅ፣ ስለ ራሳችን መከራከር አያስፈልገንም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም፣ ለሰዎች ክብር የሚያመጡ ነገሮችን በመተው፣ ራሳችንን እንደ ተሻለ ስንቆጥር ራሳችንን ዝቅ አድርገን የምናገለግልበት ነው፡፡ ኢየሱስ አምላክነቱን እያወቀ ክርክር አላነሣም፡፡ ይልቁንም፣ ሰው ለመሆን ሲል አምላክነቱን በፈቃዱ ተወ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የእኛ ትሕትና የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እያወቅን፣ ወደ መሪነት ክብር ራሳችንን ልንገፋ አይገባም፡፡ ይልቁንም፣ የመሪነትን ክብር በመተው ራሳችንን የሌሎች አገልጋይ በማድረግ ዝቅ እናደርጋለን፡፡

ረ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትሕትና ማለት ከሌሎች ሰዎች ክብር ወይም ጥቅም እንፈልግም ማለት ነው፡፡ መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፊት ለፊት ብንቀመጥ ወይም ከኋላ ብንቀመጥ፣ ወንበር ላይ ብንቀመጥ ወይም ወለል ላይ፣ ሰዎች መሪ እንደ ሆንን ቢያውቁ ባያውቁ ምንም ለውጥ አያመጣም፡፡ ይህ ማለት ለመብታችን አንታገልም፣ ነገር ግን በሥልጣን ላይ ላሉት እንገዛለን ማለት ነው፡፡ ራሱን መስጠት ያልተማረ ሰው ጥሩ መሪ አይወጣውም፡፡ ለዚያ ነው ጴጥሮስ ወጣቶች ከትዕቢት እንዲጠነቀቁና ራሳቸውን ለመሪዎች በማስገዛት ትሕትናን እንዲማሩ የነገራቸው፡፡ ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ነው እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት በመሥራት በመሪነት የሚያስነሣቸው፡፡

ሰ. ትሕትና ማለት በሌሎች ሰዎች ዘንድ ለመታወቅ ምንም ዓይነት ጥረት እናደርግም ማለት ነው፡፡ ለመታየት ስንል የመዘምራን ቡድን ውስጥ ለመግባት ወይም ለመስበክ አንጥርም፡፡ ሰዎች የምናደርገውን ቢያዩ፣ ቢያበረታቱን ወይም ለሠራነው ሥራ ቢያከብሩን ምንም ማለት አይደለም፡፡ ትሕትና ማለት የሚያከብረንን እግዚአብሔር ማክበር ነው፡፡



ይህ ባሕሪ ዓለም ከሚያስተምረው ጋር ተቃራኒ ነው፡፡ ዓለማችን በከፍተኛ ፍጥነት መሮጥ በመቻላቸው፣ ከታላላቅ ቤተሰብ በመምጣታቸው፣ ምን ያህል ሕዝብ ወደ ጌታ በማምጣታቸው፣ ረጅም ሰዓት በመጸለያቸው፣ ወዘተ. . . ጉራ የሚነዙ ሰዎችን ታከብራለች፡፡ የቀበሌ ሊቀመንበር ለመሆን ወይም የስኬትን ጥቅም ለማግኘት በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ለመሰለፍ ራሳቸውን ወደ ፊት የሚገፉት እነርሱ ናቸው፡፡ ስኬታማ የሚሆኑትንም ዓለም ታከብራለች፡፡ ክርስቲያኖችም ወንጌላዊ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ በመሆናቸው፣ ወይም በትምህርት ደረጃቸው ኩራት የሚሰማቸው ከሆነ፣ በትዕቢት ወጥመድ ይያዛሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚጠላና ትሑታንን እንደሚያከብር ይናገራል፡፡ ትሑት መሆንን ተምረሃል?

> 19ኛ ጥያቄ:- ሀ) ትሕትና ለክርስቲያኖች ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው በዓለማውያን ግን እንደማይከብር እንዴት እንዳለብክ አብራራ፡፡ ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ትሕትናን እንዴት ማሳየት እንደሚችል አብራራ፡፡ ሐ) ምን ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትዕቢትን እንደሚያሳዩ ማብራሪያዎችን ዘርዝር፡፡

## 3. ጽናት:- ነገሮች በጣም አስቸጋሪ ሲሆኑ የመቀጠል ባሕሪ፡፡

ችግርን የሚወድ ሰው የለም፡፡ ስንታመም፣ ወደ ሐኪም ዘንድ ሄደን ቶሎ እንዲሻለን እንፈልጋለን፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲኖር፣ ወዲያውኑ እንዲስተካከል እንፈልጋለን ወይም ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን፡፡ በግንኙነታችን ችግር ሲፈጠር፣ ወዲያውኑ ችግሩን ልናስወግደው እንሞክራለን፣ ወይም ሰውየውን ትተን ከዚያ ሁኔታ ለመራቅ እንሞክራለን፡፡

ምንም እንኳን ይህ የተለመደ ምላሽ ቢሆንም፣ ኃጢአተኞች በሞሉባት ዓለም የምንኖር በመሆናችን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደሚገጥማቸው ማወቅ አለባቸው፡፡ እግዚአብሔር የሚጠቀመው በመከራ ውስጥ በሚጸኑት መሪዎች ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ውጤታማ መሪ ለመሆን፣ በመከራ ጊዜ

መጽናትን መማር አለብን፡፡ አገልግሎታችን የጠበቅነውን ያህል ባለማደጉ ተስፋ የምንቆርጥ፣ ወይም ችግሮች እንደ ተፈጠሩ የምናቆምና ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ወይም ሥራ የምንገባ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር ብዙ እንሠራም፡፡

አብዛኛዎቹ አገልግሎቶች ችግር ሲፈጠር በታማኝነት ማገልገላችንን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መገንባት ሲጀምር፣ በችግር ላይ ችግር መጥቶበት ነበር፡፡ በሚሠራው ሥራ የሚያሾፉበትና እርሱንና አይሁዳውያንን ለማጥቃት የሚያስፈራሩት ውጫዊ ጠላቶች ነበሩ፡፡ ሐሰተኛ ወሬን በማስፋፋት የነህምያን መልካም ስም ለማጥፋት ሞከሩ፡፡ አይሁውያንም እኩል ያለመሆን ውስጣዊ ችግሮችም ነበሩባቸው (ነህ. 4-6)፡፡ በእያንዳንዱ ሁኔታ፣ ለነህምያ ሥራውን እቁሞ በፋርስ መንግሥት ውስጥ ወዳለው ጥሩ ሥራው መመለስ ቀላል ይሆንለት ነበር፡፡ ነገር ግን፣ እርሱ ጸና፡፡ እናም እግዚአብሔር ሥራውን ለመጨረስና ለራሱም ክብርን ለማምጣት ተጠቀመበት፡፡ እግዚአብሔር በጠራን አገልግሎትና ራእይ እስካልጸናን ድረስ፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ግዳጅ አንወጣም፡፡

በ2ኛ ቆሮ. 4:7-12 ጳውሎስ በሐዋርያነቱ ውጤታማ የሆነው ባለማቋረጡ እንደ ሆነ ይነግረናል፡፡ የሚወድቅ የመሰለባቸው በርካታ ጊዜያት እንደ ነበሩ ያካፍለናል፡፡ ወድቆ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜም ይነሣል፡፡ እናም ፈጽሞ ማቆምን አይፈቅድም፡፡ ለማገልገል በሚሞክርበት ቦታ ሁሉ ተቃውሞ ይገጥመዋል (2ኛ ቆሮ. 11:23-29 ላይ ያሉትን የጳውሎስ ተጋድሎ ዝርዝሮች አንብብ)፡፡ ነገር ግን በመጽናቱ እግዚአብሔር ብዙ ቤተ ክርስቲያናትን እንዲያቋቁምና ወንጌልን በሺህ በሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች እንዲያስፋፋ በታላቅ ኃይል ተጠቀመበት፡፡ ጳውሎስ በመጀመሪያ ተቃውሞ እንደ ገጠመው አገልግሎት አቁሞ ቢሆን ኖሮ ዓለም ምን ልትመስል እንደምትችል አስብ! ከኢየሩሳሌም ውጪ ምንም ቤተ ክርስቲያን አይገኝም ነበር፡፡ እኛም ብንጸና



እግዚአብሔር በእኛ ሲያደርግ የሚችለው ነገር ይታይህ! ዛሬ እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልገውን ለማቆም እያንገራገርክ ይሆን? ጽና፡፡ እግዚአብሔር ያንን ለራሱ ክብር የሚጠቀምበት ጊዜ ይመጣል፡፡

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ነገሮች አስቸጋሪ ሲሆኑ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት እንደሚያቆሙን አብራራ፡፡ ለ) ይሄ እግዚአብሔር እንዲፈጽሙለት የሚፈልገውን ነገር የሚያቆመው በምን ዓይነት መንገድ ነው? ሐ) ለማቋረጥ የሚፈታተኑህን ነገሮች ዘርዝር፡፡ መንፈስ ቅዱስ የመሥራትን ኃይል እንዲሰጥህ ጊዜ ወስደህ ጸልይ፡፡

## 4. የታደሰ አእምሮ፡- አእምሮውን ያለማቋረጥ በመረዳትና በመገለጥ ለማደግ የሚጠቀም ሰው፡፡

> 21ኛ ጥያቄ:- ሀ) የሚከተሉት ጥቅሶች ስለማያምኑት ሰዎችና አእምሮአቸው እንዲሁም ስለሚያምኑት ሰዎችና አእምሮአቸው ምን እንደሚል ተመልከት:- ማቴ. 22:37፤ ሉቃስ 24:45፤ ሮሜ 1:28፤ 8:5-8፣ 12:2፤ 1ኛ ቆሮ. 14:15፤ 2ኛ ቆሮ. 4:4፤ ኤፌ. 4:20-24፤ ቆላ. 1:21፤ 3:2፤ ቲቶ 1:15፤ 1ኛ ጴጥ. 4:7፡፡ ለ) የዘመናችን አማኞች ከአእምሮአቸው ይልቅ በስሜታቸው የሚመሩ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ? ሐ) አስተሳሰባችን በተግባራችን ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣባቸውን መንገዶች ግለጥ፡፡ መ) መሪዎች በአእምሮአቸው አያደጉ የሚሄዱባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

ጥንቃቄ የተሞላበት የአዲስ ኪዳንን ጥናት እግዚአብሔር በአእምሮአችን ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ያሳየናል፡፡ ከመዳናችን በፊት፣ አእምሮአችን በኃጢአት ጨለም በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነበር፡፡ ደኅንነት ወደ እኛ የመጣው ስለ ኢየሱስ እውነት ስንማርና አእምሮአችን መቀየር ሲጀምር ነው፡፡ እንደ ኢየሱስ ተከታይነታችን፣ አስተሳሰባችንን ልንቀይርና አእምሮአችንን ልናሳድግ ይገባል፡፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን ፍቅር የምናሳየው እግዚአብሔርን «በአእምሮአችን ሁሉ» ስንወድ ነው፡፡ እግዚአብሔርን በሚያከብር መንገድ እንድንኖር ካስፈለገ፣

በአእምሮአችን መታደስ መለወጥ አለብን:: ስለዚህ መሪ ውጤታማ እንዲሆንና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንዲመራ አእምሮውን ሁልጊዜ ማሳደግ አለበት:: አእምሮአችን እንድናሳድገው ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው:: ልክ እንደ ጡንቻዎቻችን፣ አእምሮአችንን ካልተጠቀምንበት እየደከመ ይሄዳል:: ስኬታማ የቤተ ክርስቲያን መሪ በሚከተሉት መንገድ ለማደግ አእምሮውን ሁልጊዜ ይጠቀማል፦

ሀ. በእግዚአብሔርና በቃሉ እውቀት ለማደግ ይፈልጋል:: ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ በቂ የሆነ እውቀት ያለው መሪ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ በጣም ስኬታማ የሆኑ መሪዎች የእግዚአብሔር ቃል መረዳታቸው እንዲጨምር ሁልጊዜ ቃሉን ያጠናሉ::

ለ. በዙሪያው ስላለው ዓለም ለመረዳት ይፈልጋል:: «ሁሉም እውነቶች ሁሉ የእግዚአብሔር እውነቶች ናቸው» የሚባል አባባል አለ:: ስለዚህ ስኬታማ መሪ ከመንፈሳዊ ነገር ውጪ ስላሉ ነገሮች የሚያነብና የሚያስብም ነው:: የተጠራው የእግዚአብሔርን መንጋ ለመምራት ነው፣ ያ ማለት የእግዚአብሔር እውነት በሚኖሩበት ዓለም ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ሊያካፍላቸው ይገባል ማለት ነው:: ስለዚህ ስለ መንግሥትና ስለ ፖለቲካ እንዲሁም እንዴት በቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ያጠናል:: ስለ ዓለም ሁኔታና ስለ አገሮች አሳብ ያጠናል:: እንደ ውርጃ ስላሉ የሥነ ምግባር ጉዳዮች ያጠናል፣ እግዚአብሔር ስለ ሥራ ስላለው አመለካከት ወይም ዓለም ለወጣቶች የምታስተምራቸው እሴቶች ምንድን ናቸው የሚለውን ያጠናል::

ሐ. መሪ በዘመኑ ያሉ ጉዳዮችን መረዳት ይፈልጋል:: ልክ እንደ ይሳኮር ሰዎች በዘመኑ ሕዝቡን በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት ምን እየሆነ እንዳለ ይረዳል (1ኛ ዜና 12:32)::

በዘመናችን፣ የምናተኩረው በስሜታችን ላይ ነው:: ሞቅ ያሉ



አምልኮዎችና ደስ የሚያሰኙ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን እንወዳለን:: ነገር ግን እኛና ሌሎች አማኞች ያለንን አስተሳሰብ ካልለወጥን በስተቀር፣ እግዚአብሔር በእኛና በሕዝቡ ላይ ለውጥ አያመጣም::

ውጤታማ መሪ የሚያደርጉና ከአእምሮአችን ጋር የተያያዙ ሌሎች ሁለት እውነታዎች አሉ:: አንደኛ፣ መሪ ሌሎች የሚያምኑትን ከመከተል ይልቅ ለራሱ የሚያስብ ነው:: አብዛኛ ዎቹ ሰዎች የራሳቸውን አስተሳሰብና አመለካከት ለማሳደግ ጊዜ አይሰጡም:: ሰዎች ምንም ይበሉ ምን ያለ አሳብ ይቀበላሉ:: የአብዛኛውን ሕዝብ አስተሳሰብ ይከተላሉ:: ነገር ግን ታላላቅ መሪዎች በጥልቀት በጉዳዮች ላይ በማሰብ የራሳቸውን እምነት ያዳብራሉ:: ሌሎች እንደዚያ ባያስቡም እንኳን፣ በእምነታቸው ይጸናሉ::

ሁለተኛ፣ መሪ በተግባር ላይ የሚያውለው ጥበብ አለው:: መጽሐፈ ምሳሌ ስለ ጥበብ የሚያወራ መጽሐፍ ነው:: እውነትን መረዳት ከሆነው እውቀት በተለየ መልኩ፣ ጥበብ እውነታዎችን በሕይወት ላይ እንዴት መተግበር እንደሚቻል ማወቅ ነው:: በጣም ጥሩ አሳብ ያላቸው ብዙ መሪዎች አሉ:: ነገር ግን አብዛኛዎቹ አሳቦቻቸው ተግባራዊ አይደሉም:: በቤተ ክርስቲያን ፊት ለተጋረጡ ችግሮች መፍትሔን አያመጡም:: ስለዚህ በጣም ውጤታማ የሆኑ መሪዎች ለተለያዩ ጉዳዮች ምርጥ የሆኑ መፍትሔዎችን የሚያመጡ ናቸው:: አሳቦቻቸው ደስ የሚሉ ዕቅዶችን ብቻ ሳይሆን፣ እውነተኛ ለውጦችን የሚያመጡ ናቸው::

## 5. ራስን መሥዋዕት ማድረግ፦ ለሌሎች ጥቅም ሲባል የራስን ፍላጎት መተው::

በተደጋጋሚ በዓለማውያን መሪዎችና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች

መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት የሌሎች አገልጋይ የመሆን አመለካከት ነው:: ከአገልጋይ መሪነት በስተጀርባ ለሌሎች ሰዎች ስንል ራሳችንን የመስጠት ባሕሪ አለ:: ኢየሱስ ዮሐንስ 15:12-13 ላይ እንዳለው፣ «ትእዛዜ ይህች ናት፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ:: ስለ ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ማንም የለውም::» ለሌሎች ሲል የራሱን ፍላጐት መተውን ያልተማረ መሪ፣ እንደ አገልጋይ መሪ መምራት አይችልም:: የቤተ ክርስቲያን አመራር ማለት ሌሎችን ለማገልገል ሲል ለራሱ ይጠቀምበት የነበረውን ጊዜና ገንዘቡን መስጠት ነው:: ሴቶች ከወንዶች በላይ ይህንን በቀላሉ ያደርጉታል:: ሴቶች ለሌሎች ሲሉ የሚፈልጉትን ነገር ይተዋሉ:: ባሎቻቸውን ለማገልገል ጊዜአቸውን ያስተካክላሉ:: ወይም ያለ ራስ ወዳድነት ሕፃናት ልጆችን ይንከባከባሉ:: ወንዶች ናቸው ከዚህ ባሕሪ ጋር የሚታገሉት:: ሕፃናት ልጆች ከነበርንበት ጊዜ አንሥቶ ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉልን መጠበቅን ተምረናል:: እናታችን ወይም እኅቶቻችን ምግብ እንዲያበስሉልን፣ እንጨት እንዲሰቅሉልንና ውኃ እንዲቀዱልን፣ ወዘተ . . . እንጠብቃለን:: ብዙዎቻችን ሌሎች የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንደሚያደርጉልን የመጠበቅ አስተሳሰብን አዳብረናል:: እንዲህ ያለውን የሕይወት አመለካከት እስካልሰበርን ድረስ፣ አገልጋይ መሪዎች ልንሆን አንችልም:: አንድ ሰው፣ «ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርግልኛለች ብለህ አትጠይቅ፤ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ እችላለሁ ብለህ ጠይቅ» ብሏል:: ያ ራስን መሥዋዕት የማድረግ መሠረት ነው፤ ያ የአገልጋይ መሪነት መሠረት ነው::

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ባሕላችን መጀመሪያ ለእኛ ከዚያ ለሌሎች እንድናስብ የሚያበረታታባቸውን መንገዶች ዘርዝር:: ለ) እውነተኛ አመራር ራስን መሥዋዕት ከማድረግ የሚመነጭባቸውን መንገዶች ዘርዝር:: ጥሩ መሪ ሌሎችን ለማገልገል መተው ያለበት ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) እግዚአብሔርንና ሌሎችን ለማገልገል ለራስህ መሞት የተማርክባቸውን



መንገዶች ዘርዝር:: በዚህ የሕይወትህ ክፍል ልታድግ የምትችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር::

## ሦስተኛ ቀን፡- ለመንፈሳዊ አመራር የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 5)

### ስኬታማ ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት፡- ከመሪው ውስጣዊ ሕይወት የሚመነጩ ባሕርያት (ክፍል 2)

የመሪው ባሕሪ እንዴት እንደሚመራ ቅርጽ ያስይዘዋል:: በመሪነት ከመመረጣችን በፊት ስኬታማ ለሆነ የመሪነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ መንፈሳዊ ባሕርያት ብውስጣችን ሊፈጠሩ ይገባል:: ትናንትና በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑና በመሪው ሕይወት ሊኖሩ ስለሚገባቸው ባሕርያት ማጥናት ጀምረናል:: ዛሬም ስለ መሪው ውስጣዊ ሕይወት ባሕርያት የጀመርነውን ጥናት እንቀጥላለን::

### 6. ስሜታችን፣ ሌሎች ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ከሚቆጣጠሩን ይልቅ ለራሳችን ኃላፊነትን መውሰድ::

መሪ ሊማር ከሚገባቸው መሠረታዊ ባሕርያት አንዱ ለራሱ ሕይወት ኃላፊነትን መውሰድ ነው:: በብዙዎቹ ባህሎቻችን አባቶቻችን ላስረከቡን ነገር «እስረኞች» እንደ ሆንን ተምረናል:: ሁሉ ነገር ወደ እኛ የመጣው በ«ዕድል» ወይም በባሕላችን ስለሆነ፣ ያለንበትን ሁኔታ መቀየር አንችልም:: የተወለድነው ከድሃ ቤተሰብ ነው፣ ስለዚህ ሀብታም የመሆን ተስፋ የለንም:: «አባቴ በበሬ ያርስ ስለ ነበረ፣ እኔም በበሬ ማረስ አለብኝ::» «ቁጡ የሆንኩት አባቴ ይቆጣ ስለ ነበረ ነው::» «ባሕሉ ሴት ልጅን ማስገረዝ ጥሩ ነው ስለሚል፣ ሴት ልጆቼን ማስገረዝ አለብኝ::» ወዘተ. . . እንላለን:: ብዙዎቻችን እኛ ስላለንበት ሁኔታ ሌሎችን ተጠያቂ እያደረግን

እንኖራለን፡፡ «የመዘምራን ቡድን ውስጥ ያልገባሁት አባቴ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ስላልሆነ ነው፡፡» «አገልግሎት ሊኖረኝ ያልቻለው ሽማግሌዎች የምሠራው ሥራ ስላልሰጡኝ ነው፡፡» ያለንበት ሁኔታና ሌሎች እንዲቆጣጠሩን እስከ ፈቀድን ድረስ፣ ማደግ አንችልም፡፡ ስላለንበት ሁኔታ ሌሎችን ተጠያቂ እስካደረግን ድረስ፣ አናድግም፡፡ መሪነት ነገሮችን ለመለወጥ ባሉበት ሁኔታ ከመቀበል ይልቅ ችግሮችን መወጣት እንደ ሆነ ካልተረዳን በቀር፣ ሁኔታዎችን መለወጥ አንችልም፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር የሕይወታችን ባለቤት እንድንሆንና ለውጥ እንድናመጣ፣ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ፣ ችሎታን ሰጥቶናል፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን እንዴት እንደምናምንና እንደምንሠራ ምርጫን የመውሰድ ችሎታን ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን እንድንለወጥ፣ በተለየ መንገድ ማመንና በተለየ መንገድ መሥራትን ለመምረጥ ቁርጠኝነትን ማሳየት አለብን፡፡

ሀ. እንደ ሁኔታው በሚሆኑ ሰዎችና ያሉትን ሁኔታ ለመለወጥ በሚወስኑ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት፡- ሁለት ዓይነት ሰዎች እሉ፡፡ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ለመሥራት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ በሴትነታቸው፣ በድኅነታቸው፣ ወይም ባለመማራቸው የተጠመዱ ይመስላቸዋል፡፡ ያንን ለመለወጥ ምንም የሚያደርጉት ነገር የለም፡፡ «ስፈጠርም እንዲሁ ነው፡፡ ልቀይረው አልችልም» ብለው ያስባሉ፡፡ ሁለተኛው ዓይነት ሰዎች ለውጥ ለማምጣት ራሳቸውንና ሁኔታዎችን የሚቆጣጠሩ ናቸው፡፡ «ድሃ ልሆን እችላለሁ፣ ነገር ግን ይህንንና ያንን በማድረግ እለወጣለሁ፡፡» «እኔ ሴት ነኝ፣ ያለሁበት ባሕል አያከብረኝም፡፡ ነገር ግን ይህንን በማድረግ ሕይወቴ የተሻለ እንዲሆን መለወጥ እችላለሁ» ይላሉ፡፡ ነገሮችን የምንገልጥበት መንገድ የራሳችንን ሕይወት በባለቤትነት መቀበላችንን ወይም ሁኔታዎችና ሰዎች እንዲነዱን የምናሳይበት መንገድ ነው፡፡ የሚከተለውን ለሕይወት የሚሰጡ ሁለቱን ምላሾች የሚያነጻጽረውን ሠንጠረዥ እስተውል፡፡



| ባለበት የሚረግጥ ሰው | ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር ሰው |
| --- | --- |
| «ድሃ ነኝ፡፡ ምንም ላደርግ አልችልም፡፡» | «ድሃ ልሆን እችላለሁ፣ ነገር ግን ሕይወቴን የማሻሽልባቸውን አማራጮች እፈልጋለሁ፡፡» |
| «ሁልጊዜ እርፍጄ እመጣለሁ፡፡ በቃ እኔ እንዲህ ነኝ፣ መለወጥ እልችልም፡፡» | «ባሕሪዬን ለመለወጥ የተለየ አመለካከትን እመርጣለሁ፡፡ ስለዚህ በሰዓቱ መምጣትን እማራለሁ፡፡» |
| «እገሌና እገሌ ስለ ሰደቡኝ ተናድጃለሁ፡፡ እኔን የሚጐዳ ነገር ስላደረጉ ምንም ልረዳቸው አልችልም፡፡» | «ስሜቴንና እስተሳሰቤን እንዲቆጣጠሩ እልፈቅድላቸውም፡፡ ምርጥ የሆነውን ነገር የማደርገው እነርሱ ያደረጉትን ስለ ወደድኩት ላይሆን፣ ኢየሱስን ለመከተልና ምርጥ የሆነውን ነገር ለማድረግ ስለ መረጥኩ ነው፡፡» |
| «የምናመልክበትን መንገድ መለወጥ አይፈቅዱልኝም፡፡ ሽማግሌዎቻችንን መለወጥ አንችልም፡፡» | «በተለየ መንገድ ማምለክ እንደሚጠቅም እንዲረዱ እንዴት እድርጌ ነው እስተላለባቸውን የምቀይረው?» |
| «ያንን ማድረግ አልችልም፡፡ ያ በጣም እስቸጋሪ ነው፡፡» | «የምፈልገውን ሁሉ ማድረግ አልችል ይሆናል፣ ነገር ግን ሁኔታውን ለመለወጥ የምችለውን እደርጋለሁ፡፡» |
| «ባሕሌ እድርግ የሚለኝን ሁሉ ማድረግ አለብኝ፡፡» | «እግዚአብሔር እንዳደርገው ይፈልጋል ብዬ የማምነውን እና ለእኔና ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅመውን አደርጋለሁ፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ባሕሌን እለውጣለሁ፡፡» |
| «ሽማግሌዎቹ ብቻ ቢቀየሩ ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ የተ ሻለች ትሆን ነበር፡፡» | «እነርሱ እስከሚለወጡ ከምጠብቅ ይልቅ፣ ነገሮችን ለማሻሻል የምችለውን አደርጋለሁ፡፡» |

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች እንዴት ባሰው ሁኔታ መቀጠል እንደሚፈልጉና ሁኔታዎቻቸውን ከመቀየር ይልቅ ስላሉበት ሁኔታ ሌሎችን ተጠያቂ ስለሚያደርጉበት ሁኔታ ተጨማሪ ምሳሌዎችን ዘርዝር። ለ) ሁኔታዎቻቸውን መቀየር የሚፈልጉ ሰዎች ለእነዚያ ሁኔታዎች ከሚሰጧቸው ምላሾች ጋር አነጻጽራቸው።

ለ. በሕይወታችን የሚመጣው ስኬት የሚወሰነው ከሁኔታዎች ይልቅ እኛ ስለ ሁኔታዎቹ ባለን አመለካከት ነው። አንድ መጋቢ በአንድ ወቅት *«ብዙ በኖርኩ ቁጥር ሕይወት 10 በመቶ በእኛ ላይ የሆነብን ነገር ሲሆን፣ 90 በመቶው ደግሞ እኛ ለዛ ነገር ምላሽ የምንሰጥበት ሁኔታ ነው»* ሲል ተናግሯል። እንደ መሪ ስኬታችን የሚወሰነው 10 % በችሎታችንና በሁኔታዎች፣ 90 % ደግሞ በአመለካከታችን ነው። በሰፊ ሁኔታ፣ ስኬታማ መንፈሳዊ መሪ መሆናችን ከትምህርታችንና ለአገልግሎታችን በመሠልጠናችን ወይም በመንፈሳዊነታችን ከሚወሰን ይልቅ፣ በአመለካከታችንና ይወሰናል። መጋቢው ግን እንዲህ ጽፏል፣ *«በጣም አስፈላጊውና በየዕለቱ የምወስነው በጣም አስፈላጊ ነገር የአስተሳሰብ ምርጫዬ እንደ ሆነ እምናለሁ። ከኋላ ታሪኬ፣ ከትምህርቴ፣ ከገንዘቤ፣ ከስኬቴና ከውድቀቴ፣ ከዝናዬ ወይም ከሥቃዬ፣ ሌሎች ስለ እኔ ከሚያወሩትና ከሚያስቡት ነገር፣ ከሁኔታዬ ወይም ከሥልጣኔ ሁሉ በላይ አስፈላጊ ነው። ወደፊት እንድራመድ ወይም እድገቴን ሽባ የሚያደርገው አመለካከቴ ነው። አመለካከቴ ትክክል ከሆነ፣ የሚያግደኝ ከፍታ፣ ጥልቅ የሆነ ሸለቆ፣ በጣም የራቀ ሕልም፣ ወይም የሚከብደኝ ፈተና አይኖርም።»*

አንድ ሰው ታላቅ መሆኑ የሚወሰነው ያን ያህል ሰውዬው ሊቆጣጠረው በማይችለው ሁኔታዎች ሳይሆን፣ ለእነዚያ ክስተቶች ያለን አመለካከት ነው። አንድ ሽባ ሆኖ የተወለደ ሰው በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ ምንም ማድረግ እንደማይችል በጣም እያማረረ ሊሰምን ይችላል። ሌላ ልክ እንደ እርሱ ሽባ ሆኖ የተወለደ ሰው ግን ራሱን ተመልክቶ፣ «ባለሁበት ሁኔታ ምን



ማድረግ እችላለሁ?» ብሎ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድና ጠንክሮ በማጥናት ጥሩ ውጤትና ጥሩ ሥራ ያገኛል። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የአመለካከታቸው ልዩነት ነው። አንደኛው «እኔ ምንም ነገር ማድረግ አልችልም፣» ሲል፣ ሌላኛው ደግሞ «የሚገድበኝ ነገር ቢኖርም፣ ብዙ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ» ብሎ ይላል። አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ብዙ ነገር ማድረግ ያልቻሉት ባህላቸው ስለሚከለክላቸው እንደ ሆነ ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ነገር ግን ጠንክረው በመሥራት አስፈላጊ የሆኑ ትልልቅ ኃላፊነቶችን የያዙ ሴቶች አሉ። ያንን እንዴት ሊያደርጉ ቻሉ? ሰዎች ሴቶች ሊጫወቱ ይችላሉ ብለው የሚያስቡት ሚና እነርሱ ሊያደርጉት የሚችሉትን እንደይገድብባቸው ይቃወሙታል። የራሳቸውን ኃላፊነት ወስደው ችግሩን ለመወጣት የሚሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተመራቂዎች ብዙ ጊዜ፣ «ሽማግሌዎች የምሠራው ነገር አልሰጡኝም። የአገልግሎት ቦታ ለማግኘት እየጸለይኩ ነው» ሲሉ እንሰማለን። ነገር ግን የራሱን ሕይወት በባለቤትነት የሚመራ ሰው፣ «ማንን ልረዳ እችላለሁ?» ደቀ መዛሙርት መሆን የሚገባቸውን አዳዲስ አማኞች አይቶ ጊዜውን እነርሱን በማስተማር ማሳለፍ ይጀምራል። ወይም አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አይቶ በመቀላቀል፣ ውጤታማ በሆነ መልኩ መምራት ይጀምራል። ሽማግሌዎች ሊከለክሉንና ሊያቆሙን የማይችሉባቸው በሺህ የሚቆጠሩ አገልግሎቶች አሉ። ችግራችን ልንሰውጣቸው የምንችላቸውን ነገሮች በባለቤትነት አለመያዛችን ነው። አስገራሚው ነገር አገልግሎታችንን በባለቤትነት ስንይዝ፣ ሰዎች ያዩናል፣ በመጨረሻም ሽማግሌዎች በመጀመሪያ የተመኘነውን አገልግሎት ይሰጡናል።

ሐ. ሰዎች በሕይወት ላይ ያላቸው ስኬት ሁኔታዎችን በባለቤትነት በመያዛቸውና ባለመያዛቸው ይወሰናል። በሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ውስጥ ከመውደቅ ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ

ራሳችንን መቆጣጠር የምንችልባቸውን ልዩ ልዩ የሕይወታችን ክፍሎች እንመልከት፡፡

1) የግል ሕይወታችንንና አስተሳሰባችንን መቆጣጠር፡፡ ሁሉም መንፈሳዊ ዕድገቶች የሚመጡት ኑሮአችንን በባለቤትነት ስንቆጣጠር ነው፡፡ የጸሎት ሰው መሆን እንፈልጋለን? ብዙ ሰው በሚኖርበት ቤት ስለምኖር መጸለይ አልችልም፣ ወይም በጣም ሥራ ይበዛብኛል ብሎ መነጫነጭ አይጠቅመንም፡፡ መንፈሳዊ ሕይወቱን በባለቤትነት የሚመራ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የሚገናኝበትና ቃሉን የሚያጠናበት ጊዜና ቦታ ይፈልጋል፡፡ አንዳንዶች የጥሞና ጊዜ ለማግኘት ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ይነሣሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ከቤታቸው አጠገብ ትንሽ ጎጆ በመሥራት በጸሎት ሰዓት ልጆቻቸው ወደዚያች ጐጆ እንዳይመጡ ያዝዛሉ፡፡ በመንፈሳዊ እውቀታችን ለማደግ የሚረዱን መጽሐፎች ያስፈልጉናል? በጣም ድሃ ነን ብለን መማረር ምንም አያመጣልንም፡፡ ይልቁንም፣ ገንዘብ ማጠራቀም የምንችልበትን መንገድ እናፈላልጋለን፡፡ ገበያ ስንወጣ ሻይ መጠጣት እናቆማለን፡፡ ወይም መሬታችንን ይበልጥ እንዲያመርት ጠንክረን እንሠራለን፡፡ በጣም አስፈላጊ ነው ብለን ለምናስበው ነገር ሁሉ ገንዘብ ማግኘት የምንችልባቸው መንገዶች አሉ፡፡ የእኛ ችግር የሚመጣው ሕይወታችንን ባላመቆጣጠራችንና አስፈላጊ ለሆነው ነገር ገንዘባችንን በጥበብ ባለመጠቀማችን ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ስሜታችንንና አስተሳሰባችንን እንቆጣጠራለን፡፡ አንድ ሰው እኛን የሚሳደብ ነገር ሲናገር ቁጣና ምሬት ይሰማናል? በሌሊትስ ይህ ነገር እንቅልፍ ይነሳናል? በሁኔታዎች ቁጥጥር ሥር ከሆንን፣ ስሜታችንን እንዲቆጣጠሩ እንፈቅድላቸዋለን፡፡ ያለ እኛ ፈቃድ ማንም ሰው ሊያናድደን አይችልም፡፡ ቁጣና ምሬት የሚሰማን ሁኔታዎችና የሰዎች ሥራ ስሜታችንን እንዲነካ ስንፈቀድለት ነው፡፡ ያንን በማድረጋችን እኛን ሁለት ጊዜ እንዲጐዱን እንፈቅድላቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ እኛን



የሚጐዳ ነገር በማድረጋቸው ይጐዱናል፡፡ ስንቆጣም እኛን መጐዳታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ አንድ ጸሐፊ «የሚጐዳን የሆነው ነገር ሳይሆን፣ ነገር ግን ለሆነው ነገር የምንሰጠው ምላሽ ነው» ብሏል፡፡ ስሜቱን የሚቆጣጠር ሰው ሰዎች ስሕተት እንደ ሠሩ አይክድም፡፡ ነገር ግን ሁኔታዎችና ሌሎች የሚያደርጉት ነገር እርሱን በማስመረር እንዲጐዱት፣ እንቅልፉን እንዲወስዱበት፣ ወዘተ. . . አይፈቅድም፡፡ ጳውሎስ ለሁኔታዎች ያለውን አመለካከት በፊልጵ. 4:11-12 ተመልከት፣ «ይህን የምለው ስለ ቸገረኝ አይደለም፤ ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ፡፡ ማጣትን ዐውቃለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቃለሁ፡፡ ብጠግብም ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትንም ምስጢር ተረድቻለሁ፡፡» ጳውሎስ መርዳት ሊገባቸው ባልረዱት ቤተ ክርስቲያናት ላይ ወይም እስር ቤት በመግባቱ ሊያማርር ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁኔዎች እንዲቆጣጠሩት አልፈቀደም፡፡ ይልቁንም፣ ጳውሎስ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት ወሰኖ ነበር፡፡ እናም ሁኔታዎችን ሊቋቋምበት የሚችለውን ጥንካሬ ለማግኘት በቃኝ ማለትንና በእግዚአብሔር ማመንን ተማረ፡፡

በሁኔታዎች የሚነዳ ሰው ግን አብዛኛውን ጊዜ በስሜቱ ይመራል፡፡ የእርሱን ደስታ ወይም ኀዘን፣ ሥራውን ይውደደው አይውደደው የሚቆጣጠረው ስሜቱ ነው፡፡ የራሱን ሕይወት በባለቤትነት የሚቆጣጠር ሰው በምርጫው ይኖራል፡፡ ሁኔታዎች ጥሩ ወይም መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ሥራው ደስ የሚል ወይም የማይል ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁኔዎች ወደ ተሻለ ሁኔታ እንዲቀየሩ በኑሮውና በሥራው ለመደሰት ይወስናል፡፡ የጐዱት ሰዎች ዳግም መጥሮ ነገር እንዳያደርጉበት ከእነርሱ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስተካከል ይወስናል፡፡ የእርሱን ምክሮች ይቀበሉ ዘንድ፣ ከሽማግሌዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል ይጥራል፡፡

2) ማኅበራዊ ሁኔታዎቻችንን መቆጣጠር፡፡ በዚህ ዘመን

እንኳን ብዙ ጎሳዎች ስላሉባቸው ችግሮች ሌሎች ጎሣዎችን ይከስሳሉ። «ያ ጎሣ የዛሬ 100 ዓመት ተዋግቶ ባያሸንፈን ኖሮ ዛሬ በጥሩ ሁኔታ ውስጥ እንሆን ነበር» ብለው ያማርራሉ። ወይም «የቤተ ክርስቲያኒቱ ጽ/ቤት እንዲህና እንዲያ ባያደርግ ኖሮ፣ እውራጃችን ወደ ፊት ይራመድ ነበር» ብለው ያማርራሉ። ጎሣዎችና የአውራጃ ቤተ ክርስቲያናት ስለ ደረሰባቸው ነገር ማማረራቸውን እስካላቆሙ ድረስ፣ ሁኔታዎችን ከመቆጣጠር ይልቅ ሁኔታዎች ይቆጣጠሯቸዋል። የራሱን ሕይወት መቆጣጠር የተማረ ሰው ሁልጊዜም የሚያድግበትን መንገድ ይፈልጋል። እርሱ ባለበት ቀጠና ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ስኬታማ ባለመሆኗ ወይም ዋናው ቢሮ ለቤተ ክርስቲያን በቂ በጀት ሳይመደብ በመቅረቱ ከመነጫነጭ ይልቅ፣ ስኬታማ መሪ ሁልጊዜ «ባለችን ነገር ምን ማድረግ እችላለሁ? ሰዎች በእምነታቸው ያድጉና ወንጌልን አሁን ከደረስንበት አንሥተው እንዲያሰራጩ እግዚአብሔር በሰጠን ነገር ምን ዓይነት ለውጥ ማምጣት እንችላለን?» ብሎ ነው የሚያስበው።

ይኸው ተመሳሳይ አመለካከት በባሕላችን መጠመዳችን ወይም እንዳይቆጣጠረን ለማድረግ ስንል ባሕላችንን መቀየራችን ላይ ተጽዕኖ ያመጣል። ለሜታዊ ገበሬ «ሕባቴ በአንድ በሬ ያርስ ነበር። ስለዚህ የእርሱን መንገድ እከተላለሁ። የተሻለ ነገር አላውቅም፣» ይላል። የራሱን ሕይወት በባለቤትነት የሚቆጣጠር ገበሬ ግን፣ «እባቴ በዚህ መንገድ ማረስን አስተማረኝ። ነገር ግን ያንን ማሻሻል የሚቻልበት መንገድ ካለ እያለሁ? በአንድ ማረሻ ከማረስ ይልቅ በሁለት ማረሻ ማረስ የሚቻልበት መንገድ ይኖር ይሆን?» ይላል። ወይም አንዲት ሚስት፣ « በእኛ ባሕል፣ የሴቶች ደረጃ ዝቅተኛ ነው። ለትምህርት የሚሆን ዕድል ስለሌላቸው ሁልጊዜ ይሠራሉ። እንዴት አድርጌ ነው የባሌን አመለካከት የምለውጠው? እንዴት አድርጌ ነው የሴት ልጆቼን ሕይወት የምለውጠው?» ብላ ልታስብ ትችላለች።

3) *ሥራችንን መቆጣጠር*። ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ



ትምህርት ቤት፣ ተመራቂዎች ከትምህርት ቤት ሲመረቁ የኃላፊነት ቦታ ስላልተሰጣቸው ተበሳጭተው ይቆርጣሉ። አገልግሎት ያጡት ውጤታማ ባልሆነው የሽማግሌዎች አሠራር የተነሣ እንደ ሆነ ወይም ቤተ ክርስቲያን ደመወዝ ልትከፍላቸው ባለመቻሏ የተነሣ እንደ ሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ያ ሕይወቱን በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ ሥር ያደረገ ሰው አስተሳሰብ ነው። የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ ወይም የራሱን ሕይወት የሚቆጣጠርና እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራው ሰው የቤተ ክርበቲያን ሽማግሌዎች ሊከላከሏቸው የማይቻሉ በሺህ የሚቆጠሩ እግዚአብሔርን ልናገለግልባቸው የምንችላቸው መንገዶች እንዳሉ ያውቃል። ስለዚህም የሚያገለግሉባቸውን መንገዶች ይፈልጋሉ። «የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እሆናለሁ ብዬ ጠብቄ ነበር፣ ነገር ግን አልመረጡኝም። የምንከፍልህ ገንዘብ የለንም አሉኝ። ነገር ግን እግዚአብሔር የዚህች ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ እረኛ እንድሆን ጠርቶኛል። ነገር ግን ለመኖር አንድ ነገር ስለሚያስፈልገኝ ልክ ቀን ቀን ድንኳን እየሰፋ ማታ ማታ እንደሚሰብከው ጳውሎስ ሥራ እፈልጋለሁ (የሐዋ. ሥራ 18:3)። እናም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላሳድጋቸው ልረዳቸው የምችላቸውን ሰዎች እፈልጋሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ወይም አሥርም ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱን በእረኝነት በማገልገል እጀምራለሁ።» ይላሉ። በሚገርም ሁኔታ በዚህ መንገድ አንድ ሰው ሕይወቱን በባለቤትነት መምራት ሲጀምር፣ በሚንከባከባቸው ሰዎች ላይ ተጽዕኖ የማምጣት ችሎታው እያደገ ሰዎች ለመንፈሳዊ ነገራቸው የሚቆረቆር እውነተኛ ሰው ሲያገኙ ከአሥር ሰዎች፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ከዚያም ወደ የኅብረት የጸሎት ቡድን እያደገ ይሄዳል። ሽማግሌዎችም ማስተዋል ይጀምራሉ። «አቶ እገሌ የቤተ ክርስቲያናችን መጋቢ እንዲሆን እንፈልጋለን። ሰዎች እንዲያድጉ ጥሩ ሥራ እየሠራ ነው። ከእኛ ጋር ሳይጣላ አብሮን እየሠራ በመሆኑ እናምነዋለን። ለዚህ አገልግሎት ስንት ልንከፍለው ይገባል?» ብለው ይጠያየቃሉ። ነገር ግን ያለበትን ሁኔታ የማይለውጥ ሰው ፈጽሞ ሲያድግና አገልግሎት ሲቀበል

አይችልም፣ ነገር ግን እግዚአብሔርንና ሕዝቡን በብዙ መንገዶች ማገልገል የሚፈልግ ሰው እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት መንገድ ያገኛል፣ በመጨረሻም ሕዝቡ መሪ እንዲሆን ያስነሡታል።

4) ቤተ ክርስቲያንን መቆጣጠር። መሪነት ለውጥ ማምጣት ነው። መሪዎች ባሉበት ሁኔታ መማረራቸውንና ላለማደጋቸው ነገሮችን ተጠያቂ ማድረጋቸውን እስካላቆሙ ድረስ መሪዎች ለውጥ አያመጡም። ለምሳሌ፣ ያለበትን ሁኔታ ለመለወጥ ጥረት የማያደርግ መሪ ቤተ ክርስቲያኒቱ ድሃ በመሆኗ ያማርራል፣ ወይም በወንጌል ሥራ ውስጥ አይሳተፍም፣ ወይም ሰዎች በእምነታቸው አያድጉም። ያለበትን ሁኔታ ተቀብሎ የሚኖር ሰው በልቡ ለውጥ የማይታሰብ ነገር እንደ ሆነ ይናገራል። ወይም ቤተ ክርስቲያን ለላስቸበት ሁኔታ ሌሎችን ተጠያቂ ያደርጋል። «ለምንድን ነው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኗ የማትረዳኝ?» ብሎ ይነጫነጫል። ነገር ግን ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር መሪ፣ «ሰዎች በርትተው እንዲሠሩ እንዴት አድርጌ ነው የሥራ ሥነ ምግባር የምለውጠው? ሰዎች ለእግዚአብሔር በብዛት ገንዘብን እንዲሰጡ ስለ ገንዘባቸው ያላቸውን አመለካከት እንዴት ነው የምለውጠው?» ወይም «ሰዎች በበለጠ ድፍረት እንዲመሰክሩ ምን ማድረግ አለብኝ? ወይም ለወንጌላውያን እንዲሰጡ ወይም በወንጌላዊነት እንዲሰማሩ ምን ማድረግ አለብኝ?» ብሎ ያስባል። እንደዚህ ያለው ዓይነት የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደዚያ ያሉ ሁኔታዎችን የሚለውጡባቸውን የሚያሻሽሉባቸውን መንገዶች ይፈልጋል።

ሁኔታዎችን በቁጥጥር ሥር ማድረግን የተማረ መሪ ችግሮች እንዳሉ ፈጽሞ አይክድም። ነገር ግን፣ «ችግሮች አሉብን።» ማለት ወይም ቤተ ክርስቲያን ስላለችበት ሁኔታ ማማረርን አይፈቅድም። ይልቁንም፣ የሚለው፣ «ይህ ችግር አለብን። ይህንን ችግር ለመወጣት ወይም ነገሮችን ለመቀየር ምን ማድረግ አለብን?» ነው። ለምሳሌ፣ የተለመደው የቤተ ክርስቲያን መሪ ንጭንጭ፣ «የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ገንዘብ የለንም፣»



የሚለው ነው። ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተስፋ በመቁረጥ እጃቸውን አየር ላይ በማወናጨፍ ምንም ነገር አይሞክሩም። ነገር ግን የራሱን ሕይወት በባለቤትት የሚቆጣጠር ሰው ሰዎች ገንዘብ የማይሰጡበትን መንገድ ያጠናል። የራሱን ሕይወት የሚቆጣጠር መሪ ሁሉንም አማራጮች በመፈተን ሁኔታዎችን የሚቀይር ውሳኔ ይወስዳል። የሁኔታዎች እስረኛ መሆንን እምቢ ይላል።

> 24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከላይ በተጠቀሱት አራት ሁኔታዎች ውስጥ ሁኔታዎችን መቀየር የማይፈልግ ሰውና ሕይወቱን መቀየር የሚፈልግ ሰው የሚሰጧቸው ምላሾች እንዴት እንደሚለያዩ ሁለት ማብራሪያዎችን ስጥ። ለ) የተለያዩት ምላሾች ምን የተለያዩ ውጤቶችን እንደሚያመጡ አብራራ።

መ. በተለያዩ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ አንድ ሐሪ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ፡- የእኛ ሁኔታ ከሦስቱ በአንዱ ውስጥ ነው።

<u>አንደኛ፣</u> <u>በቀጥታ የምንቆጣጠራቸው</u> ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ወይም ላለመሄድ ሙሉ ቁጥጥር አለን። ወይም ደግሞ አሁን በያዝነው ሥራ ላይ በመቆየት አለመቆየታችን ላይም ሙሉ ቁጥጥር አለን። ወይም በአንድ ሰው ላይ ለመቆጣት ወይም ላለመቆጣት ራሳችንን መቆጣጠር እንችላለን። ካልተማርን፣ ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን። አንድ መሪ ሌሎች ሁኔታዎች ከሚቆጣጠሩት ይልቅ የራሱን ሕይወት ተመልክቶ በቀጥታ መቆጣጠር አለበት። ይህ በቀላሉ ተጽዕኖ ሊያደርግበትና ሊለውጠው የሚችለው የሕይወት ክፍል ነው።

<u>ሁለተኛ፣</u> <u>ተጽዕኖ</u> ልናመጣባቸው፣ ነገር ግን ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ሁኔታዎችም አሉ። ለምሳሌ፣ ሽማግሌዎቻችንን ወይም የኢኮኖሚ ሁኔታችንን መቆጣጠር አንችልም። ነገር ግን እነርሱን የምናይበትን መንገድ በመቀየርና በመቀራረብ ሽማግሌዎች በእኛ ላይ ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ማምጣት እንችላለን። ወይም ሰዎች በጣም ጠንካራና ታማኝ ሠራተኛ መሆናችንን አይተው የተሻለ ሥራ እንዲሰጡን ጠንክረን በመሥራት የኢኮኖሚ

አቅማችን ላይ ተጽዕኖ ማምጣት እንችላን።

<u>ሦስተኛ፡-</u> ልንቀይራቸው የማንችላቸው ሁኔታዎችም ደግም አሉ። ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር ስለ እነዚያ ሁኔታዎች ያለንን አመለካከት መቀየር ነው። ሽባ ሆነን ከተወለድን፣ ወይም የአስም በሽታ ካለብን፣ ወይም ባለቤታችን ከሞተች፣ ወይም ሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችንን ከወሰደብን፣ ወዘተ . . . እነዚህ ልንቀይራቸው የማንችለው ነገሮች ናቸው ፡ እግዚአብሔር እኛን ያስቀመጠባቸው የሕይወት ሁኔታዎች ናቸው።

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ ሰው በቀጥታ ሊቆጣጠራቸው የሚችላቸውን ሁኔታዎችን ዘርዝር። ለ) አንድ ሰው በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ሊያመጣባቸው የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር። ሐ) አንድ ሰው ሊቆጣጠራቸው የማይችላቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር። መ) ሁኔታውን ለመለወጥ የማይፈልግ ሰው በጠቀስናቸው ሁኔታዎች ውስጥ ምላሹ ምን እንደሚመስል አብራራ። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ሁኔታዎችን ተቆጣጥሮ ለውጥ ማምጣት የሚፈልግ ሰው ምላሽ ምን የሚሆን ይመስልሃል። ሠ) ሁኔታዎችን ለመለወጥ በማይጥር ሰውና ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ለውጥ ማምጣት የሚፈልግ ሰው በሚያመጡት ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ምን ይሆናል? |

ውጤታማ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለእነዚህ ሦስት ሁኔታዎች የሚሰጠው ምላሽ ምን ይሆናል? ሁኔታዎችን ለመለወጥ ጥረት የሚያደርግ ሰው አብዛኛውን ጊዜ በሦስተኛው ሁኔታ ማለትም ምንም ልቆጣጠረው አልችልም በሚለው ላይ ያተኩራል። ማናችንም ታሪክን፣ ያለፈ ነገርን፣ የቤተሰቦቻችንን ድህነት፣ ትምህርት ቤት ለመሄድ ዕድል አለማግኘታችንን፣ ኀሳችን በሌሎች መጨቆኑን፣ ቤተ ክርስቲያናችን በሌላ ቤተ እምነት መወሰዷን፣ ወዘተ. . . መቆጣጠር አንችልም። ግን ሁኔታዎችን ለመለወጥ ጥረት የማያደርጉ ሰዎች እነዚህ ነገሮች ስሜታቸውን እንዲጎዱ ይፈቅዳሉ። እነዚህን ነገሮች በማሰብ ጊዜና ኃይላቸውን ባቃጠሉ ቁጥር፣ ውጤታማነታቸው ይቀንሳል። ሁኔታዎችን



በመቀየር የሚያምን ሰው እነዚህን ሁኔታዎች ሊቀይር እንደማይችል ስለሚረዳ ስለ እነርሱ በማሰብ ጊዜና ኃይሉን አያጠፋም። በልቡ ያለውን ቁጣና ምሬት በሙሉ ለመተው በመወሰን፣ ሊለውጣቸው የሚችላቸውን ነገሮች ማከናወን ይጀምራል።

የራሱን ሕይወት የሚቆጣጠርና የሚለውጥ መሪ ሁልጊዜ የሚያተኩረው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሁኔታዎች ላይ ነው። በእርሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ያሉ ነገሮችን በፍጥነት ይቆጣጠራል። ውጤታማነቱን በሚገድቡ ባሕሪዎችና አመለካከቶች ላይ ይሠራል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆነ፣ በጊዜው ይመጣል። ቀጠሮውን ያከብራል። የሚገባውን ቃል ሁልጊዜ ይፈጽማል። በእርሱ ችሎታ ጥሩ መሪ ሊያደርገው የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል።

ነገር ግን መሪነት በቀዳሚነት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ማምጣት ነው። ያንን በቀጥታ ማድረግ አንችልም። የሌሎች ሰዎችን ባሕሪ መቀየር አንችልም። ሰዎች ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጡ ልናስገድዳቸው አንችልም። ስለዚህ መሪነት በሁኔታዎች ላይ ያለ ማቋረጥ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ማምጣት ነው። አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቅ ነህ እንበል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ቦታ ትፈልጋለህ፣ ነገር ግን ሽማግሌዎች አይሰጡህም። እንዴት አድርገህ ነው በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የምታደርግባቸው? ሽማግሌዎች አድርግ የሚሉህን በሙሉ ያለማንገራገር በፈቃደኝነት ትፈጽማለህ። እንድትመጣ ከፈለጉ፣ ሁልጊዜ በጊዜ ትደርሳለህ። የሆነ የሚሠራ ነገር ከሰጡህ፣ እነርሱ በሚፈልጉት ጊዜ በጥራት ትሠራዋለህ። ሽማግሌዎች ምን ማድረግ እንደሚገባህ እንዲነግሩህ ከመጠበቅ ይልቅ፣ አንተ ወደ እነርሱ ሄደህ ምን ልርዳችሁ? ማለት ይጠበቅብሃል። አንተ ልትቆጣጠራቸው የምትችላቸውን እነዚህን ነገሮች በማድረግ፣ በሽማግሌዎች ላይ ተጽዕኖ ታመጣለህ። የአንተን አመለካከት ካዩ በኋላ፣ የሚበልጥ ኃላፊነት እንዲሰጡህ ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል።

ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿ ደመወዝ የማትከፍል የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነህ እንበል። ከማማረር ይልቅ፣ ከእያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ጋር ያለህን ግንኙነት ለማስተካከል ትወስናለህ። በየእሑዱ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናትን ትጐበኛለህ። ከፕሮግራሙ በኋላ ከሽማግሌዎቹ ጋር የተወሰነ ጊዜ ወስደህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁኔታ በምን ደረጃ ላይ እንዳለና የተረጋገጠባቸውን ችግር ትጠይቃቸዋለህ። አብረሃቸው ጸልይ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚሠሩባቸው ቀናት ሲኖሩ፣ እዛ ተገኝተህ እርዳቸው። ለሚመጣው ዓመት ስላላቸው ግብ ጠይቃቸውና እንዲሁም ዓላማቸውን የሚያሳኩበትን ሀብቶች እፈላልግላቸው። የአውራጃው መሪ እንደ መሆንህ መጠን ልትረዳቸው እንደ ሞከርክ ሲያዩ፣ ልባቸው ይለወጣል። እነርሱም በተራቸው ስለ አውራጃውና ስለ ዕቅድህ፣ እንዲሁም ስላለብህ ችግር መጠየቅ ይጀምራሉ። ከዚያም ያለ በቂ ገንዘብ ለመጪው ዓመት ዕቅዶችን የማስፈጸምን ፈተና ታካፍላቸዋለህ። አሁን አንተን ለመለማት ዝግጁ ከመሆን አልፈው ቤተ ክርስቲያኖቻቸው ለአውራጃዋ ዕቅዶች ገንዘብ እንዲያዋጡ ያበረታታሉ።

### የራሱን ሕይወት የሚቆጣጠር መሪ ሦስት ነገሮችን ያደርጋል:-

ሀ) ራሱን ያነሣሣል። ሰዎች ነገሮችን እንዲጀምሩ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ራሱ ይጀምራል።

ለ) በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ስሕተት ላይ አያተኩርም። ስሕተት ልንለውጠው የማንችለው ነገር ነው። ስሕተት ታሪክ ነው፣ ታሪክ ደግሞ ልንለውጠው የማንችለው ነገር ነው። ነገር ግን የራሱን ሕይወትና አገልግሎት መቆጣጠር የሚፈልግ መሪ ወደ ስሕተቱ ተመልክቶ፣ «ዳግም ስሕተት እንዳልሠራ እንዴት አድርጌ ነው በተለየና በተሻለ መንገድ የምሠራው?» ብሎ ይጠይቃል። ስሕተት እንዴት ተሠራ ብሎ የማይጠይቅ ሰው ሁልጊዜ በተደጋጋሚ ያንኑ ስሕተት ይሠራል። ነገር ግን የራሱን ሕይወትና



አገልግሎት የሚገመግም መሪ ከስሕተቱ የሚማር መሪ ነው። አንድን ሰው ወይም ነገር ተጠያቂ ማድረጋችንን እስካላቆምን ድረስ፣ ማደግ አንችልም፣ ስሕተታችንም ይቀጥላል።

ሐ) ሰዎችን ስንመራ እናደርገዋለን ባሉት ነገር ላይ በኃላፊነት ካልጠየቅናቸው ወይም ሰዎች የውሳኔያቸውን መዘዝ እንዲቀበሉ ካላስተማርናቸው በስተቀር እንዲያድጉ አንረዳቸውም። ይህንን ስናደርግ፣ በራሳቸው ሕይወት ላይ ኃላፊነት መውሰድ እንደሌለባቸው እያስተማርናቸው ነው። በርትተው እንዳይሠሩ፣ በሰዓቱ እንዳይገኙ፣ ወይም ጥሩ ሥራ እንዳይሠሩ እያስተማርናቸው ነው። የሚፈጠረውን ችግር ሁልጊዜ ሌላ ሰው ያስተካክልላቸዋል። ነገር ግን ሰዎች እናደርገዋለን ባሉት ነገር ላይ በኃላፊነት የምንጠይቃቸው ከሆነ፣ ወይም ውሳኔያቸው ያመጣውን መዘዝ እንዲቀበሉ ስናደርግ፣ ያን ጊዜ ለሕይወታቸው ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ እናስተምራቸዋለን። ሥራውን ካልሠሩ እድገት አያገኙም። ሥራውን ካልሠሩ፣ በሚቀጥለው ጊዜ ኃላፊነት አይሰጣቸውም። ሰዎች ሁልጊዜ የሚያድጉት ኃላፊነት ስንሰጣቸውና ሥራቸው ለሚያመጣው መዘዝ ተጠያቂ አድርገን ስንይዛቸው ነው።

> 26ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ሕይወትና አስተሳሰብ ከመቀየር ይልቅ ላሉበት ሁኔታ ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግ የሚፈልጉባቸውን መንገዶች ግለጥ። ለ) እመለካከት የስኬታማ አመራር 90% ውን እንዴት እንደሚይዝ አብራራ። ሐ) ማድረግ የምትፈልገውን ነገር የገደበብህ ሁኔታ ካለ አብራራ። በአንተ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ያሉ ልትለውጣቸው የምትችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ነገሮች እንዲሻሻሉ በሁኔታዎች ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽዕኖ ለማምጣት ልታደርጋቸው የምትችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

### 7. የረጅም ጊዜ ግብን ለማሳካት ሲባል ግላዊ ደስታን መተውን መማር።

ሁላችንም ማድረግ የምንፈልጋቸው ነገሮች ሲኖሩ ማድረግ

የማንፈልጋቸውም ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት እወዳለሁ፣ ነገር ግን ሰዎችን በማነጋገር ረጅም ጊዜ ማጥፋት አልወድም። ደብዳቤ መጻፍ ደስ ይለኛል፣ ነገር ግን ዶሴዎችን በፋይል ማስቀመጫ ውስጥ መደርደር ደስ አይለኝም። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሌሎችን መጐብኘት ይወድዳሉ፣ ነገር ግን መጻፍና ማጥናት አይወድዱም።

በአገልግሎታችን ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ ዓይነት መሪ ለመሆን፣ ምኞታችንን፣ የምንወደውንና የማንወደውን ነገር መቆጣጠርን መማር አለብን። የምንወደውን ነገር ብቻ ሳይሆን የማንወደውንም ነገር ማድረግን መማር አለብን። ጥሩ በሆነውና በምንወደው ነገር ከምንወሰድ ይልቅ፣ ምርጥ የሆነውን ነገር መወሰንን ልንማር ይገባናል። በፊልጵ. 1:9-11 ላይ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞች ምርጥ የሆነውን ነገር እንዲያውቁ ጸልዮላቸዋል። የተሻለውን ሲያውቁና ለእግዚአብሔር ክብር ሲያደርጉት፣ በሕይወታቸው ትልቅ ደስታ ይሰማቸዋል። የምርጥ ነገር ጠላት ሁልጊዜ መጥፎ ብቻ ሳይሆን፣ ጥሩ ነገርም ነው ይባላል። አብዛኛውን ጊዜአችንን ጥሩ የምንለውን ነገር በመሥራት እንጠመዳለን፣ ነገር ግን የምንሠራው ምርጥና እጅግ አስፈላጊው ነገር ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር እንድንሠራ የሚፈልገው ጥሩውን ብቻ ሳይሆን፣ እጅግ አስፈላጊውን ነገር ነው።

በሕይወታችን ሁሉ «ጥሩውንና» «ምርጡን» ለመለየት ስንታገል እንኖራለን። ጠዋት አርፍዶ መነሣት ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ለመገናኘትና ቃሉን ለማንበብ ማልዶ መነሣት ደግሞ «ምርጥ» ነው። «የተሻለውን» ካልመረጥን በመንፈሳዊ ሕይወታችን አናድግም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መሪዎች «ጥሩ» የሆነውን ከጓደኞቻችን ጋር ሻይ መጠጣትን «ምርጥ» ከሆነው እግዚአብሔር የሰጠንን ሥራ ከመሥራት ካስበለጥን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውጤታማ አንሆንም። ወይም ትኩረታችን «ጥሩ» በሆኑት እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ፣ የመዘምራን ልብስና



የሙዚቃ መሣሪዎች ላይ አርፎ፣ «ምርጥ» በሆኑት እንደ ወንጌል ላልደረሳቸው ኢትዮጵያውያንና ለዓለም ወንጌልን ማሰራጨትና የቤተ ክርስቲያን አባላት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ማድረግ ላይ ካላተኮርን ውጤታማ አንሆንም።

በዘመናችን፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጥሩ ነገሮችን በፍጥነት ይፈልጋሉ። ስኬታማና ታዋቂ መሆን ወይም በፍጥነት ምቹ ኑሮ ለመኖር ይፈልጋሉ። አንዳንድ መሪዎች ጥሩ የሆኑ ውሳኔዎችን ይወስዳሉ። ነገር ግን ውሳኔአቸው ለእነርሱም ሆነ ለእግዚአብሔር መንግሥት ምርጥ አይደለም። ጥሩ የሆነውን ነገር የማድረግ ፍላጐት ስላላቸው፣ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ትኩረታቸውን የሚያደርጉት ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል እውቀታቸው እንዲያድጉ በማድረግ ላይ ሳይሆን አስደሳች በሆኑ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ላይ ነው። ሌሎች ደግሞ በቅንነት ራስን መሥዋዕት ከማድረግ የሚመጣ ክብርን ከመፈለግ ይልቅ፣ ወደ ትምህርት ቤት ገብተው ዲግሪያቸውን በመያዝ ወዲያውኑ ክብር ማግኘት ይፈልጋሉ። አንዳንዶቹ መሪዎች አሁኑኑ ምቹታማ የሆነ ኑሮን ለመሙላት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ክፍያ እንድትከፍላቸው ይጠይቃሉ። የቤተ ክርስቲያን የመክፈል አቅም የሚፈቅደውን ክፍያ ከመቀበልና የሚፈልጉትን አቅማቸው የፈቀደውን ነገር ለመግዛት በጥንቃቄ ገንዘብ ከማጠራቀም ይልቅ፣ አንዳንድ አገልጋዮች ወዲውኑ እነዚህን ጥቅሞች ሁሉ ይፈልጋሉ። ሰይጣን ምርጥ በሆኑ ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቅንነትና መሥዋዕትነትን በመክፈል እንዳያገለግሉ የሕይወትን መልካም ነገሮች ይጠቀማል። በማቴ. 6:33 ላይ፣ ኢየሱስ «ምርጡን» እንድንፈልግ ነግሮናል። ምርጥ የምንለው ነገር ለእግዚአብሔርና ለመንግሥቱ ከፍተኛውን ክብርና ጥቅም የሚያመጣና የጽድቅና የቅድስና ሕይወት መኖር የሚያስችለን ነው። እነዚህ ነገሮች ዘላለማዊ ናቸው። እኛ ብዙ ጊዜ የምንፈልጋቸው ምድራዊ ነገሮች የምርጡ ነገር ጠላት የሆኑ

«ጥሩ» ነገሮች ናቸው፡፡

> **27ኛ ጥያቄ** ሀ) እንዴት አንድ «ጥሩ» የሆነ ነገር «የምርጥ» ነገር ጠላት እንደ ሆነ አስረዳ፡፡ ለ) በምን ዓይነት መንገዶች ነው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምርጥ የሆነ ነገር እያለ ጥሩ የሆነ ነገር የሚመርጡት? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ውጤት ለማስገኘት ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር መተውን መማራቸው አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል?

## 8. ራሳችንን መንከባከብንና ማደጋችንን መቀጠል የመማር ጥቅም፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰውዬ መጥረቢያ ገዝቶ እንጨት ለመፍለጥ ተጠቀመበት፡፡ በመጀመሪያ፣ መጥረቢያው ስል ስለ ነበረ ያለ ብዙ ድካም እንጨቱን መፍለጥ ችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ ስለቱ መደነዝ ጀመረ፡፡ ሰውየው አንዳንዴ በመጥረቢያው ድንጋይ ስለሚመታ፣ ስለቱ ተቸረቸፈ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ዝናብ ላይ ስለሚረሳው መጥረቢያው መዛግ ጀመረ፡፡ ወዲያውኑ የመጥረቢያው ስለት በጣም ከመደነዙ የተነሣ እንጨት መፍለጡ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ አንድ ቀን እንጨት እየቆረጠ እያለ፣ የዶለዶመው መጥረቢያ ጫፍ ከእንጨቱ ወልቆ እግሩን ክፉኛ መታው፡፡ እግሩን ለመታከም ወደ ሕክምና ማዕከል መሄድና ለሐኪም በጣም ብዙ ገንዘብ መክፈል ነበረበት፡፡

ይህ ሰውዬ የረሳው ነገር ቢኖር፣ መጥረቢያው ውጤታማ እንዲሆን፣ በየጊዜው መሳል እንዳለበት ነው፡፡ ይህ ለእኛም እውነት ነው፡፡ መሪዎች ውጤታማ ሆነው ለመቀጠል፣ በየጊዜው ራሳቸውን «መሳል» አለባቸው፡፡ ብዙ መሪዎች በሕይወታቸው ይህንን እውነት ይረሳሉ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ወይም ከዓለማዊ ትምህርት ቤት ተመርቀው አገልግሎት ይጀምራሉ፡፡ የተወሰነ የብቃት ደረጃ ላይ በመድረሳቸው ከዚህ በላይ ማደግ ያለባቸው አይመስላቸውም፡፡ ፈጥነው ይደንዛሉ፣ አገልግሎታቸውም እንደ በፊቱ ውጤታማ አይሆንም፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉ ሰዎች ለቤተ



ክርስቲያን አደጋ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልክ እንደ መጥረቢያ ስለት እንዲኖረንና በአመራራችን ላይ ውጤታማነታችንን ለመጠበቅ ሕይወታችንን መሳል አለብን፡፡ የሚከተሉት መሪዎች ሁልጊዜ ልናሳድጋቸው የሚገቡ የሕይወታችን ክፍሎች ናቸው፡፡

ሀ. የመሪው መንፈሳዊ ሕይወት፡- የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን የምንመራው ከባሕሪያችን፣ ከመንፈሳዊ ብስለታችንና ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ተመሥርተን ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር እያደገ የሚሄድ ግንኙነት ሲኖራቸው ነው ለመምራት የሚያስችል ኃይልና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መምራት እንዳለባቸው የሚያውቁት፡፡ ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለማወቅ ሲል ሥጋውን እየጐሰመ እንደሚያስገዛ ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 9:27)፡፡ ጳውሎስ ኢየሱስን ይበልጥ ለማወቅና በአገልግሎቱ ላይ ይበልጥ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲለማመድ ይጥር ነበር (ፊልጵ. 3:12-14)፡፡ ለሌሎች አማኞች ጳውሉስ ሲጸልይ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው መንፈሳዊ እርምጃቸው እንዲያድጉ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር በመረዳት እንዲያድጉ፣ በእግዚአብሔር ጥበብ እንዲያድጉ፣ በመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያድጉ፣ ወዘተ. . . ጸልዮአል (ኤፌ. 3:14-19)፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪ መንፈሳዊ ሕይወት ያለማቋረጥ ካላደገ መሞት ይጀምራል፣ እናም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአግባቡ የመምራት ኃይልም እየሞተ ይሄዳል፡፡

ለ. የመሪው ምሁራዊ ሕይወት፡- ብዙ ሰዎች አንድ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቅን በምሁራዊ ሕይወታችን ማደግ ያለብን አይመስላቸውም፡፡ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያጠፉት በአገልግሎት ላይ ነው እንጂ አማኞች ላይ ስለ ተጋረጡ ነገሮች በጥልቀት አያስቡም፡፡ አእምሮአችንን ካልተጠቀምን፣ እየደከመ ይሄዳል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነገሮችን የሚያይበትን መንገድ

ሁልጊዜ ማሳደግ የሚፈልግ መሆን አለበት:: ወደ ዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ስብሰባዎች እየሄድን (በኢትዮጵያ ላይ ስለ ተጋረጠው የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ጉዳይ፣ የድህነት ቅነሣ ጉዳይ፣ ወዘተ. . .) ላይና በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ደግሞ (ለምሳሌ:- የአመራር ብቃት፣ ሥነ መለኮታዊ እውነቶች፣ ወዘተ. . . ) መወያየት አለብን:: መረዳታችንን ለመጨመር መጽሐፎችን ማንበብ አለብን:: መሪ ለመማር የግድ ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ስብሰባ መሄድ የለበትም:: መጽሐፎችም በቤታችን ወይም በሚመችን ሰዓት ሰናነብባቸው ያስተምሩናል:: አንድ መሪ በወር ቢያንስ ቢያንስ አንድ መጽሐፍ በተለያዩ ርእሶች ላይ ካላነበበ አእምሮውን እንደሚገባ አላሳደገም ማለት ነው:: ሌላው በምሁራዊ እውቀት የምናድግበት መንገድ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር በልዩ ልዩ ርእሶች ላይ መወያየት፣ መፍትሔዎችን መፈለግ፣ በየራሳችን ፍልስፍናዎች ላይ መከራከር፣ እግዚአብሔር ያስተማራችሁን ነገር እርስ በርስ መወያየት፣ ወዘተ. . . ናቸው:: ስለ አየር ፀባይ፣ ስለ አያንዳንዳችሁ ቤተሰብና ችግር ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉ ችግሮች ብቻ አታውሩ:: ብረት ብረትን እንደሚስለው የአንተ አእምሮ የሌላውን አእምሮ፣ የሌላው አእምሮ ደግሞ የአንተን እንዲስል ፍቀድ (ምሳሌ 27:17)::

ሐ. የመሪው አካላዊ ጤና:- የተሰበረ መጥረቢያ ለምን ይጠቅማል? ወይም ራሱን ባለመንከባከቡ የተነሣ የታመመ መሪ ምን ይጠቅማል? ጳውሎስ ሲናገር አካላችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:19) ብሏል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አገልግሎት ለመፈጸም በአካላችን ነው የሚጠቀመው:: ስለዚህ በአገልግሎታችን ውጤታማ ለመሆን ካስፈለገ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ አካሉን መጠበቅ አለበት:: ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚወፍሩት በብዙ ድግሶች ላይ ስለሚጋበዙና ስብሰባ ተቀምጠው ስለሚውሉ ነው:: ከሚገባው በላይ ክብደት ስንጨምር፣ እንደሚገባን መሥራት፣ ረጅም መንገድ መጓዝ፣



ወይም እንደ በፊቱ ብዙ መሥራት አንችልም:: እንዲያውም፣ ሳይንቲስቶች ከሚገባቸው በላይ የወፈሩ ሰዎች ዝቅተኛ ክብደት ካላቸው ሰዎች በላይ ለበሽታ እንደ ተጋለጡ ደርሰውበታል:: ወፋፍራም ሰዎች በስኳር፣ በደም ግፊት፣ በአልሰር፣ ወዘተ. . . የመያዝ ዕድላቸው የሰፋ ነው:: አካላችን ጤናማ እንዲሆን ለምንበላው ምግብ መጠንና ዓይነት ጥንቃቄ መውሰድ አለብን:: አካላችን ንቁ መሆን አለበት - የአካላችንን ጥንካሬ ለመጠበቅ የእግር ጉዞ ማድረግ ወይም የሆነ ስፖርት መሥራት አለብን::

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ:- ሀ) የመንፈሳዊ መጥረቢያህን ስለት ለመጠበቅ ምን እያደረግህ ነው? ለ) በምሁራዊ አስተሳሰብህ ለማደግ በማድረግ ላይ ያለኸውን ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) የሰውነትህን ቅርጽ ለመጠበቅ ምን እያደረግህ ነው? መ) በአመራርህ ላይ ውጤታማ ለመሆንና ማደግህን ለመቀጠል ምን ዓይነት ነገሮችን በማድረግ ላይ ነህ? |

## 9. በታላቅ ኃይል መሥራት::

እግዚአብሔር በኃይል የሚጠቀምባቸውን ሰዎች አስብ:: እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገር ለመሥራት ያለ የሌለ ኃይላቸውን ተጠቅመው የሚሠሩ ናቸው:: የተለያዩ ዓይነት መሪዎች አሉ:-

ሀ. ብዙ መሪዎች ተቀምጠው ብዙ ያወራሉ:: ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ፣ ነገር ግን ሥራውን ሲጀምሩ አይታይም:: ጉባዔዎችንና ስልት በሚነደፍባቸው ስብሰባዎች ላይ መገኘት፣ ነገሮችን በወረቀት ላይ መጻፍና በቦርድ ስብሰባ ላይ ውሳኔ ማስተላለፍ ደስ ይላቸዋል:: ነገር ግን ሁሉ ነገር የሚቆመው እዚያ ላይ ነው:: ዕቅዱ በወረቀት ላይ ይጻፍ እንጂ ተፈጻሚነት አያገኝም:: እንደዚህ ያሉ መሪዎች መናገር እንጂ መፈጸምን ስለማያውቁ እግዚአብሔር አይጠቀምባቸውም:: ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚፈጽሙት ጥቂት ነው::

ለ. ሌሎች መሪዎች ደግሞ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው

ያውቃሉ፣ እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር መፈጸም ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ጠንክረው አይሠሩም:: ሰዎችን ማነጋገርን ያመርጣሉ፣ ወይም አላስፈላጊ ነገሮች እግዚአብሔር እንዲፈጽሙ የሚፈልገውን ነገር እንዳይፈጽሙ ያግዷቸው ዘንድ ይፈቅዳሉ:: ልክ 11 ሰዓት እንደ ሆነ ሥራቸውን አቁመው ወደ ቤት ይሄዳሉ:: እንዲያ ያለው መሪ ትንሽ ነው የሚሠራው፣ ነገር ግን ብዙ መሥራት ቢፈልግም ጊዜ እንደሌለው ነው የሚናገረው:: እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ለመፈጸም እንዲህ ያለውን መሪ አይጠቀምም::

ሐ. በጣም ጥቂት መሪዎች ብቻ ናቸው ብዙ ኃይል ያላቸው የሚመስሉትና ያንን ኃይላቸውን እግዚአብሔር እንዲፈጽሙለት የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ የሚጠቀሙት:: እንዲህ ያሉ መሪዎች ብዙ ጊዜ ተስፋ የሚቆርጡት ሌሎች መሪዎች በጣም ዝግተኛ በሆነ ፍጥነት በሚወስኑት ውሳኔ ነው:: ሲፈቀድላቸው፣ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ለመፈጸም ሌትና ቀን ይሠራሉ:: ጳውሎስ እንዲህ ያለ ሠራተኛ ነበር:: ቤተ ክርስቲያንን ለማቋቋም «ሌትና ቀን» እንደ ሠራ ይነግረናል (የሐዋ. ሥራ 20-31):: እርሱ በሚያርፍባቸው ስዎች ላይ እንዳከብድባቸውና ለእርሱና ለጢሞቴዎስ መኖሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት አብዛኛውን ጊዜ ቀኑን ድንኳን ይሠፋል:: ማታ ማታ ደግሞ አዳዲስ አማኞችን ያስተምራል (2ኛ ተስ. 3:6-10):: መንፈስ ቅዱስ በአጭር ጊዜ ውስጥም ታላቅ ኃይሉን በማፍሰስ በጳውሎስ ውስጥና በጳውሎስ በኩል ይሠራ ነበር::

ይህ ሦስተኛው ዓይነት መሪ እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል የሚጠቀምበት ነው:: ሁላችንም እግዚአብሔር ምን እንድንሠራለት እንደሚፈልግ ግልጽ አሳብ ቢኖረንና ያንን ለማሳካት ፈቃደኛ ብንሆን እንዴት ግሩም ነበረ! ስለ ሥራው ማውራት ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ተግባር ለመለወጥ መሥራት ይገባል:: እንደዚህ ያለ ኃይል የሌለን መሪዎች በቢሮክራሲ ማነቆ አንድ ውሳኔ ለመወሰን ብዙ



ቀናትና ወራትን እየፈጀን ለመሥራት የሚያስችል ጉልበት ያላቸውን ሰዎች እንዳንገድብ ልንጠነቀቅ ይገባል:: ያንን ካደረግን፣ ተስፋ ቆርጠው ሲያቆሙ ይችላሉ:: በሙሉ ኃይላቸው በመሥራት እግዚአብሔርን እንዳያከብሩ ባለመፍቀዳችን በኃላፊነት እንጠየቃለን:: ይልቅስ፣ መንፈሳዊ ጥበብ እንዳለው የቤተ ክርስቲያን መሪነታችን፣ በእግዚአብሔር ጥበብ ሥራቸው ለእግዚአብሔር ምርጥ የሆነ ክብር እንዲያመጣና ኃይላቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲያውሉ ልንመራቸው ይገባል::

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔርን ለማገልገል ከፍተኛ ኃይል ያለውን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ግለጥ:: እግዚአብሔር በአጭር ጊዜ ውስጥ ምን ያህል ተጠቀመበት? ለ) እንዲህ ያለው ሠራተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚወስዱት በጣም የዘገየ ውሳኔ ምን ያህል ተስፋ ሊቆርጥ እንደሚችል አብራራ:: ሐ) እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ሰው ቢሰጥ፣ የእርሱ ሥራ እግዚአብሔርን የሚያከብርና ለቤተ ክርስቲያንም የሚጠቅም እንዲሆን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በምን መልኩ ሊመሩት ይገባል? |

## 10. በሕይወት ደስ መሰኘት:- ተጫዋች የሆነ ሰው::

ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሳቅ መንፈሳዊ እንዳልሆነ ያስባሉ:: ምን ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግንባራቸውን ቋጥረው (ተኮሳትረው) እንደሚመላለሱ አስተውል:: ነገር ግን በመሪነት ላይ የተጻፉ አብዛኛዎቹ መጻሕፍት በጣም ውጤታማ የሆኑት መሪዎች በኑሮአቸው ደስተኛ የሆኑት እንደ ሆኑ በተደጋጋሚ አስረግጠው ይገልጻሉ:: ተጫዋችና ሳቂታዎች ናቸው:: ምሳሌ 17:22 ላይ «ደስተኛ ልብ ጥሩ መድኃኒት ነው» ይላል:: ሐዋርያው ጳውሎስም «ምንጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» (ፊልጵ. 4:4) ብሎ አዝዟል::

የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆናችን መጠን፣ ሁልጊዜ ከችግሮች ጋር እንጋፈጣለን:: ካልተጠነቀቅንና በሁሉም ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር ካልታመንን ልናገኘው የሚገባንን ደስታ

ልናጣ እንችላለን:: ልባችን ይከብድብንና የአገልግሎቱ ስፋት ከልካችን ያለፈ ይመስለናል::

ደስታም ሆነ ሳቅ ልክ እንደ ጉንፋን ናቸው:: በአካባቢያችን ወዳሉ ሰዎች እናስተላልፋቸዋለን:: ሳቂታና በሕይወቱ ደስተኛ ከሆነ ሰው ጋር የሚሠሩ ሰዎች ሳቂታዎችና በሕይወታቸውም ደስተኞች ናቸው:: ነገር ግን እብዛኛውን ጊዜ በኀዘን ከተቆራመተና ፊቱ ከማይፈታ ቁጡ ሰው ጋር የሚውሉ ሰዎች ልክ እንደ ሰውየው ቁጡ ይሆናሉ:: መሪዎች ሳቂታ መሆናቸው ለሚከተሉት ምክንያቶች ይጠቅማቸዋል:-

ሀ. በየዕለቱ የሚያጋጥሙት ችግሮች ቢኖሩም፣ ሳቅ የመሪውን መንፈስ ያነቃቃል::

ለ. በመሪው ዙሪያ ያሉ ሰዎች ችግር ቢኖርም እንኳን፣ በእግዚአብሔር ደስ እንዲሰኙ ያደርጋል::

ሐ. ሳቅ በመሪነት አብረው የሚሠሩት ሰዎች ደስተኞች እንዲሆኑ ያደርጋል:: በጋራ አብረው ሲስቁም፣ እንዳንድ ጥቃቅን ግላዊ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በጋራ ይፈታሉ::

30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች በመሪዎች ፊት ላይ የደስታ ስሜት ከመጥፋቱ የተነሣ አብሮ መሥራት እንዴት እንዳቃታቸው እንዳየህ ግለጥ:: ለ) እንዴት እግዚአብሔር ሳቂታ ፊት ካላቸው መሪዎች ጋር አብሮ መሥራትን እንዳቀለለና የስብዕና ግጭቶችን እንደ ገደበ እንዳየህ ግለጥ::

31ኛ ጥያቄ:- ለስኬታማ አገልግሎት እነዚህን ስለ ግለሰባዊ ባሕርያት የሚናገሩ አሥር ባሕርያትን ከልስ:: ሀ) እነዚህ ባሕርያት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ የሆኑት ለምን ይመስልሃል? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ የተጠቀሱት እያንዳንዳቸው ባሕርያት ባይኖሩት ሊመጣ የሚችለውን ውጤት ዘርዝር:: ሐ) በየትኛዎቹ ባሕርያት ጥሩ ነህ? መ) ደካማስ የሆንከው በየትኛዎቹ ባሕርያት ነው? ሠ) ደካማ በሆንክባቸው ባሕርያት ለማደግ ምን ማድረግ ትችላለህ?



## አራተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ስብሰባ ይሆን ዘንድ የሳምንቱን ትምህርቶች ከልስ::

# ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች:-

1. ሀ) ለአገልግሎትና ለመሪነት ከእግዚአብሔር የሆነ «ጥሪ» አለኝ ማለት ምን ማለት ነው? ለ) ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በእርሱ ቦታ ሆነው እንዲያገለግሉት «ጥሪ» ሲኖራቸው የሚገባው ለምንድን ነው ትላለህ? ሐ) ትኩረታችን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች ከእግዚአብሔር የሆነ ግልጽ ጥሪ እንዲኖራቸው ከሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን የተለየ ነገር ይፈጠራል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የሆነ ጥሪ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ምን ማድረግ አለባቸው? ሠ) ሽማግሌዎች አንድን ሥራ የሚፈጽም ሰው ከማግኘት ይልቅ በጥሪ ላይ ቢያተኩሩ ኖሮ ለአገልግሎት የሚሆንን ሰው ስለ መምረጥና ስለ መሾም ያላቸው መረዳት እንዴት ሊለወጥ ይችል እንደ ነበር ግለጥ::

2. ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በሕይወትህ በትንሹ መታመንህ እንዴት ትልቅ ኃላፊነትን እንዳስገኘልህ ግለጥ:: ለ) ይህ መመሪያ ቤተ ክርስቲያን መሪን በምትመርጥበት መንገድ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ወይም በቤተ ክርስቲያን ላይ የአገልጋዮች እሿሿም ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ግለጥ? ሐ) ባላቸው ነገር ላይ ታማኞች ያልኑ ሰዎች በአመራር ደረጃ ላይ እንዲያገለግሉ ሥልጣን ሲሰጣቸው ምን ዓይነት ችግር ሊፈጠር አይተሃል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ለትልልቅ ኃላፊነት ከመሾማቸው በፊት በአነስተኛ ኃላፊነቶች ላይ ልምድ እንዲያዳብሩ ምን ማድረግ አለባቸው?

3. ሀ) መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ግንኙነት የሚመነጩትን አራት የስኬታማ መንፈሳዊ አገልጋይ ባሕርያትን ዘርዝር። ለ) እነዚህ አራት ነገሮች በቤተ ክርስቲያን መሪ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠቀምባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአራቱ ባሕርያት ለማደግ ምን ማድረግ አለባቸው?

4. ሀ) ከመሪው ግላዊ ባሕሪ ጋር የሚያያዙትን አሥር የስኬታማ አገልግሎት ባሕርያት ዘርዝር። ለ) እያንዳንዱ ባሕሪ ለቤተ ክርስቲያን መሪ የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ የተዘረዘሩት እያንዳንዱ ባሕርያት ከጐደሉት ሊመጡ የሚችሉትን አንዳንድ ውጤቶች ዘርዝር። መ) ከእነዚህ ባሕርያት ውስጥ በአብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ደካማ ሆነው የሚታዩት የትኞቹ ናቸው? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ የሕይወታቸው ክፍል እንዲያድጉ ምን ትመክራለህ?

# ትምህርት አምስት

## የመጀመሪያ ቀን፡- ለመንፈሳዊ መሪነት የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 6)

አንድ መሪ በአንድ ወቅት፣ «ለሕዝቡ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔርን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል ቀላል ነበረ» አለ። መሪነት በጣም አስቸጋሪ የሆነው ሥራ ስለሚበዛ አይደለም፣ ነገር ግን ከሕዝቡ ጋር ባለው ችግር ነው። ኢሳይያስ፣ ሁላችንም የበጎች ባሕሪ አለብን፣ እያንዳንዳችን የራሳችንን መንገድ እንከተላለን» (ኢሳ. 53:6) ያለው ቃል በትክክል በቤተ ክርስቲያን ያለውን ሕይወት ይገልጣል። ኃጢአተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንደ መሆናችን፣ እያንዳንዱ እማኝ ወደ ገዛ መንገዱ



ያዘነብላል። እግዚአብሔር ልጆቹ ሥጋዊ መንገዳቸውን ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ የሚፈልገው በመሪዎች በኩል ነው። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለሕዝቡ ኢየሱስን መከተልን ሊያስተምራቸው ከፈለገ ራሱን ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር የሚያቀራርብበት መንገድ በጣም አስፈላጊ ነው።

### ለስኬታማ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት፡- መሪው ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለው ግንኙነት የሚመነጩ ባሕርያት

### 1. ታጋሽነት፡- እግዚአብሔር በእኛ ቦታ ሆኖ እንዲሠራልን መጠበቅ።

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ምሳ. 14:29፤ 16:32፤ 19:11፤ 25:15፤ መክ. 7:8፤ 1ኛ ቆሮ. 13:4፤ ገላ. 5:22፤ ቆላ. 1:10-12፤ 2ኛ ጢሞ. 4:2፤ ዕብ. 6:12፤ ራእይ 14:12ን አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ስለ ታጋሽነት ምን ያስተምሩናል? ለ) መሪ በተለየ ሁኔታ ትዕግሥት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? |

አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ጸለየ፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ትዕግሥት ስጠኝ፣ አሁኑኑ ትዕግሥት ያስፈልገኛል!» ብሎ ጸለየ። ጥያቄው እንደሚያሳየው ሰውዬው ችኩላ ላይ ነበር። ልክ እንደ ብዙዎቻችን፣ ሰውየው ፈጣን ምላሽ ፈልጓል። ነገር ግን እግዚአብሔር ፈጽሞ አይቸኩልም፣ ሰዎችም በፍጥነት አይለወጡም። ስለዚህም ትዕግሥት መሪ ሊያዳብረው የሚገባ አስፈላጊ ባሕሪ ነው። ታጋሽ ሰው አንድ ነገር በፍጥነት እንዲሠራ ከመገፋፋት ይልቅ፣ እግዚአብሔር እስከሚያደርገው ድረስ በመተማመን ይጠብቃል። መጽሐፍ ቅዱስ ትዕግሥትን በተለያዩ መንገዶች ይመለከታል።

ሀ. እንደ ስደት ወይም ድህነት ባሉ የመከራ ጊዜዎች ትዕግሥት ያስፈልጋል። በመከራ ጊዜ መታገሥ ማለት ያለምንም ማጉረምረም መከራውን መቻል፣ በዚያ ችግር ውስጥ በጽናት ማለፍ የምንችልበትን ጥንካሬ እግዚአብሔር እንደሚሰጠንና

ከመከራው እንደሚያሳርፈን ማመን ነው። መሪነት በራሱ ትዕግሥትን የሚጠይቅ ችግር ነው። አንዳንድ የማይችሉ ችግሮች አሉ። እንደ ገንዘብ እጥረት ወይም የብቁ አገልጋይ እጥረትና መፍትሔ የሌላቸው የሚመስሉ ከሰዎች ጋር ያሉ ችግሮች አሉ። ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ማድረግ የምንፈልገውን ነገር ይቃወማሉ። ወይም ይሰድቡናል፣ ወይም ባላደረግነው ነገር ይከሱናል። ትዕግሥትና ጽናትን ካልተማርን በስተቀር እናቆማለን። ነገር ግን ስናቆም፣ ለውጥን የምናመጣ የእግዚአብሔር መሣሪያዎች መሆናችን ይቀራል። ትዕግሥት በእምነት አገልግሎት እንድንቀጥል ያደርገናል፣ እግዚአብሔር ቅንነታችንን እንዲገልጥና ሰዎች እኛን ይሰሙ ዘንድ ልባቸውን እንዲለውጥ ያደርጋል። ትዕግሥት ከሌለን ብዙ ጊዜ የምናማርር እንሆናለን፣ ደግሞም ሰዎችን እንበቀላለን። ታጋሽነት ሰዎች ጉዳት ሲያደርሱብን መቀበል እንድንችል እግዚአብሔር ለእኛ እስኪበቀል መጠበቅ ነው።

ለ. ሰዎች እስኪያድጉ በትዕግሥት እንድንጠብቃቸው ተነግሮናል (1ኛ ቆሮ. 13:4)። ይህ ማለት አንድ ሰው የሚጐዳንን ወይም የሚያስከፋንን ነገር ሲያደርግ እንቆጣም ማለት ነው። ያ ማለት ሰዎች ሲያስከፉን አንድ ዕድል ብቻ እንሰጣቸዋለን ማለት አይደለም፣ ነገር ግን እስኪለወጡና እስኪያድጉ ድረስ ብዙ ዕድል እንሰጣቸዋለን ማለት ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነታችን፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች ወዲያው እንዲለወጡ እንፈልጋለን። ነገር ግን ሁሉም ለውጥና እድገት አዝጋሚ ሂደት ነው። መሪ ሆነን እኛ የምንፈልገውን ለውጥ ሕዝቡ ካልፈለገ ተስፋ ለመቁረጥ በጣም ቀላል ነው። ትዕግሥት ማለት ሰዎችን በማስተማርና በመስበክ እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ውስጥ እንዲሠራና እንዲለውጣቸው ጊዜ መስጠት ማለት ነው። ታጋሽ መሪ ውሳኔዎችን የሚወስደውና የሚመራው ሰዎች ለመለወጥ ፈቃደኛ በሆኑበት ፍጥነት ነው። ከአባላት ፊት ቀድሞ እየሮጠና ጠንካራ ቃላትን እየተጠቀመ እርሱ የሚፈልገውን ነገር እንዲያደርጉ እያስገድዳቸውም። ይልቁንም፣



ሰዎች ለመስማት ዝግጁ እስኪሆኑ ድረስ ታግሦ ከሰዎች ጋር ይሠራል። እረማመዱን ከሕፃን ልጁ እረማመድ ጋር እንደሚቃኝ አባት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪም የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት የሚቃኘው አባላት መራመድ በሚችሉበት ፍጥነት ነው። ሰዎች ሲያጠፉ ክፉ አይሆንባቸውም፣ ነገር ግን ድካማቸውን በመረዳት በጨዋነት ያስተናግዳቸዋል።

በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ሰሎሞን የታጋሽነትን ኃይል አሳይቷል። ትዕግሥት የሰዎችን ቁጣ በማብረድ ለጊዜው ችግር መፍትሔን ይሰጣል። ብዙ ጊዜ መሪዎች ችኩላ ላይ ከሆንን ለሰዎችና ለችግራቸው መፍትሔ ከማምጣት ይልቅ እንጎዳቸዋለን። ጥበብ እግዚአብሔር ነገሮችን እስኪያስተካክልና በችግሩ ላይ መንፈሳዊ ጥበብ እስኪያመጣ ድረስ እንድንቆይ ያስተምረናል። አንድን ጉዳይ ለመፍታት ትክክለኛ የሆነና ያልሆነ ጊዜ አለ። ችግርን ለመፍታት በታጋሽነት የእግዚአብሐርን ጊዜ መጠበቅ አለብን። አለበለዚያ፣ ሰይጣን ችግሩን ለማባባስ ትዕግሥት የለሽነታችንን ይጠቀምበታል።

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመሪዎች ፊት የተጋረጡና ትዕግሥትን የሚጠይቁ ሁኔታዎችን ዘርዝር። ለ) የመሪው ትዕግሥት ማጣት ለቤተ ክርስቲያን እንዴት ችግር ሊፈጥር እንደሚችል አብራራ። |

## 2. በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች መገዛትና መታመን።

አንድ ሰው ምንም ዓይነት የመሪነት ደረጃ ላይ ቢሆን፣ ከበላዩ ላለ መሪ እንዴት እንደሚገባ መታዘዝ እንዳለበት ማወቅ ይገባዋል። መገዛትን ያልተማረ መሪ ብዙ ጊዜ የዐመፀኝነት መንፈስ ስለሚታይበት በመሪነት ላይ ካሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር ይታገላል። በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የሚፈጠር የዐመፀኝነት መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልልቅ ችግሮችን ያመጣል፣ ምክንያቱም ሥልጣንን ለመቆጣጠር ሁሉም ስለሚፈልግ ነው። አንድ አፍሪካዊ አባባል እንደሚለው፣ «ዝሆኖች ሲጣሉ፣ ሣሩ ይጐዳል።» በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሥልጣን ላይ

ላሉ ሰዎች ካልተገዙ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ይጐዳሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች በመገዛት የሚታወቁ መሆን እንዳለባቸው ያስተምራል። ለሌሎች ጥቅም ብለን የግል ፍላጐቶቻችንን ወደ ጎን በምናደርግበት ጊዜ፣ እያንዳንዳችን በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛን እንሆናለን (ኤፌ. 5:21)። ዓለማውያን መሪዎችንም ቢሆን እግዚአብሔር ለዓላማው በእኛ ላይ እንደ ሾማቸው አውቀን ልንገዛላቸው ይገባል (ሮሜ. 13:1-2)። ለጊታ እንደምንገዛ በሥራ ቦታችን ላሉ አለቆቻችን መገዛት አለብን (ኤፌ. 6:5-8)። ወጣቶችም ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ከመጣላት ይልቅ እንዲታዘዟቸው ተነግሮአቸዋል (1ኛ ጴጥ. 5:5)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃይለኛ የሚባለው መሪ እንኳን ሳይቀር ለእግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት መገዛት አለበት (ያዕ. 4:7)። አንድ ሰው ለሌሎች መገዛትን ካልተማረ፣ ለእግዚአብሔር የመገዛት መንፈስ አይኖረውም። ስለዚህ በግልጽ፣ የሌሎችን አገልግሎት ዝቅ አድርጐ ከመመልከት ይልቅ በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች መገዛትና አብሮ የመሥራት ባሕሪ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ ያስፈልጋል።

ኅብረተሰቡ በኮሚኒስት ደርግ መንግሥት አገዛዝ ውስጥ ከማለፉ የተነሣ ከተፈጠሩ አሉታዊ ውጤቶች መካከል አንዱ በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎችን አለማክበርና ለእነርሱም አለመገዛት ነው። ሕፃናት ቤተሰባቸውን መስማትና መታዘዝ ያለባቸው አይመስላቸውም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ መገዛት ያለባቸው አይመስላቸውም። ሌላው ቀርቶ ለቤተ ክርስቲያን ወጣቶች እንደ ምሳሌ የሚታዩት የመዘምራን ቡድን አባላት እንኳን፣ ሽማግሌዎች በማይፈልጉበት መንገድ በማምለክ፣ ሙዚቃን ከሚገባ በላይ በማጮህ፣ ወይም ሙዚቃውን እንዲቀንሱ ሲጠየቁ እስከ መጨረሻው በመክፈት በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ላይ «ያምፃሉ።» ወይም አምልኮአቸውን እንዲቀይሩ ሲጠየቁ፣ ለቤተ ክርስቲያን ከመገዛት ይልቅ ቤተ



ክርስቲያንን እንለቃለን ብለው ያስፈራራሉ። ደመወዝተኛ የሆኑ መጋቢዎችና ወንጌላውያን ብዙ ጊዜ ለሽማግሌዎች ሲገዙ አይታይም። ዕቅዳቸው ተቀባይነትን ካላገኘ፣ ሽማግሌዎችን ከመሪነታቸው ላይ ለማስነሣት ከወጣቱ ጋር ይሠራሉ ወይም ሽማግሌዎች ካልተገዙላቸው ቤተ ክርስቲያን እንደሚለቁ ያስጠነቅቃሉ። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ጊዜ በሽማግሌዎች ጉባኤ የተወሰነን ነገር አንቀበልም ይላሉ። ሌሎች ሽማግሌዎች የወሰኑትን ውሳኔ ካልወደዱት፣ በዝምታ በማመፅ ስለ ውሳኔው ለማንም አይነጋሩም ወይም ውሳኔው ምን ያክል መጥፎ እንደ ሆነ በመናገር ሲያጣጥሉ ይታያሉ። እነዚህ ሁሉ በሥልጣን ላይ «የማመፅ» መንገዶች በእግዚአብሔር ላይ የሚሠሩ ኃጢአቶች ሲሆኑ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ትልቅ ችግር ያስከትላሉ። ዛሬ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ከጠፋባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ለባለ ሥልጣን አለመገዛታችን ነው።

## ለባለ ሥልጣናት «መገዛት» ምን ማለት ነው?

ሀ. ያ ማለት አማኞች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለየ አመለካከት ሊኖራቸው አይችልም ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በጨዋነትና በትሕትና ነገሮችን በተቻለ መንገድ ማድረግ የሚቻልባቸውን መንገዶች ለመሪዎቻችን እንድናካፍል ያሳየናል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን መስማት እንዳለባቸው መረዳት አለባቸው። ሌሎችን የማይሰማ መሪ ጥበበኛ አይደለም። ነገር ግን መገዛት ማለት አንድ ጊዜ የእኛን አመለካከት ካሳየን በኋላ፣ ውሳኔውን በሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች እንተዋለን ማለት ነው። እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው ብለን የምናስበውን ነገር ባለመናገራችን በኃላፊነት ይጠይቀናል። ነገር ግን ትክክለኛ ነው ብለን የምናስበውን ካካፈልናቸው በኋላ፣ እግዚአብሔር መሪዎችን ባለመስማታቸውና አስፈላጊ የሆነውን ለውጥ ባለማምጣታቸው ይጠይቃቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ላለው ችግር እግዚአብሔር በኃላፊነት አይጠይቀንም።

ሰ. መገዛት ማለት በእኛ ላይ መሪ ለሆነ ሰው መታመንና መርዳት ነው። በመሪዎች ቡድን ውስጥ አብረን ስንሠራ፣ እርስ በርስ ልንረዳዳና ልንተጋገዝ ይገባል። መገዛት ማለት አንድ መሪ የበላይ መሪ ከሆነው ሰው ጋር የአሳብ ልዩነት ካለው ወደ በላይ መሪው ሄዶ የእርሱን አመለካከትና ለምን በተለየ መንገድ እንዳሰበ ማሳየት ነው። በጉዳዩ ላይ በጋራ ከተነጋገሩ በኋላ ላለመስማማት ይስማሙ ይሆናል። ሰዎች ሁልጊዜም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አሳቦች ይኖራቸዋል። ነገር ግን በመጀመሪያ በግል፣ ከዚያም በሽማግሌዎች ጉባኤ በልዩነቶቹ ላይ ከተወያዩ በኋላ፣ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ፣ ውሳኔውን ያልተቀበለ ሽማግሌ በውሳኔው ላይ ያለውን ቅሬታ ከዚያ በኋላ ለማንም መግለጥ የለበትም። ያንን ማድረግ ለመገዛት ፈቃደኝነት ማጣትና ዐመፅ ነው። ከዚያም ሰይጣን መለያየትን ለመፍጠር ያንን ሰው ይጠቀማል።

ሐ. የምንገዛ ከሆነ፣ መሪው ቢሳሳትም እንኳን፣ በፍጹም ችግር እንፈጥርም። አንዳንድ ጊዜ መሪው ስሕተት እንደ ሠራና ሌላው ቀርቶ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይሄድ ኃጢአት እንደ ሠራ ልናውቅ እንችላለን። ምንድን ነው ማድረግ ያለብን? የዳዊትና የንጉሥ ሳኦል ምሳሌ እንዲህ ያለውን ችግር የምንይዝበትን መንገድ በጥሩ ሁኔታ የሚገልጽ ይመስለናል። ሳኦል ንጉሥ ዳዊትን ሲገድለው ሲሞክር የሚከተሉትን ነገሮች እናያለን።

1) ሳኦል መጥፎ ነገር ማድረጉን ሲያውቅ፣ ዳዊት ተቃውሞታል። ዳዊት በተደጋጋሚ ለሳኦል እርሱ ምንም ያስብ ምን ወይም ሌሎች ምንም ቢሉ ለሳኦል ታማኝ እንደ ሆነ ተናግሯል። (ለምሳሌ:- 1ኛ ሳሙ. 24:8-24)። ዳዊት ግን በንጉሥ ሳኦል ላይ ዐመፅ አልጀምርም፣ ንጉሡንም አልገድልም ብሏል። ዳዊት፣ «እግዚአብሔር በቀባው ላይ እንዴት እጄን አነሣለሁ?» ብሏል (1ኛ ሳሙ 24:5-6)። ዳዊት መሪን የሚያስነሣው እግዚአብሔር እንደ ሆነና የቀባውን የማውረድ ኃላፊነትም የእርሱ እንደ ሆነ ተረድቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ደስተኛ



ካልሆንን፣ ሰውየው ሥልጣኑን እንዲለቅ የማስገደዱ ሥራ የእኛ አይደለም። እስከሚቀጥለው ምርጫ በትዕግሥት ልንጠብቅ፣ ወይም እግዚአብሔር መሪውን እንዲለውጠው ወይም በሰላም ከኃላፊነቱ ላይ እንዲያስነሣው ልንጸልይ ይገባል (ማስታወሻ፣ 1ኛ ጢሞ. 5:19-20 ላይ አንድ መሪ በዐመፅ መንፈስ ተገፋፍቶ ከባድ ኃጢአት ሲሠራ ምን ማድረግ እንዳለብን መመሪያ ተቀምጦልናል።)

2) ፀብ ከመፍጠር ይልቅ፣ ዳዊት ከዚያ ሁኔታ ሸሸ። ለሳኦል እውነቱን ማለትም እንደማያምፅበት ነግሮታል። ሳኦል አልሰማ ሲለው፣ ዳዊት ራሱን ከዚያ ሁኔታ አወጣ። የመንግሥት ሥራውን ትቶ በምድረ በዳ ኖረ። ሌሎችን በጦር ሠራዊት ወይም በመንግሥት ኃላፊነት ላይ የነበሩትን በማሰባሰብ ሳኦልን ለመውጋት አልሞከረም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መሪው ወይም ሽማግሌዎቹ ኃጢአት መሆኑ የሚታወቅ ነገር ሲሠሩ፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ አንጻር ስሕተቶቻቸውን የማሳየት ኃላፊነት አለብን። ከዚያ በኋላም መስማት ካልፈለጉ፣ ከዚያ ሁኔታ መውጣት፣ ምናልባትም ከኃላፊነታችንን መልቀቅ አለብን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን መፍጠር ወይም እንዲፈጠር መደገፍ የለብንም።

3) ዳዊት በሳኦል ላይ የሚደረግ ዐመፅን ከመምራት ይልቅ፣ ለሳኦል ታማኝ ሆኖ በመቅረት እግዚአብሔር እንዲበቀልለት ፈቀደ። ምንም እንኳን በዳዊት አመራር ብዙ ሰዎች ተሰበው ቢቀሳቀሱትም፣ ዳዊት እነዚያን ሰዎች ተጠቅሞ በእስራኤል መካከል መከፋፈልን ለማምጣትና በሳኦል ላይ ሕዝባዊ ጦርነትን አላነሣሣም። ዳዊት በመሪነት ለመነሣት ሳኦል እስኪሞት ጠብቋል። መሪ ወይም የመሪዎች ቡድን መሳሳቱ በግልጽ ሲታወቅ፣ ወደ እግዚአብሔር ልንጸልይና እርሱ እንዲሠራ ልንጠይቀው ይገባል። የመሪዎችን ልብ እንዲለውጥ እንጠይቀዋለን። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሠሩትን ስሕተት ማየት እንዲችሉ እንጸልያለን። በጉዳዩ ላይ ያለንን ቅንነት እንጠብቃለን። ከዚያም እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ሁኔታውን ይለውጠዋል። ያንን ለማድረግ ብዙ ጊዜ የቅድስናና

የመንፈሳዊነትን አስፈላጊነት ለማሳየት የእኛ ሕይወት ይጠቅማል:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዐመፅና መከፋፈልን ካመጣን፣ መለያየትን ለማምጣት የሰይጣን መሣሪያዎች እንሆናለን:: በኋላም ለማቆም የሚከብድና መቋጫ የሌለውን ዐመፅ በቤተ ክርስቲያን እናስነሣለን:: ዐመፅን ብንመራና በኋላ መሪ ብንሆን፣ ሌላ ሰው ደግሞ በእኛ ላይ ያምፃል::

መሪዎች በግልጽ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሲሠሩ ካየህ፣ በትሕትና ቃሉን ካካፈልካቸው በኋላ ሁለት ምርጫዎች ይኖሩሃል፣ መንፈስ ቅዱስም የትኛውን መከተል እንዳለብህ ይመራሃል:: አንደኛ ፣ ልክ እንደ ዳዊት እግዚአብሔር የእነዚያን ሰዎች ልብ በመቀየር ወይም ከአመራር ላይ እስኪያነሣ ትጠብቃለህ:: ይህ በጣም መንፈሳዊ ምላሽ ነው:: ሁለተኛ፣ ድምጽ ሳታሰማ መልቀቅ ትችላለህ:: በቤተ ክርስቲያንህ የተፈጠረውን ችግር ትንፍሽ ሳትል ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን መግባት ትችላለህ:: ለሽማግሌዎች ለመልቀቅ የወሰንክበትን ሁኔታ ታስረዳለህ፣ ነገር ግን በጉዳይ ላይ በትኩረት ካልተጠየቅህ በስተቀር ለሌሎች ሰዎች መናገር የለብህም:: ከዚያ ትለቅቃለህ:: ይህንን የምታደርገው ግን በጣም ዝቅተኛ የሆነ የለውጥ ተስፋ ሲኖር ብቻ ነው:: ብዙ ችግር ጊዜ ሲፈጠር በችኮላ ነው ቤተ ክርስቲያን ለቅቀን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የምንገባው:: ነገር ግን ወደዚያ ከሄድንም በኋላ፣ ችግሮች ያጋጥሙናል:: ሁላችንም ፍጹማን ያልሆንን ክርስቲያኖች በመሆናችን፣ በሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ችግር ይኖራል:: ፍጹም የሆነች ቤተ ክርስቲያን በፍጹም ልታገኝ አትችልም:: እኛ ችግር በተፈጠረ ቁጥር የምንለቅ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለውጥ ለማምጣት ሊጠቀምብን አይችልም::

3ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ እንደተጠቀሰው ለመሪዎች መገዛትን ብንማር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ይበልጥ ኅብረት ሊመጣ የሚችለው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ:: ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በመሪዎች ላይ ዐመፅ የተፈጠረባቸውን ሁኔታዎች አብራራ :: ምን ነበር የተፈጠረው? ሁኔታው



በምን መልኩ ነው መንፈሳዊ በሆነ ሁኔታ ሊያዝ ይችል የነበረው? ሐ) አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው፣ በተለይ መሪ፣ ቤተ ክርስቲያኑን ጥሎ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሊገባ የሚለጠው ምክንያት ምንድን ነው? ምንም ልዩነት እንዳይፈጠርና ለይጣንም የኢየሱስን ክብር እንዳያጉድፍ ሁኔታውን በምን መልኩ መያዝ ይገባዋል?

## 3. ፍትሕ:- ሰዎችን ዓለም በሚያይበት መንገድ ሳይሆን በእኩልነትና በፍትሐዊነት የማስተናገድ ባሕሪ ነው::

4ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሚክያስ 6:8ን አንብብ:: እግዚአብሔር ከሕዝቡ በለሚያበፈልገው ነገር ምን አስ? ለ) መሪዎች ፍትሕን መውደዳቸውና ለዎች በእኩልነትና በፍትሐዊነት እንዲስተናገዱ መፍቀዳቸው አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን ሁሉ እኩል ማስተናገድ በጣም ለለሚከብዳቸው ሁኔታዎች ዘርዝር:: መ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ችግር እንደሚፈጥር ግለጥ::

ሁላችንም ያደግነው ኢ-ፍትሐዊነትን በሚያከብርና እንደ ተለመደ ነገር በሚቆጥር ማኅበረሰብ ውስጥ ነው:: የእኩልነት አለመኖር በዙሪያችን አለ:: በወንዶችና በሴቶች መካከል፣ በተማሩትና ባልተማሩት መካከል፣ በሐብታምና በድሃ መካከል፣ በተከበሩ ብሔሮች (ለምሳሌ፣ አማራ) እና በማይከበሩት (ለምሳሌ፣ ሻንቅላ ወይም ሸክላ ሠሪዎች)፣ በተከበሩ ዓይነት ሥራዎች (ለምሳሌ፣ አስተማሪነት) እና በማይከበሩ ሥራዎች (ለምሳሌ:- ሸክላ ሠሪና ቀጥቃጭ) መካከል ልዩነት እናደርጋለን:: እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ይህ በእኩል ያለማየት ነገር የተለመደ ይመስላል:: ብዙ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይከሰታል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ኢ-ፍትሐዊነትና መለያየት ለማየት ክርስቲያኖች የትዳር አጋራቸውን እንዴት እንደሚመርጡ ተመልከት::

የቤተ ክርስቲያን መሪ እነዚህ መለያየቶች የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆኑ የእኛ ኃጢአተኝነት ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ አለበት:: እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊነትንና ማንኛውንም ዓይነት ማዳላትን እንደማይቀበል ልንረዳ ይገባል (ዘሌዋ. 19:15፤

ዘዳግ. 1:17፣ 2ኛ ዜና 19:7፤ 1ኛ ጢሞ. 5:21):: የእግዚአብሔር ሕዝብና የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍትሐን ካልተገበሩና ለማኅበረሰቡ ፍትሕ እንዲመጣ ካልፈለጉ፣ ሁሉም አምልኮዋቸው ተቀባይነትን አያገኝም (ኢሳ. 1:10-17፤ 6:6-8፤ ምዕራፍ 58፤ያዕቆብ 1:27):: ጳውሎስ ሲናገር በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኩልነት ያልሰፈነበት ክፍፍል የለም:: ሁሉም ሰው በእኩል ዓይን መስተናገድ አለበት (ገላ. 3:26-29):: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የወንጌልን ትምህርት በሚያንጸባርቅ መልኩ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት ካለባቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትን ማምጣት ካለባቸው፣ ፍትሕን መውደድን መማር አለባቸው:: ፍትሕ ትክክለኛና ሚዛናዊ የሆነ ነገርን ማድረግና የሰዎችን እኩልነት በሚቀበል መልኩ ነገሮችን ማድረግ ነው:: ይህ ማለት መሪው በወንዶችና በሴቶች መካከል፣ በሐብታሞችና በድሆች መካከል፣ በተማሩትና ባልተማሩት መካከል፣ በልዩ ልዩ ብሔሮች መካከልና በምንም ዓይነት ኢ-ፍትሐዊ ነገሮች መካከል አይሠራም ማለት ነው::

በቤተ ክርስቲያን፣ ሁሉም ወንድማማቾችና እኅትማማቾች ናቸው:: የኢኮኖሚ አቅማቸውና የትምህርት ደረጃቸው ምንም ቢሆን እና ከየትኛውም ብሔር ቢመጡም እንኳን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ ልጆች ናቸው:: እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉንም መንፈሳዊ ልጆቹን በእኩልነትና ሚዛናዊነት እንድናስተናግዳቸው ይፈልጋል:: መሪ ለራሱ ቤተሰብ ወይም ጐሣ፣ ለተማረ ወይም ለሀብታም ሲያዳላ ኢ-ፍትሐዊነትን በማስፋፋት ላይ እየተሳተፈ ነው:: ሰይጣንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩነትን ለመፍጠር ይጠቀምበታል::

በቤተ ክርስቲያንህና በማኅበረሰብህ ውስጥ ፍትሕ እንዲኖር ትናፍቃለህ? ከምታገኛቸው ሰዎች ጋር ፍትሕን ትለማመዳለህ? ቤተ ክርስቲያንህን እኩልነትንና ሚዛናዊነትን በጠበቀ መልኩ ትመራለህ? አስታውስ፣ የእግዚአብሔር ቃል ያለ ፍትሕ



እግዚአብሔርን በእውነት ልናመልከው እንደማንችል ይገልጥልናል::

**4. ርኅራኄ:- የሚታገሉትንና የእኛን ዕርዳታ የሚፈልጉትን በመርዳት ላይ የሚያተኩር ባሕሪ ነው::**

| |
|---|
| 5ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 22-34-40፤ ሉቃ. 10:25-37ን አንብብ:: ሀ) ኢየሱስ በሁለተኛ ደረጃ እጅግ አስፈላጊ ነው ያለውና እግዚአብሔርን በሁለንተናችን ከማክበር ጋር የማይነጣጠለው ነገር ምንድን ነው? ለ) ርኅራኄን ማሳየት ያልፈለገው ማን ነው? ሐ) ማን ነው ርኅራኄን ያሳየው? መ) ይህ ታሪክ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሕዝቡ ርኅራኄን ማሳየት እንዳለባቸው ምን ያስተምረናል? |

በቤተ ክርስቲያን መሪ ሕይወት ከሚታዩ ትልቅ አደጋዎች መካከል አንዱ ችግር ውስጥ ለወደቁት አለማሰብ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይረዷቸው ዘንድ በብዙ ሰዎች ይጠየቃሉ:: ድሆች ገንዘብ ፍለጋ ይመጣሉ:: ሕሙማንም ዕርዳታ ፈልገው እኛ ዘንድ ይመጣሉ:: ባልና ሚስቶች ወይም የተጣሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስምምነት እንድናመጣ ወደ እኛ ይመጣሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ስንሆን በማያቋርጥ ሁኔታ የእኛን እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎች ይመጡብናል::

ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች መድከምና ለሰዎች ርኅራኄ ማሳየትን ማቆም ቀላል ነው:: እነዚህን ሰዎች በወንጌል ሕዝባችንን መድረስ የሚያስችል ዕቅድ ማውጣት እንዳንችል እንደሚያደርጉ ደንቃራዎች ልንመለከታቸው እንችላለን:: በሉቃስ 10 ላይ፣ አማኞች ስለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ኢየሱስ የሰጠው ትምህርት አለ:: በዚያ ላይ በተለይ መሪዎች ለተጎዱት ሰዎች ርኅራኄ እንዲያሳዩ ይጠይቃል:: በዚህ ገጽ ላይ የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል:-

ሀ. ምንም እንኳን የሕግ አዋቂው ታላቁ ትእዛዝ የትኛው ነው ብሎ ቢጠይቅም፣ ኢየሱስ ግን ሁለቱ ትእዛዛት አብረው እንደሚሄዱ ተናግሯል:: የመጀመሪያው ትእዛዝ እግዚአብሔርን

በሙሉ ልብህ ውደድ የምትለው ነች። ነገር ግን የሰው አመለካከት እግዚአብሔርን መውደድ ላይ ስለሚሆን እርስ በርሳችን ያለመዋደድ እንደሚከሰት ኢየሱስ ያውቃል። ስለዚህ ኢየሱስ ወዲያውኑ ሁለተኛውን ትእዛዝ «ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለውን ተግባራዊ እንድናደርግ ሰጠን።

ሰ. የ«እኛ ጐረቤት» የዳነና ያልዳነ ማንኛውም ችግር ያለበት ሰው ነው። ያ መሠረት የሚያደርገው ከእኛ ብሔር በሆኑ ወይም ባልሆኑ፣ ከእኛ ቤተሰብ ከሆኑና ካልሆኑ ወይም በምናውቃቸው ሰዎች አይደለም። ሀብታም ይሁኑ ድሃ፣ የተከበረ አኗኗር፣ ይኑራቸው ወይም ያልተከበረ አኗኗር፣ ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ በመሆናቸው ሁሉም የእኛ ጐረቤት በመሆናቸው ልንረዳቸው ይገባል።

ሐ) ርኅራኄን ማሳየት በጣም የሚከብዳቸው የሃይማኖት መሪዎች ናቸው። ኢየሱስ ሁለት ዋና ዋና የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችን ካህኑንና ሌዋዊውን መርዳት ሲገባቸው ሳይረዱ በማለፍ ጠቅሷቸዋል። ሌሎችን ለመርዳት ልባቸው በመደንደኑ በሰው ሥቃይ ውስጥ ራሳቸውን አይከትቱም።

ዛሬም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ይህ ነገር ይሠራል። የሰውን ችግር መረዳት ምን ያክል ይቀልለናል። ሰዎች በኃጢአት ሲወድቁ ወዲያውኑ ትዕግሥታችን አልቆ እንደ ጠላት እንመለከታቸዋለን። ወይም ሰዎች ችግሮቻቸውን ይዘው ሲመጡ «እግዚአብሔር ይርዳህ» ብለን እንሄዳለን። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚረዳው በእኛ እልፎ እንደ ሆነ እንረሳለን። መከራ በቤተ ክርስቲያንና በአገራችን በማደግ ላይ ነው። የኤድስ ወረርሽኝ ሲስፋፋና በቤተ ክርስቲያናችንና በማኅበረሰባችን የሚገኙ ሰዎች ሲታመሙና ሲሞቱ፣ የማደጐ ልጆች ሲጨምሩ፣ ርኅራኄ እንድናሳይ በእኛ ላይ የሚወድቀው ጥያቄ ይጨምራል።

እግዚአብሔር የጠየቀን ጥቅም የሚያመጣልንን እድገት



እንድንፈልግ ሳይሆን፣ ለተጎዱት ፍቅርን እንድንሰጥ ነው። ከርኅራኄ ልብ የማይፈስ እድገት ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ የእግዚአብሔርን በረከት ባለመቀበል ነው የሚያበቃው። ልብህ እየደነደነ ሄዷል? ርኅራኄህን አጥተሃል? የአንተ ቤተ ክርስቲያን ለተጐዱት በመራራት ይታወቃል? እግዚአብሔር ለሰዎች ችግር ልባችንን ሩኅሩኅ ያድርግልን።

## 5. ወዳጅነት፡- ሰዎችን ጓደኛ የማድረግና ወደ እኛ ሲመጡ ደስ የመሰኘት ባሕሪ ነው።

> 6ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ጎብኚዎች የአንተን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ባሕሪ ይገልጧታል? መልስህን አብራራ። ለ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች በወዳጅነት ባሕሪያቸው የሚታወቁ፣ በቤታቸው፣ በቢሮአቸውና በቤተ ክርስቲያናቸው ሰዎችን በደስታ የሚቀበሉ ናቸው? መልስህን አብራራ። ሐ) መሪዎች ተግባቢ መሆን ለምን የሚቸግራቸው ይመስልሃል? መ) ማቴ. 11፡9ን አንብብ። በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ ምንድን ነው የተባለው? ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ነገር ዝነኛ እንዲሆኑ የሚፈቅዱ ይመስልሃል? ለምን?

አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያን መሪነታቸውን ክብር ለመጠበቅ ከሰዎች ጋር መቀራረብ ያለባቸው አይመስላቸውም። ከሰዎች ጋር መቀራረብ አይፈልጉም። ሰዎች ኃጢአተኛ መሆናቸውን ከሰማን፣ ከእነርሱ ጋር ያለንን ርቀት እንጠብቃለን። ነገር ግን ይህ ኢየሱስ ካሳየው ጋር ይቃረናል። እርሱ ይታወቅ የነበረው የሕዝቡ ወዳጅ እንደ ነበረ ነው። ሰዎች ከእርሱ ጋር መሆን ደስ ይላቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ በጣም የታወቁ ኃጢአተኞችም እንኳን ከእርሱ ጋር መሆን ደስ ያለኛቸው ነበር። እርሱ ሥራቸውን እንደማይደግፍ ያውቁ ነበር። ነገር ግን እንደሚወድዳቸውና ወደ እርሱ ሲመጡ ደስ እንደሚለው ያውቃሉ። የሃይማኖት መሪዎች ናቸው ኢየሱስ እነርሱ ርኩስ ከሚሏቸው ሰዎች ጋር መወዳጀቱን ያልወደዱት።

በኢየሱስ ዘመን እንደ ነበሩት የሃይማኖት መሪዎች ሆንን

እንዴ? ከሰዎች ሁሉ ጋር ወዳጅ መሆንን እንፈራለን? መሪዎች የወዳጅነት ስሜት ካልተነበበባቸው፣ ቤተ ክርስቲያናት የሚጋብዙ አይሆኑም:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጉብኝት የሚመጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ከሚወቅሱባቸው ምክንያቶች አንዱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ስሜት አይነበብባቸውም የሚል ነው:: ማንም ሰው እንኳን ደህና መጣችሁ እይላቸውም፣ ወይም ማንም ግድ አይሰጠውም:: ስለዚህ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፣ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን ይተዋሉ:: በጣም ከፍተኛ ከሆነ የኃጢአት ሕይወት የዳኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ በሌሎች አማኞች እንኳን ደህና መጣችሁ አይባሉም:: የተለወጠች ሴተኛ እዳሪ አንድ ጊዜ ወደ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት መሄድ እንደማትፈልግ ተናግራለች:: መሪዎችና አባላት ሴተኛ አዳሪ እንደ ነበረች እንደ ለሙ፣ የእንኳን ደህና መጣሽን ስሜት ሊያሳዩዋት አልቻሉም:: ቤተ ክርስቲያን መሆን ካለባት ምን ያክል እንደ ራቅን ይታያችኋል! ቤተ ክርስቲያን ሕሙማን መጥተው እንደሚፈውሱበት ሆስፒታል ነች:: ኃጢአተኞች መድኃኒት ፍለጋ ወደ ኢየሱስ ሲመጡ እንኳን ደህና መጣችሁ የሚባሉበት ቦታ ነው (ማር. 2:17):: ቅዱስ እንደ ሆኑ ለሚያስቡ ሰዎች የሚሆን ቦታ አይደለም፣ ይልቁንስ የዳኑ ኃጢአተኞች እግዚአብሔር ስላዳናቸው ሊያመሰግኑ የሚመጡበት ቦታ ነው::

## 6. ማበረታታት:- ሌሎች በእምነታቸው እንዲያድጉ የመገንባት ባሕሪ ነው::

7ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዕብ. 3:13፣ 10:25ን አንብብ:: ምን ዓይነት ትእዛዝ ነው በዚያ የተሰጠው? ለ) የሐዋ. ሥራ 4:36ን አንብብ:: ለዮሴፍ የተሰጠው ልዩ ስም ምንድን ነው? ያ ስም ምን ማለት ነው? ሐ) ለመሪ የእነዚህ ባሕርያት መኖር ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

ለአብዛኛዎቹ ሰዎች፣ ሕይወት በጣም አስቸጋሪ ነው:: በሥራ ቦታና በቤታቸው ችግር አለባቸው:: እግዚአብሔርን መታዘዝ ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን በተደጋጋሚ ስለሚወድቁ ተስፋ ይቆርጣሉ::



በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የመሪ ባሕርያት ውስጥ አንዱ ሰዎችን ማበረታታት ይገኝበታል:: የሚያበረታታ ሰው የሰዎችን ተስፋ መቁረጥ አይቶ በመምጣት በመንፈሳዊ ምክር ፍቅርን የሚያሳይና ለእግዚአብሔር መኖራቸውን እንዲቀጥሉ የሚያበረታታቸው ነው:: ይህ ሰው የሚመጣው ሊከሰክላቸው ሳይሆን፣ እንዲያድጉ ሊረዳቸው ነው:: የቆጵሮሱ ዮሴፍ እንደዚህ ዓይነት ሰው ነበር:: በሆነ ነገር የተከፉ ሰዎችን ሁልጊዜ መርዳት ይፈልጋል:: ለዚያ ነው ቤተ ክርስቲያን ስሙን ወደ በርናባስ የቀየሩት፣ ትርጉሙም «የመጽናናት ልጅ» ማለት ነው:: በርናባስ ነው ጳውሎስ በተርሴስ ተሰውሮና ተስፋ ቆርጦ ሳለ ያገኘው (የሐዋ. ሥራ 11:25-26):: በመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞው ውድቀት የደረሰበትን ዮሐንስ ማርቆስን ያጽናናው እርሱ ነው:: በርናባስ ዮሐንስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ሌላ ዕድል ሊሰጠው ፈለገ (የሐዋ. ሥራ 15:36-40):: በርናባስ ጳውሎስን ሳያበረታታው ቢቀርና በአንጾኪያ እንዲያገለግል ዕድሉን ባይሰጠው ኖሮ ምን እንደሚፈጠር ይታያችሁ:: ምናልባትም የአሕዛብ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ ወንጌልን ወደ አውሮፓ ሳያደርስና አብዛኛዎቹን የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ሳይጽፍ ይቀር ነበር:: ዮሐንስ ማርቆስ ማንም አያምነኝም ብሎ አገልግሎት ሲያቋርጥ ምን እንደሚፈጠር ይታያችሁ:: የማርቆስ ወንጌል አይጻፍም ነበር:: ማን ያውቃል ምናልባትም እግዚአብሔር ለክብሩ ሊጠቀምባቸው የሚፈልግ ብዙ ሰዎች መሪዎች ስላላበረታቷቸው ብቻ ተስፋ ቆርጠው ይሆናል? በጣም ስኬታማ የሆኑ መሪዎች ሌሎችን ለታላላቅ አገልግሎት የሚያበረታቱና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲቀጥሉበት የሚገፋፉት ናቸው::

## 7. ዲፕሎማሲ:- በትክክለኛው ጊዜና በትክክለኛው መንገድ የሚናገሩትን ማወቅ::

የመሪን የማገልገል ብቃት ከሚያሳድጉ ባሕርያት አንዱ ነገሮችን ከማባባስ ይልቅ መፍትሔ የሚያመጣ ንግግር ማድረግ መቻል

ነው። ስሎሞን ሲጸፍ፣ «ባግባቡ የተነገረ ቃል፣ በብር መደብ ላይ እንደ ተቀረጸ የወርቅ እንኮይ ነው» (ምሳ. 25:11)። ያንን ሲል መሪ አንደበቱን በትክክለኛው መንገድ መጠቀምን መማሩ ውብ ነው ማለቱ ነው። መሪዎች የሚመሩት በንግግር ነው። በሚናገሩት ነገር መከፋፈልን ሊያመጡና ሰዎችን ሊጐዱ ይችላሉ። ወይም በንግግራቸው ሰላምን ሊያመጡ ይችላሉ። የሚሉትን ማወቅ፣ መቼ እንደሚሉት ማወቅና እንዴት እንደሚሉት ማወቅ ጥሩ መሪዎች ሊማሩት የሚገባ ክህሎት ነው። በትክክለኛው ነገር ትክክል ያልሆነ ነገር በመናገር ትልቅ መከፋፈልን ልናመጣ እንችላለን። መሪ እንደ መሆናችን መጠን፣ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ትክክለኛ በሆነ መንገድና ሰዓት እንዴት መናገር እንደምንችል መማር አለብን። ይህ ሲሆን፣ ችግሮች ይወገዳሉ። ግንኙነቶች ይፈወሳሉ። የእግዚአብሔርም ሥራ ይከናወናል።

**8. ሰላምን የሚያመጣ ሰው መሆን፦ ሰዎች በኅብረት እንዲኖሩና ተስማምተው እንዲሠሩ ማድረግ።**

«ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና» (ማቴ. 5:9)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ከምናሳይባቸው ዋነኛ መንገዶች አንዱ በሰዎች መካከል በንቃት ሰላምን ስናመጣ ነው ብሏል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊያደርጋቸው ከሚገቡ ዋነኛ አገልግሎቶች መካከል በሁለት ወገኖች መካከል ሰላምን ማምጣት ነው። እንዳላመታደል ሆኖ፣ ከራስ ወዳድነት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጆች እርስ በርስ ያለ-መስማማትና ፀብ ያጠቃቸዋል። በሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ማለት ይቻላል ለረጅም ዓመታት ያህል ሳይፈቱ የቆዩ አለመስማማቶች አይጠፉም። በአጥቢያዎች መካከልም ለረጅም ዓመታት የቆዩ አለመስማማቶች አሉ። እነዚህ እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን ለምንሰጠው ምስክርነት ዋነኛ መሰናክል ናቸው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ለዓለም በግልጽ የሚያሳየው አንድነታችን እንደ ሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 17:20-21)።



መሪዎች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ንቁ ሰላም አምጪዎች መሆናቸው አስፈላጊ ነው።

ሀ. መሪዎች ሰላምን የመጠበቅ ምሳሌዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኛዎቹ ጠንካራ አለመግባባቶች የሚነሡት በመሪዎች መካከል ነው። ቤተሰባቸው ወይም ብሔራቸው ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ስላልተስተናገደ፣ ወይም ሌላ መሪ አሳባቸውን ባለመስማቱ ስለ ተጐዱ፣ አንዱ መሪ ከሌላው መሪ ጋር ትግል ይጀምራል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሆኑ ሰዎች በመሪዎች መካከል ያለውን ኅብረት የሚያሰናክል ነገር ላለማድረግ ይወስናሉ። «ጳውሎስ እንዳለው፣ የክርስቶስን ስም ከማስደብ ይልቅ ቢበደሉ ይመርጣሉ (1ኛ ቆሮ. 6:7)።

ለ) መሪዎች ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ንቁ መሆን አለባቸው። በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል መለያየት እስከሚያድግና ሰዎች በስሜት ተነሣሥተው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያየ ጽንፍ እስኪይዙ ከመጠበቅ ይልቅ ገና በአማኞች መካከል መለያየት መፈጠሩን እንደ ሰሙ በነገሩ ውስጥ ራሳቸውን አስገብተው ለመፍታት ይሞክራሉ። ምንም እንኳን አንዳንድ አለመግባባቶች ራሳቸው ቢፈቱም፣ አብዛኛዎቹ አለመግባባቶች ለመፈታት እርዳታ የሚፈልጉ ናቸው።

መሪዎች በግንኙነቶች መካል የሚፈጠሩ ችግሮች ራሳቸውን እንዲፈቱ ተስፋ በማድረግ ለረጅም ጊዜ ክጠበቁ፣ ሦስት ነገሮች ይፈጠራሉ።

አንደኛ፣ ጊዜ በገፋ ቁጥር በነገሩ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች ስሜት እየተባባሰ ይሄዳል። ባል ሚስቱን ቢሰድብ፣ ወዲያው ይቅርታ እንዲጠይቅ ካደረግን፣ በባልና ሚስቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ማስተካከል እንችላለን። ነገር ግን ለብዙ ወራት ከቆየን፣ በሚስቲቱ ውስጥ ያለው ቁጣ እያደገ ይሄዳል። ባለቤቷን የሚያናድድ ነገር ማድረግ ትጀምራለች። ቁጣውና ምሬቱ ሲያድግ፣ ግንኙነቱን

መፈወስ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል።

ሁለተኛ፣ ባለመግባባቱ ውስጥ የሚሳተፉት ሰዎች ቁጥር ይጨምርና በሰዎች መካከል ሰላም ማምጣቱ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ባልና ሚስት ሲጣሉ፣ ሰዎች እንዲራሩላቸው ለማድረግ ሲሉ ጉዳታቸውን ለሰው ማውራት ይጀምራሉ። ስለዚህ ልጆቻቸው ከእነርሱ ጐን እንዲቆሙ ይገፋፋሉ። ከዚህ የተነሣ ቤተሰቦቻቸውን ችግሩ ውስጥ ይከትታሉ። ከዚያም ችግሩን ለጓደኞቻቸው ስለሚያማክሯቸው፣ ጓደኞቻቸውም ከጐናቸው ይቆማሉ። አሁን መሪው ሰላም ማምጣት ያለበት በባልና በሚስት መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በችግሩ ውስጥ በተሳተፉት ወገኖች መካከል በሙሉ ነው።

ሦስተኛ፣ ግጭቱ በተራዘመ ቁጥር፣ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ችግሩን መፍታት አስቸጋሪ ይሆናል። አትክልቱን ሳይጐዱ ገና ያቆጠቆጠን አረምን መንቀል በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ያ አረም የተክሉን ያህል ካደገና ሥሩ በጥልቀት ካደገ፣ አረሙን መንቀል አትክልቱን ይጐዳዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድ ጊዜ አለመግባባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተስፋፋ፣ መሪው አንዱ ወገን ፍትሐዊ እንዳልሆነ በማመን እርቁን እምቢ ስለሚል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።

ይህ ማለት መሪዎች በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ሰላም ከፈለጉ፣ ሰላም በማምጣት ላይ በንቃት ሲሳተፉ ይገባል። አለመግባባቶችን ልንቆጣጠርና አለመግባባቱ ከመስፋፋቱ በፊት እርቅ ለመፍጠር አፋጣኝ እርምጃ ልንወስድ ይገባል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሆኑ መሪዎች እግዚአብሔር ሰላምን ለማምጣት ጣልቃ እንዲገቡ እንደሚፈልግ ያውቃሉ። በችግሩ ላይ መጸለይ ብቁ እንዳልሆነ ያውቃሉ። ኃጢአትን ልንጋፈጠውና የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ዳግም ጤነኛ እንድትሆን ሰላም መስፈን አለበት።



9ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመሪዎች መካከል መከፋፈል የሚፈጠረው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ። ይህ ሲፈጠር ሰላም አምጪው ምን ሚና ሊኖረው ይችላል? ለ) በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል መከፋፈል የሚፈጠርባቸውን ምሳሌዎች ስጥ። ሰላም የሚያመጣ ሽማግሌ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? ሐ) ልዩነቶች ሲፈጠሩ በቶሎ አለመፍታት እንዴት ችግሩን ለመፍታት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ግለጽ። መ) አብዛኛዎቹ ሽማግሌዎች ችግሩን ቶሎ ለመፍታት ጥረት ውስጥ የማይገቡት ለምን ይመስልሃል? ሠ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የምታውቃቸው አንዳንድ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው? ሰላምን ለማምጣት እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሚና እንዲያመጣ ይፈልጋል:

## 9. ነገሮች ከሚገባው በላይ የሚሰማው ሰው አለመሆን:- ቅያሜንና ነቀፋን መቀበልን መማር።

በብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮች እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ካልሆኑ ስሜታቸው በጣም ስስ ስለሆነ በቀላሉ ይጐዳሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ሰላም ሳይላቸው ካለፈ፣ ያ ሰው አይወደኝም ብለው ያስባሉ። ወይም ከሌላ ብሔር የሆነ ሰው ስብሰባ ከቀረ፣ ሰውየው ያንን ያደረገው የእርሱን ብሔር ስለማልወደው ነው ብለው ያስባሉ። በጣም በቀላሉ የሚሰማው (የሚቀየም) ሰው መሆን መሪዎችን በተለያዩ መንገዶች ምላሽ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል:-

ሀ. መሪው በጣም ቁጥጥር ያበዛል። ብዙ ጊዜ መሪዎች ቁጥጥር ሲያበዙ፣ ያንን የሚያበዙት ለራሳቸው ዋስትና ስለሌላቸውና በእግዚአብሔር ስለማያምኑ ነው። ሰዎች እነርሱ የማይፈልጉትን ነገር ያደርጋሉ ብለው በመፍራት፣ ብዙ መሪዎች ውሳኔውን ሁሉ ሌሎች ሰዎችን ሳያሳትፉ ይወስናሉ። ወይም ከእነርሱ በተሻለ ሁኔታ መስበክና ማስተማር የሚችል ሰው ይመጣል ብለው ስለሚፈሩ፣ ሌሎች ሰዎች እንዳያገለግሉ በማድረግ የተቀቡ ወጣቶችን ያባርራሉ። መሪዎች ይበልጥ ዋስትና የሚሰማቸው በእግዚአብሔር መታመንን በመማር ነው። የእግዚአብሔርን ክብር ይፈልጋሉ፣ ስለዚህ ማን ለስኬት በቃ